# መሠረተ ሕይወት

## ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

**ለሙዓለ ሕፃናት**

ተማሪዎች የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ

www.zeorthodox.org

አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ነሐሴ

፳፻፫ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፫ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

አድራሻ፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

www.zeorthodox.org


Email:- kesisolomon@gmail.com
Website፡- www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ። በመጨረሻም የሚያስ ፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም።

## መታሰቢያነቱ




በትምህርተ ቤተ ክርስቲያንና በክህነት ወልደው ላሳደጉኝ ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ይሁንልኝ።

www.zeorthodox.org

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል።

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | ዐውደ ዓመት | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | ሥነ ፍጥረት/አንድ/ | 4 | | ሁለተኛ | |
| 3. | ሥነ ፍጥረት/ሁለት/ | 7 | | ሦስተኛ | |
| 4. | ሥነ ፍጥረት/ሦስት/ | 10 | | አራተኛ | |
| 5. | አዳም ለእንስሳት ስም አወጣላቸው | 12 | | አምስተኛ | |
| 6. | አዳም እና ሔዋን በገነት | 14 | | ስድስተኛ | |
| 7. | የተወደደው የአቤል መሥዋዕት | 16 | | ሰባተኛ | |
| 8. | ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ታዘዘ | 18 | | ስምንተኛ | |
| 9. | ኖኅ ያቀረበው መሥዋዕት | 20 | | ዘጠነኛ | |
| 10. | ማክበር ያስባርካል | 21 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | የሰናዖር ግንብ | 23 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | የአብርሃም መጠራት | 25 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | አብርሃም እና ሎጥ | 27 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | አብራም በካህኑ ተባረከ | 29 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | ኢየሱስ እናቱን ይታዘዛት ነበር | 31 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ኢየሱስ ተጠመቀ | 33 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | አሮጊቷ ሣራ ወንድ ልጅ ወለደች | 35 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | ሕፃኑ ሙሴ | 37 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | ያዕቆብ በቤቴል ያየው ሕልም | 39 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | ይስሐቅ እና ርብቃ | 41 | | ሃያኛ | |
| 21. | ርብቃ መንታ ልጆችን ወለደች | 44 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም ተረጎመ | 46 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | የጥበብ ሰዎች | 48 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | ወደ ግብጽ ሸሹ | 50 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | ያዕቆብ እና ዔሳው ታረቁ | 52 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | ታዛዡ ይስሐቅ | 54 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ይስሐቅ ክፉውን በበጎ አሸነፈ | 56 | | ሃያ ሰባተኛ | |
| 28. | ዮሴፍ ለቤተሰሱ ይቅርታ አደረገ | 58 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ሳሙኤል ዳዊትን ቀባው | 60 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | ዳዊት ጎልያድን አሸነፈ | 63 | | ሠላሳኛ | |


www.zeorthodox.org

| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 31. | ዳዊት እና ዮናታን | 65 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | ተአምረኛው ዓሣ አጠማመድ | 68 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | ጌታችን ዓይነ ሥውሩን አዳነ | 70 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | ነቢዩ ኤልያስ በቁራዎች ተመገበ | 71 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | ነቢዩ ኤልያስ እና መበለቲቱ /አንድ/ | 73 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | ነቢዩ ኤልያስ እና መበለቲቱ /ሁለት/ | 75 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | የሦስቱ ሕፃናት ጽናት | 77 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ ተጣለ | 79 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | በማኅፀን የተቀደሰ ነቢይ | 81 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ | 83 | | ዐርባኛ | |
| 41. | የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት | 85 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | የጌታችን ልደት | 87 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | መላእክት እና እረኞች | 89 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | ዮሴፍ በአባቱ ቤት | 90 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ሳሙኤል በእግዚአብሔር ተጠራ | 92 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | ዮሴፍ ወደ ግብጽ ወረደ | 95 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | በገና ደርዳሪው ዳዊት | 97 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | አቡነ አረጋዊ | 99 | | ዐርባ ስምንተኛ | |
| 49. | እምነትሽ አድኖሻል | 101 | | ዐርባ ዘጠነኛ | |
| 50. | የመበለቲቱ ትልቅ ስጦታ | 103 | | ሃምሳኛ | |
| 51. | ሆሣዕና | 105 | | ሃምሳ አንደኛ | |
| 52. | የጌታ ትንሣኤ | 107 | | ሃምሳ ሁለተኛ | |
| 53. | በቃል የማጠኑ ትምህርቶች | 109 | | ሃምሳ ሦስተኛ | |
| 54. | ፍልሰታ | 113 | | ሃምሳ አራተኛ | |



www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጎቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሠራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ

ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ ዐሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸዉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸዉ። በዚህም መሠረት ጥርት ያለዉን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸዉ እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸዉ መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎ ቻቸዉም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

www.zoorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ

ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣ ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለዉን ርእስ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸዉን ተረድተዉና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

በመጨረሻም ይኸን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

# ዐውደ ዓመት

## አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ:-** ልጆች ስለ ዘመን መለወጫ በዓል አውቀው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** *"አቤቱ አንተ በቸርነትህ ዘመናትን ታቀዳጃለህ፡፡" መዝ. ፷፬ (፷፭) ፥ ፲፩*

## መግቢያ

- በየዓመቱ የመጀመሪያው ቀን የሚከበረው በዓል ዐውደ ዓመት ይባላል፡፡ ስለዚህ በዓል በዛሬው ትምህርታችን እናያለን፡፡
- የሚከተሉትን ጥያቄዎች እና መልሶቻቸውን አጥኑ፡፡

1. የመጀመሪያው ወር ማን ይባላል?
   - መስከረም ይባላል፡፡
2. በወር ውስጥ ስንት ቀናት አሉ?
   - ሠላሳ፡፡
3. የመጀመሪያ አምስት ቀናትን ቊጥር ጥሩ?
   - አንድ (፩)
   - ሁለት (፪)
   - ሦስት (፫)
   - ዐራት (፬)
   - አምስት (፭)
4. በአዲስ ዓመት ለቤተሰብ እና ለወዳጆቻችን መልካም ምኞታችንን ለመግለጽ ምን ይባላል?
   - እንኳን አደረሳችሁ እና መልካም አዲስ ዓመት ይባላል፡፡
5. በአዲስ ዓመት ከሚታሰቡ ቅዱሳን አንዱን ተናገሩ፡፡
   - መጥምቁ ዮሐንስ

www.zeorthodox.org

## የትምህርቱ ዋና ይዘት

- ልጆች ዛሬ ስለ ዐውደ ዓመት እንማራለን፡፡
- በሀገራችን የዓመቱ የመጀመሪያ ቀን መስከረም አንድ ቀን ይባላል፡፡ በዚህ ቀን አዲሱ ዓመት መጀመሩ የሚነገርበት እና መልካም ዘመን እንዲሆን የሚታወጅበት ቀን ነው፡፡ የወሩን ስም በቢጫ ቀለም ቀቡ፡፡

መስከረም

አ = አንድ

- በዓመቱ መጀመሪያ መስከረም አንድ ቀን በሀገራችን ያሉ ሕፃናት በወረቀት ላይ ሥዕል እየሣሉ ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት እና በቅርብ ላገኙት ሰው በመስጠት መልካም ምኞታቸውን ይገልጣሉ ፡፡ ሥዕላቱም የቅዱሳን መላእክትና የአበባ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ሥዕላት በተመሳሳይ ቀለማት ባዶውን ሙሉ፡፡



- በዚህ ዕለት አሮጌውን ዘመን አሳልፎ ወደ አዲሱ ዘመን ላሸጋገረን ለእግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ምስጋና ይቀርባል፡፡

**መዝሙራት፡-**

1 ለዚህ ላደረሰን በሰላም በጤና
ሃሌ ሃሌ ሉያ (4) እናቅርብ ምስጋና

ዐውደ ዓመት ለባርኮ
ንዒ ማርያም ለምሕረት ወሣህል

- በዚህ ዕለትም ዘመናትን ለመሸጋገራችን ምሳሌ የሆኑ ታሪኮች እና በዕለቱ በእግዚአብሔር ኃይል የተፈጸሙ የቅዱሳን መታሰቢያዎች ይከበራሉ፡፡ ከእነዚህም፦
  - ሀ. ኢዮብ፦ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን እያለ ሁሌም የሚያመሰግን ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው ነበር፡፡ መስከረም አንድ ቀን መታሰቢያው ስለሆነ ይከበራል፡፡
  - ለ. ኤልያስ፦ በእሳት ሠረገላ ተጭኖ ወደ ሰማይ ያረገ ነቢይ ነው፡፡
  - ሐ. ዮሐንስ፦ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን መካከል የነበረ ነው፡፡ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያጠመቀ ቅዱስ ነው፡፡ በአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ቀን መስከረም አንድ ቀን መታሰቢያው ይከበራል፡፡
- ይህን ቀንም በየዓመቱ እናከብረዋለን፤ መጠሪያውንም በዓመቱ ካሉት በዓላት ለመለየት ዐውደ ዓመት ይባላል፡፡

## *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመምህሩ ጋር እየተወያያችሁ አጥኑ፡፡*

1. በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ቀን የሚከበረው በዓል ምን ይባላል?
   ሀ. ዐውደ ዓመት ለ. ፋሲካ ሐ. ልደት
2. ሕፃናት ለምን በአዲሱ ዓመት ስጦታ ይሰጣሉ?
   ሀ. ለመመረቅ ለ. ለወላጆቻቸው እና ለጎረቤት መልካም ምኞታቸውን ለመግለጥ፡፡
   ሐ. ሁሉም መልስ ነው፡፡
3. ዐውደ ዓመት ማለት ምን ማለት ነው?
   ሀ. የዓመቱ መጨረሻ ወር ለ. የዓመቱ መጀመሪያ ወር ሐ. የዓመቱ መጀመሪያ በዓል

www.zeorthodox.org

# ሥነ ፍጥረት (አንድ)

## ሁለተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ:-

- ልጆች እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸው ፍጥረታት አውቀው ስለ ፍጥረታቱ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፤ ሐሳባቸውን በሥዕል ይገልጻሉ።

### የሚጠና ጥቅስ:-

- *‹‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድርን ፈጠረ››* ዘፍ. ፩ ፥ ፫

### መግቢያ

- ልጆች በሳምንት ውስጥ ስንት ቀናት አሉ? በስም ታውቋቸዋላችሁ? ማን ማን ይባላሉ? የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሯቸው።

በሚከተለው ሰንጠረዥ ያሉትን የሳምንቱ ቀናት በግእዝ እና በአማርኛ አጥኑ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰኑይ | ሠሉስ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቀዳሚት | ሰንበት |
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሑድ |

ልጆች ዛሬ እግዚአብሔር በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት የፈጠራቸውን ፍጥረታት እንማራለን።

### የመግቢያ ጥያቄዎች

1. ልጆች የምትረግጡትን መሬት እና ቀና ብላችሁ የምታዩትን ሰማይ ማን ፈጠረው? መቼ ተፈጠሩ?
2. ፍጥረታት ለምን ተፈጠሩ?

www.zeorthodox.org

## የትምህርቱ ይዘት

- እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን በስድስት ቀናት ፈጥሯቸዋል።

***የመጀመሪያው ቀን***

- ልጆች እግዚአብሔር የምናየው ሰማይ እና የቆምንባት ምድር ሳይኖሩ ብቻውን ነበረ። ክብሩን ሊያካፍለን ፈልጎ ፈጠረን።

- እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረታት ብዙ ናቸው። በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድርን ፈጠረ። አብሮም በሰማያት ያሉትን መላእክትን እና ጨለማንም ፈጠረ። ከዚያም ብርሃንን ፈጠረ።
- ከመካከላችሁ እነዚህን ፍጥረታት እግዚአብሔር እንዴት ፈጠራቸው ብሎ የሚጠይቅ ጉበዝ ተማሪ አለ? አዎን እግዚአብሔር እነዚህ ፍጥረታት እንዲፈጠሩ ስላሰበና ስለፈቀደ ምንም ሳይናገር ተፈጠሩ፤ ሳይናገር በሐሳቡ ብቻ መፍጠር የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
- በዚህ መሠረትም በመጀመሪያው ቀን ሌሊት ዐራቱ ባሕርያት የሚባሉትን ፈጠረ። እነርሱም
  1. ውኃ፣
  2. መሬት፣
  3. ነፋስ
  4. እሳት ናቸው።
- ጨለማም በዚህ ጊዜ ተፈጥሯል።
- ከዚያም ሰማይ ተፈጠረ።
  - ኦሪት ዘፍጥረት "***በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድርን ፈጠረ።***" ዘፍ. ፩፥፩ ያለን ለዚህ ነው።
- ከዚያ በኋላም በዚያው ሌሊት በሰማያት የሚኖሩትን መላእክትን ፈጠረ ።
- መፍጠር በጀመረ በአሥራ ሁለተኛው ሰዓት ‹‹***ብርሃን ይሁን***›› ብሎ ብርሃንን ፈጠረ። እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዲሁም መላእክትንና ጨለማን ምንም ሳይናገር ፈጠራቸው፤ ብርሃንን በመናገር ፈጠረ። ይህንንም መልካም እንደሆነ አየ። ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ አንድ ቀን።
- ይህች እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር የመጀመሪያ ያደረጋት ቀን እሑድ ትባላለች።
- በዚህ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሔር ስምንት ፍጥረታትን ፈጥሯቸዋል። እነርሱም ውኃ፣ መሬት፣ ነፋስ፣ እሳት፣ ጨለማ፣ ሰማይ፣ መላእክትን እና ብርሃን ናቸው።

www.zeorthodox.org

## ሁለተኛው ቀን

- ልጆች ሰኞ ሁለተኛዋ የፍጥረት ቀን ናት። እግዚአብሔር በዚህች ዕለት ውኃን ለይቶአል።
- እሑድ የተፈጠረው ውኃ ከምድር እስከ ሰማይ የሞላ ነበር። መሬትም ከውኃ ጋር ተቀላቅላ ነበር።

- ሰኞ ዕለት እግዚአብሔር "*በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን፣ በውኃና በውኃ መካከልም ይክፈል።*" አለ፤ ውኃ ተለየ፤ አንዱን እጅ ከጠፈር በላይ ሌላውንም ከምድር በታች አደረገው። በመካካልም ጠፈርን አደረገ።

***ሦስተኛው ቀን***

ማክሰኞ የሥነ ፍጥረት ሦስተኛ ዕለት ናት። በዚህች ቀን እግዚአብሔር ምድርን ከውኃ ለይቶ በነፋስ አደረቃት። ከሥር እና ዙርያዋንም ውኃ አደረገላት፣ ያንንም ባሕር አለው።

- ከዚህ በኋላም "***ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል።***" ብሎ እግዚአብሔር አዘዘ።
- ምድርም አትክልትን አዝርዕትን እና ዕፅዋትን አስገኘች። ባዶዋን ምድር እግዚአብሔር ፍሬያማ አደረጋት።
- ልጆች አትክልት ምንድነው? አዝርዕትስ? ዛፎችንስ በደንብ ታውቃላችሁ? ልዩነታቸውን ከመምህር ጋር ተነጋገሩ።

***ማጠቃለያ ጥያቄዎች***

1. ልጆች ያለንን እና የምንወደውን ለሌሎች እናካፍላለን?
2. እግዚአብሔር ለምን ፈጠረን?
3. እግዚአብሔር መፍጠር የጀመረው መቼ ነው?
4. በዚሁ የመጀመሪያው ቀን ስንት ፍጥረታት ተፈጠሩ? በስም ዘርዝሩ።

## ተግባር

1. በምታዩት ቀለም መሠረት ሥዕላቱን ቀቡ።
2. የአንድ መልአክ፣ የዝናብ ውኃ ሲንጠባጠብ እና የእሳት ነበልባል ሥላችሁ ለመምህር አሳዩ።
3. ከቤተሰብ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ አንብባችሁ እግዚእብሔር ስለ ፈጠራችሁ አመስግኑት።
4. የሚከተለውን መዝሙር አጥኑ።

www.zeorthodox.org

| *<u>መዝሙር</u>* | *<u>ትርጉም</u>* |
|---|---|
| ዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድር ሣረረ | ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና |
| አልቦ ዘየአብዮ ለአምላክነ | አምላካችን የሚሳነው የለም (ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ ያለ አንተ ማን አለና) |

# ሥነ ፍጥረት (ሁለት)

## ሦስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ

- በረቡዕና በሐሙስ ዕለታት የተፈጠሩትን ፍጥረታት አውቀው ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ:-

- ***‹‹እርሱ ተናግሮአልና፥ ሆኑም እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም፡፡››*** መዝ. ፴፫፥፱

### <u>የክለሳ ጥያቄዎች:-</u>

ልጆች ባለፈው ትምህርታችን የተማርነውን ታስታውሳላችሁ? ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. በመጀመሪያ ቀን የተፈጠሩ ፍጥረታት ስንት ናቸው? አንድ በአንድ ተናገሩ፡፡
2. ውኃ መቼ ተፈጠረ? በአንድ ላይ የነበረው ውኃ መቼ ተሰባሰበ?
3. ብርቱካን፣ በሰፈራችን የምናያቸው ዛፎች፣ ዳቦ የሚሠራበት ስንዴ መቼ ተፈጠሩ?

ልጆች ከላይ የተጠየቃችሁትን በደንብ አስታውሳችሁ መለሳችሁ? አሁን ወደ ቀጣዩ የሥነ ፍጥረት ታሪክ እናመራለን፡፡

## መግቢያ

- በሥነ ፍጥረት ክፍል አንድ ትምህርታችን አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት የፈጠራቸውን ፍጥረታት ተምረናል፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም እግዚአብሔር በቀጣዮቹ ሁለት ቀናት (ረቡዕ እና ሐሙስ) የፈጠራቸውን እንማራለን፡፡

www.zoorthodox.org

### የመግቢያ ጥያቄዎች:-

1. ቀን ቀን በሰማይ ላይ እያበራች ብርሃን የምትሰጠው ማን ትባላለች? በማታ የምታበራውንስ ስምዋን ታውቃላቸው? ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ ሥዕላቸውን ሥላችሁ ለመምህር መልሱ፡፡

| | |
|---|---|
| | |

2. ስንት ዓይነት አዕዋፋት ታውቃላችሁ?

3. ቤት ውስጥ ስንት እንስሳት አሉ ? (ለምሳሌ ውሻ፣ ድመት፣ በግ... አሉ? )

4. እነዚህ ሁሉስ መቼ ተፈጠሩ?

***የረቡዕ ፍጥረታት፡-***

- ***ረቡዕ ዐራተኛው የሥነ ፍጥረት ቀን ነው፡፡*** እግዚአብሔር በዚህ ዕለት ቀንና ሌሊትን እንዲለዩ እና ቀናትን ለመቍጠር እንዲረዱ፡ ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት ይፈጠሩ ሲል ሦስቱም ተፈጠሩ፡፡
- ፀሐይን በቀን ጨረቃ እና ከዋክብትንም በሌሊት እንዲያበሩ አደረገ፡፡ እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ፡፡

www.zeorthodox.org

***የሐሙስ ፍጥረታት፡-***

- አምስተኛው ቀን እግዚአብሔር በሰማይ የሚበሩትን እና በውኃ ውስጥ የሚኖሩትን ፈጥሯል፡፡
- በዚህ ቀን እግዚአብሔር ***"ውኃ ሕያው ተንቀሳቃሽ የሆኑ እንስሳትን ታስገኝ"*** አለ፡፡ ዓሣ፣ አዞ የመሳሰሉት በውኃ ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታት ተገኙ፡፡
- ከዚያም "***በሰማይ አዕዋፋት ይሁኑ***" ሲል የወፍ ዘሮች በሙሉ ተገኙ፡፡ እነ ርግብ ፤ ቁራ፤ አሞራ በሰማይ የሚበሩ አእዋፍ በዚህ ቀን ተፈጠሩ፡፡
- እግዚአብሔርም ይህም መልካም እንደሆነ አየ፡፡

## ማጠቃለያ

- ረቡዕ እና ሐሙስ እግዚአብሔር ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት ፣በውኃ የሚኖሩ እና በሰማይ የሚበሩትን ፍጥረታት ሁሉ አስገኘ።

### የማጠቃለያ ጥያቄዎች፡-

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ቀን እና ሌሊትን እንዲለዩ የፈጠራቸው ማንን ነው?

________________________________________

አዕዋፋት መቼ ተፈጠሩ?

________________________________________

ከእንስሳት በጣም የምትወዱት ማንን ነው ? ሣሉት።

________________________________________

## ተግባር

- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የአበባ እና የዛፎች ስም ጠይቃችሁ ዝርዝራቸውን ለመምህራችሁ ግለጹ።
- የሚከተለውን መዝሙር ዘምሩ።

www.zeorthodox.org

| <u>መዝሙር</u> | <u>ትርጉም</u> |
| --- | --- |
| ዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድር ሣረረ | ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና |
| አልቦ ዘየአብዮ ለአምላክነ | አምላካችን የሚሳነው የለም (ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ ያለ አንተ ማን አለና) |

# ሥነ ፍጥረት (ሦስት)

## ዐራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ:-**

- ልጆች ዓርብ ቀን የተፈጠሩትን ፍጥረታት አውቀው ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፤ በሥዕል ይገልጻሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-**

- ***" እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ፡፡"*** ዘፍ. ፩፥፴፩

**የክለሳ ጥያቄዎች፡-**

- በዕለተ ረቡዕ ማን ማን ተፈጠሩ? ሐሙስስ?
- ባለፈው ሳምንት ያጠናነውን ጥቅስ ለመምህር ድገሙላቸው?

## መግቢያ

- ልጆች እስከ አሁን አግዚአብሔር በመናገር እና በማዘዝ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ተምረናል፡፡
- በዛሬው ትምህርታችን በመጨረሻዋ የሥነ ፍጥረት ዕለት የተፈጠሩትን ፍጥረታት እንማራለን፡፡

**የመግቢያ ጥያቄዎች፡-**

- የምድር አራዊት እና የቤት እንስሳት ልዩነታቸው ምንድነው? ሰው እንዴት ተፈጠረ?

## የትምህርቱ ዋና ይዘት

***የዓርብ ፍጥረታት፡-***

www.zeorthodox.org

- ዓርብ የፍጥረት የመጨረሻው ዕለት ነው፡፡ በዚህ ቀን በምድር የሚኖሩ እንስሳት እና ሰው ተፈጥረዋል፡፡

**በምድር የሚኖሩ እንስሳት**

- ዓርብ ሌሊት እግዚአብሔር ***"ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፣ እንስሳትንና*** ተንቀሳቃሾችን ***የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ፡፡"*** አለ፡፡
- በምድር ላይ የምናያቸው፡- በግ፣ ድመት፣ አንበሳ፣ ዘንዶ የምንላቸው ከሰው ጋር የሚኖሩ እና በዱር የሚኖሩት በሙሉ በእግዚአብሔር ቃል ምድር ታውጣ ተብሎ ሲታዘዝ ከምድር ተፈጠሩ፡፡ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ፡፡

- እነዚህን እንስሳትም በየወገናቸው ከፋፍሎ አስቀመጠ፡፡
- የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፥ አንበሳን፣ ነብርን፣ ጅብን ሌሎቹንም የዱር እንስሳት በጫካ እንዲኖሩ አደረገ፡፡
- እንስሳውንም እንደ ወገኑ፥ በቤት የሚኖሩትን እና ሰውን የሚያገለግሉትን በግ፣ በሬ፣ አህያ ሌሎቹንም የቤት እንስሳት አደረገ፡፡
- የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ፡፡
- ልጆች እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ በቃሉ በማዘዝ ብቻ አስገኝቶዋል፡፡

## ሰው

- "***እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር አለ፡፡*** " በዚህ መሠረትም ዓርብ በጠዋት ሰውን ከምድር አፈር ወስዶ ሠራው፤ ከዚያም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፡፡ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ፍጥረት ሆነ፡፡
- ከዚህ በኂላም በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ ጣለበት ከጐኑም ሔዋንን ፈጠራት፡፡ ወንዱ አዳም ሴቲቱም ሔዋን ተባሉ፡፡
- ***እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እጅግም መልካም ነበረ፡፡***
- ልጆች እግዚአብሔር እስከ አሁን ስለፈቀደ እና በማዘዝ ብቻ ሲፈጥር ነበር፡፡ ሰውን ሲፈጥረው ግን በእጁ ሠራው፤ የምናመልከው እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ማድረግ የሚችል አምላክ ነው፡፡

# ማጠቃለያ

- ***ዓርብ*** እግዚአብሔር በምድርም የሚመላለሱትን እንስሳት እና ሰውን ፈጠረ፡፡

### የማጠቃለያ ጥያቄዎች፡-

1. አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ቀን እና ሌሊትን እንዲለዩ የፈጠራቸው እነማንን ነው? የምድር አራዊት ከምንላቸው ሁለቱን ተናገሩ?

www.zeorthodox.org

---

2. ዓርብ እግዚአብሔር ምን ምን ፈጠረ? ከእንስሳት በጣም የምትወዱት ማንን ነው? በሥዕል ስላችሁ አሳዩ፡፡

---

# ተግባር

ሰው ሁሉ አክብሩ፡፡ ያለፈውን ሳምንት መዝሙር ዘምሩ፡፡

# አዳም ለእንስሳት ስም አወጣላቸው

## አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ልጆች ስም ማውጣት እንዴት እንደተጀመረ ተገንዝበው ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

- *"በስሙ እንደጠራው ስሙ ያው ሆነለት፡፡"* ዘፍ. ፪ ፥ ፲፱

**የክለሳ ጥያቄዎች፡-**

1. ልጆች የራሳችሁን እና የቤተሰባችሁን ስም ትርጉም ታውቁታላችሁ? መልሳችሁ አዎን ከሆነ ለመምህር አብራሩ፡፡
2. በቤታችሁ ያሉትን እንስሳት ስምስ ታውቃላችሁ? እስኪ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው፡፡

## መግቢያ

- ልጆች ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ፍጥረታትን እንዴት እንዳስገኘ ተምረናል፡፡
- ዛሬ ደግሞ ፍጥረቱን እንዲገዛ የተሾመው አዳም ለእንስሳት ስም እንዳወጣላቸው እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

- አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ፈጥሮ አጠናቀቀ፡፡ በጣም ስለሚወደንም አባታችንን አዳምን በመጨረሻ ፈጠረው፡፡
- ከዚያም በምድር ያሉትን ሁሉ እንዲገዛ ሥልጣን ሰጠው፡፡ አዳም የምድር ንጉሥ ሆኖም ተሾመ፡፡
- ***እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ፤*** ስም እንዲያወጣላቸውም ወደ አዳም አመጣቸው፡፡
- እንስሳቱ ብዙ ነበሩና አዳም ተራ በተራ በቋንቋው ስም አወጣላቸው፡፡

- እሑድ እንስሳትን እና አራዊትን በግ፣ አንበሳ፣ ሚዳቋ፣ ዝሆን፣ በሬ፣ ውሻ እያለ ለሌሎቹም ሁሉ ስም አወጣላቸው፡፡
- ሰኞ እና ማክሰኞ ወፎችን አመጣለት፡፡ ርግብ፣ ዶሮ፣ አሞራ፣ እያለ ስም አወጣላቸው፡፡
- ረቡዕ እና ሐሙስ በባሕር የተፈጠሩትን ፍጥረታት ዓሣ፣ አዞ፣ ዘንዶ፣ ዶልፊን ወዘተ እያለ በየራሳቸው መጠሪያ እንዲኖራቸው ስም አወጣላቸው፡፡
- ዛሬም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጠመቅ ስንመጣ ከምድራዊ መጠሪያችን ሌላ የክርስትና ስም ፡- ወልደ ሥላሴ፣ እኅተ ማርያም፣ ኃይለ ኢየሱስ ወዘተ እየተባለ በካህናት ስም ይሰጠናል፡፡

## ማጠቃለያ

- አዳም በእንስሳት ሁሉ ላይ ንጉሥ ሆኖ ስለተሾመ አዳም እንዳወጣላቸው የእንስሳት ስም ሁሉ ያው ሆነ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. አዳም ለእንስሳት ስም እንዲያወጣ ያደረገው ማን ነው?

---

2. የክርስትና ስም የሚያወጣልን ማን ነው ?

---

## ተግባር፡-

www.zeorthodox.org

- ክርስትና ስም የወጣላችሁ መቼ እንደሆነ እና ትርጉሙም ምን እንደሆነ ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ተረዱ፡፡

# አዳም እና ሔዋን በገነት

## ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ልጆች፤ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን መልካም ፈቃድ ተገንዝበው፤ አዳምና ሔዋን በገነት ስለነበረው ኑሮአቸው እና ስለተሰጣቸው ትእዛዝ ያውቃሉ፡፡ የሚሰጧቸውንም ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

- *" እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው"* ዘፍጥ. ፪ ፥ ፲፭

**ምንባባት፡-** ዘፍጥረት ፩ ፥ ፳፮ - ፪ ፥ ፳፭

**የክለሳ እና የመግቢያ ጥያቄዎች፡-**

- አዳም እና ሔዋን መቼ ተፈጠሩ? እንዴት እንደተፈጠሩስ ታስታውሳላችሁ?
- ልጆች ገነት ምንድን ነው? እግዚአብሔር አዳም እና ሔዋንን ለምን ወደ ገነት ያስገባቸው ይመስላችሁዋል?

## መግቢያ

- አዳም እና ሔዋን ከተፈጠሩ በኂላ ወደ ገነት አመጣቸው፡፡ ኃላፊነት እና ትእዛዝ ሰጥቶም አኖራቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### ገነት

- ገነት በጣም የምታምር በልዩ ልዩ ዕፅዋት የተዋበችና በልምላሜ ያጌጠች ደስ የሚያሰኙ አበቦች የሞሉባት ናት፡፡ የሚጣፍጡ እና የሚስማሙ ፍራፍሬዎችም በገነት አሉ፡፡
- የሕይወት ዛፍ የተባለ ሰዎች በልተውት ለዘላለም እንዲኖሩ የሚያደርግ ዛፍም በገነት አለ፤ በገነት መካካልም የበለስ ዛፍ ነበረ፡፡
- ገነትን የሚያጠጣ እና ከዚያም ለዐራት ክፍል የሚከፈል በጣም የሚያምር ወንዝም አለ፡፡
- ገነት አሁንም  እግዚአብሔርን የሚወዱ እና የታዘዙት የሚኖሩባት ናት፡፡

2. እግዚአብሔር አዳምን ወደ ገነት አስገባው፡፡

- ልጆች ሁሉን የሚያውቀው እግዚአብሔር ለአዳም የሚበጀውን ስለሚያውቅ ወደ ገነት አመጣው፡፡ ለምን አመጣው ?

    ሀ.  በገነት የደስታ ኑሮ እንዲኖር፣

www.zeorthodox.org

ለ. የምታምረውን ገነትን እግዚአብሔር በሰጠው ዕውቀት የበለጠ እንዲያሳምራት፣

ሐ. እንዲጠብቃት አዳምን በገነት አኖረው፡፡

3. የአዳም እና የሔዋን ኑሮ በገነት

- የደስታ እና የምሥጋና ነበር፡፡ እግዚአብሔርን እያመሠገኑ እና እየተደሰቱ ይኖሩ ነበር፡፡
- በገነት ሁሉም ሲፈቀድ አዳምና ሔዋን አንዲት ዛፍ ብቻ እንዳይበሉ ተከልክለው ነበር፡፡ ምክንያቱም ቢበልዋት እንደሚጎዱ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ እና ትእዛዙን በመፈጸም እንዲጠብቁዋትም ነው፡፡
- ልጆች አዳም እና ሔዋን ከእንስሳቱ ጋር ይግባቡ ነበር፡፡ እንስሳቱ ሁሉ ወደ ጌታቸው ወደ አዳም እየመጡም ይባረኩ እና ይታዘዙት ነበር፡፡
- አዳም እና ሔዋን በዚህ ዓይነት ደስታ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየጠበቁ እና እየተደሰቱ በገነት ይኖሩ ነበር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ሰውን ወዳጅ የሆነው እግዚአብሔር ለአዳም እና ለሔዋን በጎነት ያደረገው ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሳ ነው፡፡
- ለዚህም ነው እጅግ በጣም በምታምረው እና በምታንጓው ገነት ያኖረው ዘንድ ሰውን ወደ ገነት ያመጣው፡፡
- አዳም እና ሔዋንም በዚህ ዓይነት ኑሮ ለእግዚአብሔር እየታዘዙ ኖሩ፡፡

## ተግባር

- የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቁ አዳምጡም፡፡ ቤተሰቦቻችን የሚመክሩንን እንፈጽም፡፡ በመታዘዝ ከኖርን እግዚአብሔር ይባርከናል፡፡

www.zeorthodox.org

***መዝሙር፡-***

አይ ይዕቲ ዛቲ እንተ ታስተርኢ እምርሑቅ ከመ ማኅቶት ደብረ ገነት

ሙሴኒ ርእያ ሀገር ቅድስት ዕዝራኒ ተናገራ (3) ዘመራ ዳዊት

***ጥያቄዎች፡-***

1. በገነት ምን ዓይነት ዕፅዋት ነበሩ?በገነት አዳም እና ሔዋን የተከለከሉት ምን ነበር?
2. እግዚአብሔር አዳምን ወደ ገነት ለምን አመጣው?

# የተወደደው የአቤል መሥዋዕት

## ሰባተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ልጆች፤ ስለ አቤልና ቃየን ሥራና መሥዋዕት አውቀው በንጽሕና በእግዚአብሔር ፊት መቆም እና መጸለይ እንዳሚገባ በመገንዘብ የተሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

- “እግዚአብሔርም ***ወደ አቤል እና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፡፡”*** ዘፍጥ. ፬ ÷ ፬

### ምንባባት፡-

- ዘፍጥረት ፬ ÷ ፩ - ፳፤ ዕብራውያን ፲፩ ÷ ፬

### የክለሳ እና የመግቢያ ጥያቄዎች፡-

- አዳም እና ሔዋን ምን ታዘዙ?
- ስለ አዳም እና ሔዋን የመጀመሪያዎቹ ልጆች ምን ታውቃላችሁ ? ስማቸውስ ማን ይባል ነበር ?
- የአቤል መሥዋዕት ምን ዓይነት ቢሆን ነው እግዚአብሔር የተመለከተለት ?

### መግቢያ

- ልጆች አዳም እና ሔዋን በእግዚአብሔር ፍቃድ ልጆችን ወለዱ፤ የመጀመሪያው ቃየን ሁለተኛውም አቤል ይባሉ ነበር፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም ሁለቱም ስለ አቀረቡት መሥዋዕት እንማራለን፡፡

## የትምህርቱ ዋና ይዘት

www.zeorthodox.org

- አቤል በግ ጠባቂ ነበር፤ቃየንም ምድርን የሚያርስ ገበሬ ነበር፡፡
- ሁለቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሊያቀርቡ ተዘጋጁ፤ አቤል በቅንነት ለእግዚአብሔር የተሻለውን ከመንጋው መርጦ ንጹሑንም አዘጋጅቶ መሥዋዕቱን አቀረበ፡፡
- ቃየን ግን እግዚአብሔር አይበላውም ብሎ በግድየለሽነት ንጹሑን ከተበላሸው ስንዴ ጋር ቀላቅሎ አቀረበ፡፡
- እግዚአብሔርም ወደ አቤል እና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፡፡ ምክንያቱም አቤል በንጹሕ ልብ መሥዋዕቱን ለእግዚአብሔር ብሎ ያቀረበው ስለነበር በእግዚአብሔር ፊት ተወደደ፡፡

- የቃየንን መሥዋዕት ግን እግዚአብሔር አልተመለከተውም ፡፡ ምክንያቱም ቃየን በክፉ ሐሳብ ሆኖ፤ በወንድሙ በመቅናት ያቀረበው መሥዋዕት ነበር፡፡ ከዚህም በላይ መሥዋዕቱን በግድየለሽነት ሰብስቦ ነበር ያቀረበው፡፡
- ጸሎት እና መዝሙር ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መሥዋዕት ነው፡፡ ስለዚህም ስትዘምሩም ሆነ ስትጸልዩ በንጹሕ ልብ፣ ፍጹም በሆነ ፍቅርና ትሕትና በትኩረት መሆን አለበት፡፡
- ከወንድሞቻችን እና እኅቶቻችን ጋር ያለን ግንኙነት ከክፋት እና ከቅናት በመራቅ መሆን ይገባዋል፡፡

## ማጠቃለያ

- የአቤልን መሥዋዕት እግዚአብሔር የወደደው የቃየንንም መሥዋዕት እግዚአብሔር ያልተመለከተው በልባቸው ባሰቡት እና በድርጊታቸው በገለጡት ነገር ነበር፡፡

## ተግባር

- በቤተክርስትያን በጸሎት ጊዜ እግዚአብሔርን በመፍራት እና በትሕትና ልንቆም ይገባናል፡፡
- ልትቆርቡ ስትመጡ በንጽሕና እና እግዚአብሔርን በማክበር መሆን አለበት፡፡
- በክለሳ እና መግቢያ ጥያቄዎች የተቀመጠውን ሁለተኛና ሦስተኛ ጥያቄዎችን በድጋሚ ተወያዩባቸው፡፡

**መዝሙር**

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው (2) አምላኬ መመኪያዬ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች፡-**

1. የአቤል ሥራ ምን ነበር? የቃየንስ?

---

2. የአቤል መሥዋዕት ምን ነበር?

---

3. የቃየንን መሥዋዕት እግዚአብሔር ያልተቀበለው ለምንድነው?

---

# ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ታዘዘ

## ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ልጆች፤ ስለ ኖኅ እና የመርከቡ ታሪክ አውቀው እግዚአብሔርንም ስለ መታዘዝ በመገንዘብ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ ፡-**

- *‹‹መርከብን ለአንተ ሥራ››* ዘፍ ፮ ፥ ፲፬

**ምንባብ፡-** ዘፍ ፮፡፡

## መግቢያ

- ባለፈው ሳምንት አቤል በቅንነት ያቀረበውን መሥዋዕት እግዚአብሔር እንደተቀበለለት ተምረናል፡፡
- በዛሬው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የሆነው ኖኅ እንዲድን መርከብ ሥራ መባሉን እናያለን፡፡

**የመግቢያ ጥያቄዎች ፡-**

1. ልጆች መርከብ ዓይታችሁ ታውቃላችሁ ?
2. የመጀመሪያዋን መርከብ የሠራው ማነው

## የትምህርቱ ይዘት

- አባታችን ኖኅ በኖረበት ዘመን የነበሩ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ፡፡
- በዚያን ዘመን የቀረው መልካም ሰው ኖኅ ብቻ ነበር፡፡ ኖኅ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር፡፡
- እግዚአብሔር ኖኅን ጠርቶ ምድርን በውኃ ሊያጠፋ እንደሆነ ነገረው፣ መርከብም መሥራት እንዳለበት አዘዘው፡፡
- ኖኅ ሁሌም እንደሚያደርገው ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ሆኖ መርከብ ሠራ፡፡
- ከዚያም ኖኅ በእግዚአብሔር እንደታዘዘው ከሁሉም እንስሳት ሁለት ሁለት አስገባ፡፡ እንስሳቱም በደስታ ገቡለት፡፡ ዳክየዋ ... ኳክ... ኳክ፣ ላሞች... እምቧ... እምቧ፣ በጎች እምበ... እምበ እያሉ እየተጫወቱ በመርከብ ተቀመጡ፡፡

www.zoorthodox.org

- ከዚያም ኖኅ ቤተሰቡን በሙሉ አስገባ፡- ሚስቱ፣ ሦስት ልጆቹ እና የልጆቹ ሚስቶች በጠቅላላ ስምንት ነፍስ ሆነው ገቡ፡፡ ሁሉም ከገቡ በኋላ ኖኅ ወደ መርከቡ ገባ፡፡
- ከዚያም ከሰማይ ብዙ ዝናብ መዝነብ ጀመረ፤ ውኃም ከምድር እየፈለቀ እና ከላይ እየዘነበ ምድርን ሸፈናት፡፡ ይህም ለአርባ ቀን ሆነ፣ የኖኅ መርከብም መንሳፈፍ ጀመረች፡፡ ኖኅ እና ቤተሰቡ፣ ከእንስሳትና ከአዕዋፍ ወገን ወደ መርከብ የገቡት በሙሉ ዳኑ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- እግዚአብሔር የሚታዘዙትን እና የሚላቸውን የሚሰሙትን ይጠብቃል፡፡ እግዚአብሔር እንድናደርገው የሚፈልገውን ከፈጸምን ከኛ ጋር ይሆናል ይጠብቀናል፡፡

## ተግባር፡-

- **መምህር** ልጆች የራሳቸውን መርከብ ከወረቀትና ከልዩ ልዩ ነገሮች እንዲሠሩ ወይም በሥዕል እንዲያሳዩ ያድርጉአቸው፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ኖኅ መርከብ እንዲሠራ የታዘዘው ለምንድን ነው?

___________________________________

2. በኖኅ መርከብ ስንት ሰዎች ገብተው ዳኑ?

___________________________________

3. ውኃው እየዘነበ ስንት ቀን ቆየ?

___________________________________

www.zeorthodox.org

# ኖኅ ያቀረበው መሥዋዕት

## ዘጠነኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ

- ልጆች፤ ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ውኃ ከዳኑ በኋላ ኖኅ ስላቀረበው ምሥጋናና መሥዋዕት አውቀው ስላደረገለን ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ በመገንዘብ፤ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያና መልስ ይሰጣሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

- ‹‹***እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ፡፡***›› ዘፍ. ፰ ፥ ፳፩

### መግቢያ፡-

- እግዚአብሔር ኖኅን እና ቤተሰቡን እንዳዳነ ተምረናል፡፡ ዛሬም ኖኅና ቤተሰቡ ያቀረቡትን መሥዋዕትና የእግዚአብሔርን መልስ እናያለን፡፡

## የትምህርቱ ይዘት፡-

- በምድር ላይ የነበረው ዝናብና ጐርፍ ደርቆ ምድር ስትገለጥ ኖኅና ቤተሰቡ እንስሳትና አዕዋፍ ከመርከቡ ወጡ፡፡
- ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠውያውን ሠራ፣ ከንጹሐኑም ወስዶ በመሠውያው ላይ መሥዋዕትን አቀረበ፡፡
- እግዚኣብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ፤ እግዚአብሔርም "… ምድርን ዳግመኛ ስለ ሰው አልረግምም፡፡" አለ፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- አያችሁ ልጆች! እግዚአብሔር ንጹሕ አምላክ ስለሆነ ንጹሕ ነገር ይወዳል፡፡ ስለዚህ እናንተም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ስትመጡ፣ ንጹሕ ልብስ ልበሱ፣ ልባችሁ ከክፋት ከጥላቻ ይራቅ፤ አትጨቃጨቁ፡፡
- ቤተሰቦቻችሁ እና የቤተ ክርስቲያን መምህራን እግዚአብሔር የሚወደውን ሲነግሩአችሁ ስሙ ፡፡
- ኖኅ ከነ ቤተሰቡ ከእንስሳቱ ጋር ከመርከብ ከወጣ በኋላ ምን አደረገ? እግዚአብሔርስ ምን አለው?

# ማክበር ያስባርካል

## ፀሥረኛ ሳምንት

<u>የትምህርቱ ዓላማ፡-</u>

- ልጆች፤ ወላጆቻቸውን፣ አረጋውያንን እና ካህናትን በማክበር መባረክ እንደሚያስፈልግ በኖኅ ልጆች አርአያነት ተገንዝበው ለመምህሩ ጥያቄዎች ማብራሪያና መልስ ይሰጣሉ፡፡

<u>የሚጠና ጥቅስ፡-</u>

- " ***ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ፡፡"*** ፩ኛ ቆሮ ፲፪ ፥ ፴፩

## መግቢያ

- ልጆች! ኖኅ ስንት ልጆች ነበሩት? ስማቸውንስ ታውቃላችሁ ? ለመምህር ንገሩዋቸው፡፡
- ገበሬ ሥራው ምንድነው?

## ትምህርቱ

- ልጆች አባታችን ኖኅ እና ሦስቱ ልጆቹ ሴም፣ካም እና ያፌት መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር አቀረቡ፡፡
- እግዚአብሔርም ባረካቸው፤ ‹‹ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት›› አላቸው፡፡
- ከዚያም በኋላ ኖኅ ገበሬ ሆኖ አትክልት እና ፍራፍሬ እየተከለ ማረስ ጀመረ፡፡
- የወይን ዛፍም ተከለ እርስዋም ፍሬያማ ነበረች፡፡ ከዕለታት አንድ ቀንም ኖኅ ከወይኑ ጠጥቶ ዕርቃኑን ሆነ፡፡
- ከልጆቹ አንዱ ካም አባቱን አይቶ ለወንድሞቹ ነገራቸው፡፡
- ሁለቱ ወንድሞቹ ግን ሸማ የተባለ ጨርቅ ወስደው በትከሻቸው ላይ አደረጉ፤ የአባታቸውን ዕራቁትነት ላለማየትም የኋሊት ሄደው የአባቸውን ዕራቁትነት ለመሸፈን አለበሱ፡፡
- ኖኅም ሲነቃ ሁሉም ልጆች ያደረጉበትን አወቀ፡፡ ከዚያም ሁለቱን ልጆች ***"እግዚአብሔርም ያፌትን ያስፋ በሴምም ድንኳን ይደር"*** ብሎ ባረካቸው፡፡

www.zoorthodox.org

## ማጠቃለያ

- ልጆች ቤተሰብን ማክበር እና በሽማግሌ ላይ አለመቀለድ መልካም ነገር ነው፡፡ የወላጆቻ ችንንና የታላላቆቻችንን መልካም ምክር መቀበል፣ ትእዛዛቸውንም ማክበር እንዲሁም በዕድሜያቸው የገፉ ሽማግሌዎችን መርዳት በረከትን ያስገኝላችኋል፡፡

## ተግባር

- ታላላቆቻችሁን አክብሩ፤ ሰው ሲሳሳት ወይም ሲታመም ከቻልን እንረዳዋለን እንጂ አይሳቅም፡፡
- የቤተሰቦቻችሁንም መልካምነት ለሌላው ከማካፈል በቀር የማይወደደውን ነገር ለሌላው በማውራት አትቀልዱ፡፡
- ዛፎች ሳሉ እና በተለያዩ ቀለማት አስውቡት፡፡

### መዝሙር፡-

ባርከኒ አባ መፍቀሬ ሕፃናት ማትያስ*

እስመ አንተ ሰባኪ ወንጌል ሐዲስ ሰባኪ ወንጌል ሐዲስ

❅ ስሙ እንደየ ሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ስም ሊቀያየር ይችላል፡፡

www.zeorthodox.org

# የሰናዖር ግንብ

## ዐሥራ አንደኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ልጆች፤ ስለ ስለ ሰናዖር ሰዎች ታሪክ አውቀው መምህሩ ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች ምላሹን በክፍል ውስጥ ያብራራሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

- "ኑ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው፡፡" ዘፍጥ ፲፩ ፥ ፯ - ፰፡፡

### መግቢያ

- **ልጆች ረጅም ሕንጻ የሚባሉትን አይታችኋቸዋል? ዛሬ ለመጀመሪያ ግዜ ስለተሠራው ረጅም ግንብ እንማራለን፡፡**

### ትምህርቱ

- በድሮ ጊዜ ምድር በአንድ ቋንቋ እና በአንድ ንግግር ነበረች፡፡ ዛሬ በምድራችን ያሉ ሰዎች የሚናገሩዋቸው የተለያዩ ቋንቋዎች ዱሮ አልነበሩም፡፡
- ከዚያም ከምሥራቅ የተነሡ ሰዎች ሰናዖር በተባለ ቦታ አንድ ሰፊ ሜዳ አገኙ፤ በዚያም ተቀመጡ፡፡ ብዙ ሥራዎችን ይሠሩ እና ይፈጥሩ ጀመር፡፡ ከነዚህም አንዱ ጡብ መሥራት ነበር፡፡ ልጆች ጡብ ታውቃላችሁ? ቤት ለመሥራት የሚያገለግል ከሸክላ አፈር የሚሠራ የድንጋይ ዓይነት ነው፡፡
- ከዚያም ሰፊ ከተማ ሠሩ፤ በከተማውም በእነሱ ዕይታ እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ገነቡ፡፡ እነሱ ሰማይ የደረሰ ቢመስላቸውም ያን ጊዜ ፎቅ መሥራት ስላልተለመደ ነው እንጂ ሰማይ ሊደርስ ቀርቶ የዛሬዎችንም ታላላቅ ፎቆች አያክልም ነበር፡፡
- ይህን ለመሥራት ያሰቡትም ስማቸውን ለማስጠራት እና ፈጣሪ ላይ ለመድረስ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ይህን አየ፡፡ እግዚአብሔር በሐሳባቸው ቢያዝንም ለሰው ልጆች ነጻነት የሰጠ እርሱ ነውና ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አልከለከላቸውም ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

- ሥራቸውን ፈጽመው እግዚአብሔርን መሳደብ እና ክፉ ማድረግ ሲጀምሩም እግዚአብሔር ፈረደ እና ቋንቋቸውን ደባለቀባቸው፤ ለመግባባትም አልቻሉም፡፡ አንዱ በእንግሊዝኛ ሐመር ሲለው ሌላው በግእዝ መዶሻ ያለው እየመሰለው እርስ በርሳቸው ተጣሉ፡፡
- እግዚአብሔርም ከዚያ በምድር ሁሉ ላይ በተናቸው፣ ከተማዋን መሥራትም ሆነ አብሮ መኖር አልቻሉም፡፡ ስለዚህም ስምዋ ባቢሎን ተባለ፡፡

## ማጠቃለያ

- የሰናዖር ሰዎች ዓመጸኞች ስለሆኑ ቋንቋቸው ተደባለቀ፤ መግባባትም አልቻሉም፡፡

## ተግባር

- ማንኛውንም ነገር ስትሠሩ በእግዚአብሔር ስም አድርጉት፡፡

### ጥያቄ

1. እግዚአብሔር የሰናዖር ሰዎችን ቋንቋቸውን የደባለቀባቸው ለምንድን ነው? መምህር ልጆቹ መልሱን በክፍል ውስጥ እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
2. ቋንቋቸው የተደባለቀባቸው ሕዝቦች ከተማ ማን ትባላለች?

www.zeorthodox.org

# የአብርሃም መጠራት

# ዐሥራ ሁለተኛ ሳምንት

## የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ልጆች፤ ስለ አብርሃም ታሪክ አውቀው በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

## መግቢያ

- አብራም የአብርሃም የመጀመሪያ ስሙ ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የአብርሃምን ታሪክ የመጀመሪያ ክፍል እናያለን፡፡

## ትምህርቱ

- የአብራም አባት ታራ ይባላል፡፡ አብራም ናኮር እና ሐራን ከተባሉ ሁለት ወንድሞቹ ጋር በአባታቸው ፊት በዑር ይኖር ነበር፡፡
- ሐራን ሎጥን ወልዶ ሞተ፣ አብራም እና ናኮርም ሦራ እና ሚልካ የተባሉ ሚስቶች አገቡ፡፡
- ከዚያም ታራ ከአብራም ከሦራ እና ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር ከዑር ወደ ካራን መጡ፣ በዚያም ተቀመጡ፡፡ አባታቸው ታራም በካራን ሞተ፡፡
- እግዚአብሔርም አብራምን "***ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ፡፡ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ፤ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፡፡***" አለው፡፡
- አብራምም እግዚአብሔር እንደነገረው ሲወጣ ሎጥ እና ሚስቱ ሦራ አብረውት ወጡ፡፡ አብራምም ሲወጣ የሰባ ዓመት ሰው ነበር፡፡ ከካራን ወጥቶም በከነዓን ገባ፡፡
- ከካራን እንዲወጣ ያዘዘው እግዚአብሔር ተገለጠለትና "***ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ***" አለው፡፡
- አብራምም ለተገለጠለት ለእግዚአብሔር በዚያው መሠውያን ሠራ፣ በቤተል ምሥራቅ ወዳለው ተራራም ወጣ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- አብራም ቤተሰቡን በመልካሙ ምክር በመከተል እግዚአብሔር እስኪገለጥለት ኖረ፡፡
- እግዚአብሔር ሲጠራውም ሳያመነታ ከአገሩና ከዘመዶቹ ተለይቶ ከካራን ወጣ፤ ከነዓን ከሚባለው አገርም ገባ፤ እግዚአብሔርም ባረከው፡፡

## ተግባር

- እግዚአብሔር በቤተሰብ እና በቤተ ክርስቲያን መምህራን በኩል የሚነግረንን እንስማ፡፡

**ጥያቄ፡-**

1. የአብርሃም የመጀመሪያ ስሙ ማን ይባል ነበር?
2. የአብርሃም አባት ስም ማን ይባላል?
3. አብርሃም በአባቱ ቤት ከዘመዶቹ ጋር መጀመሪያ ይኖርበት የነበረው አገር ስም ማን ይባላል?
4. አብርሃም ይኖርበት የነበረውን አገሩን ትቶ እግዚአብሔር በነገረው መሠረት ሄዶ የገባበት አገር ማን ይባላል?

www.zeorthodox.org

# አብራም እና ሎጥ

## ዐሥራ ሦስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ልጆች የአብራም እና የሎጥን ታሪክ አውቀው ቅድሚያ ለእህቴና ለወንድሜ ማለትን ይገነዘባሉ፡፡ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎችም በክፍል ውስጥ መልስ ይሰጣሉ፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

- ***"እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ ..... መካከልም ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ፡፡"*** ዘፍጥ. ፲፫ ፥ ፰

### የክለሳ ጥያቄዎች፡-

1. አብራም እና ቤተሰቡ በመጀመሪያ የት ይኖሩ ነበር?

______________________________

2. የአብራም አባት እና ወንድሞች ስም ማን ነው?

______________________________

3. አብራም እግዚአብሔር ሲገለጥለት ምን አደረገ?

______________________________

www.zeorthodox.org

## መግቢያ

- በምድር ራብ ጸንቶ ነበርና አብራም ከቤተል ተነሥቶ፤ ወደ ግብጽ ወረደ፡፡ ከዚያም ወደ አዜብ ምድር ወጣ፡፡

## ትምህርቱ፡-

- አብራምም በከብት በብርና በወርቅ እጅግ በለጠገ፡፡ ቀድሞ በነበረት ሥፍራም የእግዚአብሔርን ስም ጠራ፡፡

- ከአብራም ጋር የሄደው ሎጥም የላም እና የበግ መንጋ ድንኳንም ነበረው፡፡
- የአብራምና የሎጥ የላም፣ የበሬ፣ የበግ መንጋ እጅግ ብዙ ነበረ፡፡ እንስሳቱን በየመስኩ አሠማርተውሉ ለማድረግ ቦታ ጠበባቸው፡፡ በአንድነት ሊቀመጡ ስላልቻሉም የአብራምንና የሎጥን መንጎች በሚጠብቁት መካከልም ጠብ ሆነ፡፡
- አብራምም ሎጥን "እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼ እና በእረኞችህ መካከልም ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ" አለው፡፡ "ምድር ሁሉ በፊትህ አይደለችምን? ከእኔ ትለይ ዘንድ እለምንሃለሁ አንተ ግራውን ብትወስድ እኔ ወደ ቀኝ አንተም ቀኙን ብትወስድ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ፡፡" አለው፡፡
- ሎጥም ዓይኑን አነሣ፤ በዮርዳኖስ ዙርያ ያለውንም አገር ሁሉ ውኃ የሞላበት መሆኑን አየ፡፡ ሎጥም በዮርዳኖስ ዙርያ ያለውን አገር ሁሉ መረጠ ሎጥም ወደ ምሥራቅ ተጓዘ፡፡
- ሎጥ ከተለየው በኂላም እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ በዙርያው ያለውን ምድር ሁሉ እንደሚሰጠው ቃል ገባለት፡፡ "ዘርህንም እንደ ምድር አሸዋ አደርጋለሁ" አለው፡፡ አብራምም በኬብሮን በመምሬ የአድባር ዛፍ ተቀመጠ፤በዚያም ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠራ፡፡

## ማጠቃለያ

- አብራም እና ሎጥ ምድር ብትጠባቸው እና እረኞቻቸው ቢጣሉም እነርሱ አልተጣሉም፡፡
- አብራም ጸብ እንዳይሆን የተጠነቀቀው እግዚአብሔርን እና ወንድሙን የሚወድ ሰው ስለነበረ ነው፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- ከወንድሞቻችን እና ከጓደኞቻችን ጋር በሰላም እንኑር፡፡
- መጫወቻም ሆነ ልብስ ሲገዛ ለእናንተ እንድምትፈልጉ ለወንድሞቻችሁ ለእህቶቻችሁም ቅድሚያ ስጡ፡፡

# አብራም በካህኑ ተባረከ

## ዐሥራ አራተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ:-

- ልጆች፤ ከተማሩት ትምህርት አብራም እንዴት እንደተባረከ ተገንዝበው፤ በካህናት አባቶች መባረክን ይለምዳሉ። መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎችም ይመልሳሉ።

### የሚጠና ጥቅስ:-

*"የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር፤ባረከውም"* ዘፍ. ፲፬ ፥ ፲፰ - ፲፱

### መግቢያ:-

- በዛሬው ትምህርታችን አብራም ሎጥን ከምርኮ ለማዳን መሄዱን እና በካህን መባረኩንም እንማራለን።

### የክለሳ ጥያቄዎች:-

1. የአብራም እና የሎጥ እረኞች ሲጣሉ አብራም ምን አደረገ?

_______________________________________________

2. ሎጥ ከአብራም ተለይቶ ወዴት ሄደ?

www.zeorthodox.org

_______________________________________________

3. አብራም ብቻውን እያለ ምን ተባለ?

_______________________________________________

# ትምህርቱ

- የአሕዛብ ነገሥታት በሁለት ቡድን ሆነው ተዋጉ፤ ሎጥ የሰዶም እና የገሞራ ምድርም ተሸነፉ፤ ያሸነፉዋቸውም ማርከው ንብረታቸውን እና ሰዎችን ወሰዱ፤ ሎጥ እና ከብቱንም ወሰዱ።
- አንድ የሸሸ ሰውም ለአብራም መጥቶ ነገረው። አብራምም ይህን ሲሰማ 318 ብላቴኖች አስከትሎ ሄደ።
- ብላቴኖችንም ለሁለት ከፍሎ በሌሊት ወረደባቸው፣ መታቸውም፣ አሳደዳቸውም። ከብቱንም ሁሉ አስመለሰ፤ ሎጥን እና ከብቶቹን ሴቶቹን እና ሕዝቡንም አስመለሰ።
- በዚህ ጊዜ የተለያዩ የአካባቢው ነገሥታት ተባበሩ፣ አብራምንም ተቀበሉት።
- የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር። ባረከውም፡- “አብራም ሰማይን እና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው። ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው።” አለው። አብራምም ከሁሉ ዐሥራትን ሰጠው።

# ማጠቃለያ

- አብራም ከሎጥ ጋር ቢለያይም በችግሩ ደርሶለታል።
- በእግዚአብሔር ካህን ሲባረክም አብራም ዐሥራት አወጣ።

# ተግባር

- የተኳረፋችሁትን ይቅርታ ጠይቃችሁ ታረቁ፣ ጓደኞቻችሁ ብቻቸውን ሲሆኑም አጫውቱዋቸው።
- በካህናት በመስቀል ሁልጊዜ ተባረኩ።

www.zeorthodox.org

# ኢየሱስ እናቱን ይታዘዛት ነበር

## ዐሥራ አምስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓለማ፡-

- ኢየሱስ እናቱን ያከብራት እና ይታዘዛት እንደነበረ፤ ሕፃናትም እናትና አባታቸውን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን ማክበርና መታዘዝ እንዳለበቸው አውቀው፤ በክፍል ውስጥ መምህሩ የሚሰጡትን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "ይታዘዝላቸውም ነበር።" ሉቃ ፪ ፥ ፶፩

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ሉቃ. ፪ ፥ ፵ - ፶፪፣ ተአምረ ኢየሱስ፣ ዘጸ. ፳ ፥ ፲፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው።
- መምህሩ ተአምረ ኢየሱስ ላይ ኢየሱስ እንዴት እናቱን እንደታዘዘ እና እንደ አገለገላት የሚተርከውን ታሪክ ለሕፃናት ይንገሯቸው።
- ሕፃናት ወላጆቻቸውን እንዴት እንደሚሰሙ እና እንደሚታዘዙ ይጠይቋቸው።

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ኢየሱስ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ እናቱ ማርያም እና ዮሴፍ ሆነው የፋሲካን በዓል ሊያከብሩ ከናዝሬት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። በዚያን ዘመን እስራኤላውያን ፋሲካን እና በዓለ ሃምሳን ሊያከብሩ ከተለያዩ ከተሞች ወደ ኢየሩሳሌም ይመጡ ነበር። እንደዚህ ዘመን በቅርብ ርቀት ቤተ ክርስቲያን ስላልነበረ ከሩቅ ሀገር በግመል፣ በአህያ እና በፈረስ ብዙ ሆነው ሽማግሌዎች፣ አሮጊቶች፣ ጎልማሶች፣ ወጣቶችና ሕፃናት በዓላቱን ለማክበር ተጉዘው ይመጡ ነበር። እንደ ሀገሩ ርቀት እና ቅርበት አንድ ቀን ሁለት ቀን ሦስት ቀን እንዲሁም ሳምንት እና ከዚያም በላይ ይጓዙ ነበር።
- በእስራኤል ባህል ማንኛውንም ጉዞ ሲያደርጉ ወንዶች ከፊት ይቀድማሉ፤ ሴቶች ከኋላ ይሆናሉ። ልጆችም ከልጆች ጋር እየተጫወቱ ረጅሙን ጉዞ ይጓዛሉ። በዚህ የተነሣ

www.zeorthodox.org

እናቶች ልጆቻቸውን እና የቤተሰቡ አባላት መኖራቸውን የሚያረጋግጡት በሚያርፉበት አካባቢ ወይም ሥፍራ ነበር። የኢየሱስ እናት ማርያም ልጇ ከዮሴፍ ጋር ከፊት እየተጓዘ መስሏት ነበር፤ ዮሴፍ ደግሞ ኢየሱስ ከእናቱ ጋር ከኋላ እንደሆነ አስቦ ይጓዝ ነበር። የአንድ ቀን መንገድ እንደተጓዙ እናቱ ማርያም እና ዮሴፍ ኢየሱስን ሲፈልጉት እርሱ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ስለነበር አጡት። ከዘመዶቻቸው እና ከሚያውቋቸው ሰዎች ዘንድ ፈለጉት ነገር ግን አላገኙትም። ስለዚህ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ከሦስት ቀናት በኋላ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውና ሲይጠይቃቸው አገኙት። በመቅደስ የነበሩት መምህራን እንዲሁም የሰሙት ሁሉ በማስተዋሉ እና በመልሱ ይገረሙና ይደነቁ ነበር።

- ብዙ ጊዜ የ0ሥራ ሁለት ዓመት ልጆች በተለያዩ ጨዋታዎች ይመሰጣሉ። ቁም ነገር በሌላቸው ነገሮች ውድ ጊዜያቸውንም ያባክናሉ። ጌታ ኢየሱስ ግን ጊዜውን በትምህርት፣ እናቱን እና ሌሎችን በማገልግል ያሳልፍ ነበር።
- ስለዚህ ሕፃናት ጌታ ኢየሱስ እንዳስተማረን ወላጆቻችንን ልናከብር፣ እንዲሁም ምክራቸውን ልንሰማ እና ጊዜያችንን በመልካም ነገሮች ላይ ልናሳልፍ ይገባል። ጌታ ኢየሱስ እናቱን ይወዳት፣ ያከብራት ይንከባከባት ነበር። እኛም ወላጆቻችንን፣ አኅትና ወንድሞቻችንን እንዲሁም ጓደኞቻችንን በአጠቃላይ ሰውን ሁሉ ልንወድ እና ልናከብር፣ በተቻለን ሁሉ ልናገለግል፣ ልንረዳ ይገባናል ማለት ነው። ይህን ስናደርግ እግዚአብሔር ያሳድገናል፣ በብዙ በረከት ይባርከናል፣ ረጅም ዕድሜና ጤናንም ይሰጠናል።

## ማጠቃለያ፡-

- ሕፃናት፤ ጌታ ኢየሱስ እናቱ ማርያምን እንደታዘዛት እና እንዳገለገላት እናትና አባታችሁን አክብሩ፣ ምክራቸውንም ስሙ፣ ወላጆቻችሁን መታዘዝና ማገልግልን አትርሱ፣ ይህን በማድረጋችሁ ወላጆቻችሁ በጣም ይደሰታሉ፣ እግዚአብሔርም ያሳድጋችኋል፤ ረጅምን ዕድሜና ጤናም ይሰጣችኋል።

www.zeorthodox.org

### ጥያቄዎች፡-

1. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘው ከማን ጋር ነው?
2. ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዙት ለምን ነበር?
3. የኢየሱስ እናት ማርያም እና ዮሴፍ ኢየሱስ አብሮአቸው እንዳልተመለሰ ያወቁት መቼ ነበር?
4. ከስንት ቀን በኋላ አገኙት?
5. ኢየሱስ የተገኘበት ሥፍራ ምን ይባላል?

# ኢየሱስ ተጠመቀ

# ዐሥራ ስድስተኛ ሳምንት

## የትምህርቱ ዓለማ፡-

- ሕፃናት ስለ ጥምቀት ታሪክና ምንነት አውቀው በክፍል ውስጥ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፤ ስለ ጥምቀት የሚያሳይ ሥዕል ይስላሉ፡፡

## በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡፡" ማቴ ፫ ፥ ፲፯

## ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ማቴ. ፫ ፥ ፲፫ - ፲፯፣ ማር. ፩ ፥ ፱ - ፲፩፣ ሉቃ ፫ ፥ ፳፩ - ፳፪፣ እና ዮሐ. ፩ ፥ ፴፪-፴፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- መምህሩ ለሕፃናት ስለ ጥምቀት በዓል እና ሕፃናት ሲጠመቁ የሚያሳይ ሥዕል ወይም ፊልም ያሳዩዋቸው፡፡
- ሕፃናት ክርስትና መቼ እንደተነሡ፣ የክርስትና ስማቸው ማን እንደሆነ፣ ሲጠመቁ የተነሡትን ፎቶ አይተው እንደሚያውቁ እና የክርስትና አባት ወይም እናት እንዳላቸው ይጠይቋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ሰዎችን የንስሓ ጥምቀት በዮርዳኖስ ወንዝ የሚያጠምቅ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበር፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" እያለ ሲሰብክ ብዙ ሰዎች ንስሓ እየገቡ ይጠመቁ ነበር፡፡
- መጥምቁ ዮሐንስም ለሕዝቡ፤ ‹‹እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል፡፡ እርሱ ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ ከእኔም በኋላ ይመጣል፡፡›› እያለ ስለ ኢየሱስ ይነግራቸው ይመሰክርም ነበር፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ

ይህን ሲመሰክር፣ ሕዝቡም ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ የንስሓ ጥምቀት ሲጠመቁ ጌታ ኢየሱስ ወደ ዮሐንስ ሊጠመቅ መጣ፡፡ ያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ የሠላሳ ዓመት ሰው ነበር፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን አጠመቀው፡፡

- ኢየሱስ የተጠመቀው ኃጢአተኛ ስለነበር ሳይሆን ለእኛ ምሳሌ አርአያ ለመሆን ነው፡፡ እኛ በጥምቀት ኃጢአታችን እንደሚሠረይ እና የእግዚአብሔር ልጆች እንደምንሆን ለማስተማር ጌታ ኢየሱስ ተጠመቀ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ ተጠምቆ ከውኃ ውስጥ ሲወጣ ሰማይ ተከፈተ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ሆኖ በራሱ ላይ ተቀመጠ፣ ከሰማይም የአባቱ ድምፅ እንዲህ ሲል ተሰማ፡- "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡፡" በዚህም የሥላሴ አንድነት እና ሦስትነት በክርስቶስ ጥምቀት ተገለጠ፡፡ በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ጥር አሥራ አንድ ቀን የሥላሴ አንድነት እና ሦስትነት የተገለጠበት ስለሆነ የጌታን ጥምቀት በዓል ከዋዜማው ከከተራ ጀምሮ በታላቅ ድምቀትታከብራለች፡፡
- በበዓሉ ዕለት ጠዋት አባቶች ካህናት በውኃው ላይ ጸሎት ካደረጉ በኋላ ሁላችንም እንጠመቃለን፣ ከበዓሉ በረከትም እንሳተፋለን፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ሕፃናት ጌታ ኢየሱስ የተጠመቀው ለእኛ ምሳሌ ለመሆን ነው፡፡ ስለዚህ ሁላችንም በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ብዙ ሰዎችን የንስሓ ጥምቀት ያጠምቅ የነበረ ሰው ማን ነው?
2. ጌታ ኢየሱስ የት እና በማን ተጠመቀ?
3. የጥምቀት በዓል መቼ ይከበራል?
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ምን ተሰማ? ምን ታየ?
5. ሕፃናት እስካሁን ስንት የጥምቀት በዓላትን ከወላጆቻችሁ ጋር አክብራችኋል?

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህሩ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት የሚያሳየውን ሥዕል ሕፃናት ቀለም እንዲቀቡት ያድርጓቸው፡፡
- ሕፃናት የጥምቀትን በዓል እንዴት እንደሚያከብሩ ይጠይቋቸው፡፡

# አሮጊቷ ሣራ ወንድ ልጅ ወለደች

## ዐሥራ ሰባተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት ከአብርሃምና ሣራ ታሪክ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ሲሆን የሚሳነውም ምንም ነገር እንደሌለ ተገንዝበው መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "እግዚአብሔር ሳቅ አድርጎልኛል፡፡" ዘፍጥ. ፳፩ ÷ ፮፡፡

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ዘፍጥ. ፲፰፣ ዘፍጥ. ፳፩፣ ሉቃ ፩ ÷ ፴፯

## መግቢያ

- መምህሩ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አሥራ ስምንት እና ሃያ አንድን ለሕፃናቱ ይተርኩላቸው፡፡
- የሕፃናትን ምስል ያሳዩአቸው እና ሕፃናት ለምን እንደሚያስፈልጉ ይጠይቋቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

- ከዕለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ ያነጋግረው ጀመር፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም በቅርቡ ወንድ ልጅ እንደሚሰጠውም ነገረው፡፡ እግዚአብሔር እና አብርሃም ሲነጋገሩ የአብርሃም ሚስት ሣራ በሌላ ክፍል ውስጥ ሆና ትሰማቸው ነበረ፡፡ በልቧ "ካረጀሁ በኋላ እንዴት ልጅ ልወልድ እችላለሁ?" ብላ አሰበችና በጣም ሳቀች፡፡ እግዚአብሔርም አብርሃምን፤ "ሚስትህ ሣራ ካረጀሁ በኋላ እንዴት እወልዳለሁ? ስትል ለምን ሳቀች? ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" ሲል ጠየቀው፡፡

- በዓመቱ እግዚአብሔር ለሽማግሌው ለአብርሃምና ለሚስቱ ለአሮጊቷ ሣራ ወንድ ልጅ ይስሐቅን ሰጣቸው፡፡ አብርሃምና ሣራም እግዚአብሔር የሚሳነው ምንም ነገር እንደሌለ ሁሉን በጊዜው መሥራትና ማከናወን እንደሚችል በሕይወታቸው ተማሩ፡፡ አብርሃምና ሣራ የመጀመሪያ ልጃቸውን ይስሐቅን ሲወልዱ አብርሃም የመቶ ዓመት ሽማግሌ፣ ሚስቱ ሣራ ደግሞ የዘጠና ዓመት አሮጊት ነበረች፡፡ አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔር ወንድ ልጅ ይስሐቅን ስለሰጣቸው በጣም ደስተኛ ነበሩ፡፡

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት እግዚአብሔር የሚሳነው ምንም ነገር እንደሌለ በዚህ ታሪክ ተምራችኋል፡፡ እግዚአብሔር ለሚታመኑበት ልጆቹ ከዚህም በላይ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በቃሉ የሚነግረንን ማመን አለብን፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. አብርሃም ከማን ጋር ነበር ሲነጋገር የነበረው?
2. የአብርሃም ሚስት ማን ትባላለች?
3. የአብርሃምና የሣራ የመጀመሪያ ልጅ ማን ይባላል?
4. ሣራ ይስሐቅን ስትወልድ የአብርሃም ዕድሜ ስንት ነበር?
5. እግዚአብሔርና አብርሃም ሲነጋገሩ የሳቀችው ሴት ማን ናት? ለምን ሳቀች?

## ተግባር

- መምህሩ ትምህርቱን ካጠቃለሉ በኋላ ለሕፃናቱ ስለ አብርሃምና ሣራ የሚተርክ ቪዲዮ (Video) ፊልም ወይም ምስል (Picture) ያሳዩዋቸው፡፡
- በመጽሐፉ ላይ ያለውን የይስሐቅን ምስል ሕፃናት ቀለም እንዲቀቡ ይንገሩዋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሕፃኑ ሙሴ

## ዐሥራ ስምንተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት ከሙሴ ታሪክ እግዚአብሔር የወደቁትን እንደሚያነሣ እና በእያንዳንዳችን ሕይወት ዓላማ እንዳለው አውቀው፤ መምህሩ ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "እኔ ከውኃ አውጥቼዋለሁና ስትል ስሙን ሙሴ ብላ ጠራችው" ዘጸአ. ፪ ፥ ፲

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ዘጸአ. ፩፥ ፩ - ፳፪፣ ዘፀ. ፪ ፥ ፩ - ፲

### መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው።
- እግዚአብሔር ሰዎችን ለተለያየ አገልግሎት እንደሚመርጥ ለሕፃናቱ ይንገሯቸው።

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ሕፃኑ ሙሴ የተወለደው ግብጽ በሚባል ሀገር ነው። ሙሴ በተወለደበት ዘመን የነበረው የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን በጣም ክፉ እና ጨካኝ ንጉሥ ነበር። ከእስራኤላውያን የሚወለዱ ወንድ ልጆች ሁሉ እንዲገደሉና ወደ ወንዝ እንዲጣሉ ትዕዛዝ አውጥቶ ነበር።
- በዚህ በክፉ ንጉሥ ዘመን ሙሴ ተወለደ። ሙሴ መልከ መልካምና ውብ ስለነበር እናቱ ሦስት ወር ለሰው ሳይታይ በቤት ውስጥ ሸሸገችው። ከዚህ በላይ ልትደብቀው ስላልቻለች ሕፃኑን ሙሴን በቅርጫት ሳጥን ውስጥ አድርጋ ወደ ወንዝ ጣለችው።
- የሕፃኑ ሙሴ እኅት ማርያም ወንዝ ላይ የተጣለውን ወንድሟን እየጠበቀችው እንዳለ የፈርዖን ልጅ ልትታጠብ ወደ ወንዙ መጣች። በወንዙ ላይ የሚንሳፈፍ አንድ ሳጥን ተመለከተችና አገልጋዮቿ እንዲያመጡላት አዘዘች።
- ሳጥኑን ስትከፍተው በጣም ውብ እና ቆንጆ ወንድ ልጅ ተመለከተችና አዘነችለት። ወደ ቤተመንግሥት ወስዳው እንደ ልጇ ታሳድገው ጀመር። በፈርዖን ቤተ መንግሥት ውስጥም እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ነበር።

www.zoorthodox.org

- እግዚአብሔር ሙሴን እስራኤልን ከግብጽ ምድር ነጻ እንዲያወጣቸው እና ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲያገባቸው መረጠው፡፡
- የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ግን ሕዝቡን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልነበረ የእግዚአብሔር ቁጣ በፈርዖን ላይ ነደደ፤ በተለያዩ መቅሰፍቶችም ስለተመታ ሕዝቡን በግድ ለመልቀቅ ተገደደ፡፡
- ሕዝበ እስራኤል በሙሴ መሪነት ከግብጽ የባርነት ኑሮ ነጻ ወጥተው የኤርትራን ባሕር ተሻገሩ፡፡ ፈርዖንና ሠራዊቱም በባሕሩ ውስጥ ሰጠሙ፡፡
- እግዚአብሔር ሕዝቡን በምድረ በዳ አልረሳቸውም ነበር፤ ከሰማይ መና ምግብ አውርዶ ይመግባቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ በምድረ በዳ ዐሠርቱ ቃላትን ሰጠ፡፡

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት እግዚአብሔር በሕፃኑ ሙሴ ሕይወት ውስጥ ዓላማ ስለነበረው በሕፃንነቱ እንደመረጠው፤ እናንተንም ለተለያየ አገልግሎትና መልካም ሥራ መርጧችኋል፡፡
- እግዚአብሔር ሕፃኑ ሙሴን የመረጠው ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዲያወጣ እና የተስፋይቱን ምድር እንዲያወርሳቸው ነበር፡፡ እናንተንም እግዚአብሔር ድሆችን ከድህነት፣ ያልተማሩትን ከድንቁርና እንዲሁም በተለያዩ ሱሶች የተያዙትን ከተያዙበት ሱስ በማላቀቅ መልካም ዜጋ እና ጥሩ ሰው እንዲሆኑ ነጻ አውጪ አድርጎ መርጧችኋል፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ሙሴ የተወለደበት ሀገር ማን ይባላል?
2. እስራኤላውያን የሚወልዷቸው ወንድ ልጆች እንዳያድጉ እና ወደ ወንዝ እንዲጣሉ ትዕዛዝ የሰጠው ንጉሥ ማን ይባላል?
3. የሙሴ እኅት ማን ትባላለች?
4. ለሙሴ ስም ያወጣችለት ሴት ማን ናት?
5. የግብጽ ንጉሥ እስራኤላውያንን አልለቅም ያለበት ምክንያት ምን ነበር?

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህር ሕፃናቱ በመጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ፍቀዱላቸው፡፡

# ያዕቆብ በቤቴል ያየው ሕልም

## ዐሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት የያዕቆብን ታሪክ አውቀው፤ ሰማይ ከምድር ጋር እንዴት እንደሚገናኝ እና ስለ መላእክት በመገንዘብ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፤ መላእክትንም በሥዕል ይሠራሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር" ዘፍ. ፳፰ ፥ ፲፪

### ተጨማሪ ምንባብ፡-

- ዘፍ. ፳፰ ፥ ፲ - ፳፪

### መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት የመላእክትን ምስል አይተው እንደሚያውቁ ይጠይቋቸው፡፡
- ሕፃናት መላእክት ምን ይመስላሉ? መምሰል ምንድን ነው?
- መምህሩ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሃያ ስምንት ላይ ያለውን ታሪክ ለሕፃናቱ ይተርኩላቸው፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ያዕቆብ በአባቱ በይስሐቅ እጅ ከተባረከ በኋላ ከወንድሙ ከዔሳው ፊት ለመሸሽ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን ተጓዘ፡፡ ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ ረጅሙን ጉዞ ከተጓዘ በኋላ ያዕቆብ ደከመው፡፡ ስለመሸበትም ሎዛ በሚባል ስፍራ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ፣ ከባድ እንቅልፍም ወሰደው፡፡
- ያዕቆብ በከባድ እንቅልፍ ውስጥ ሆኖ ሕልም ማየት ጀመረ፡፡ ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ የተዘረጋ መሰላል ተመለከተ፡፡ በመሰላሉም ላይ መላእክት ሲወጡበትና ሲወርዱበት አየ፡፡ እግዚአብሔር በመሰላሉ ጫፍ ላይ ሆኖ ለያዕቆብ ታየውና በብዙ በረከት ባረከው፡፡ ብዙ ልጆች እንደሚሰጠው፣ በሚሄድበት በጉዞው ሁሉ አብሮት እንደሚሆን እና እንደማይለየው ቃል ገባለት፡፡

www.zeorthodox.org

- ያዕቆብም በሕልሙ እጅግ በጣም ተደነቀ፤ ከእንቅልፉ ሲነቃም እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ እንዳለ አስተዋለ። ስለዚህም ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ ዘይት አፈሰሰበት፣ የሥፍራውንም ስም ‹‹ቤቴል፤ የእግዚአብሔር ቤት ይባል›› አለ። ለእግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ቃል ገባ ስለትንም ተሳለ። "እግዚአብሔር ከያዕቆብ ጋር ቢሆን፣ በሚሄድበትም መንገድ ቢጠብቀው፣ የሚበላውን እንጀራ የሚለብሰውንም ልብስ ቢሰጠው እና ወደ አባቱ ቤት በሰላም እና በጤና ቢመልሰው እግዚአብሔር አምላኩ ይሆንለታል፤ ለያዕቆብም ከሚሰጠው ሁሉ ለእግዚአብሔር ከዐሥር አንዱ እጅ ይሆናል" አለ።

## ማጠቃለያ፡-

- እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዲያገናኙ መላእክቱን ይልካል። መላእክት በምንጓዝበት መንገድና ጉዞ ሁሉ ይረዱናል፤ ይጠብቁናልም። መላእክት እግዚአብሔር አድርጉ ብሎ የነገራቸውንና ያዘዛቸውን ሁሉ የሚያደርጉ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው።

## ጥያቄዎች፡-

1. ያዕቆብ የማን ልጅ ነው?
2. የያዕቆብ ወንድም ማን ይበላል?
3. ያዕቆብ የተጓዘው ከየት ተነሥቶ ወደየት ነበር?
4. ያዕቆብ ሕልም ያየበት ሥራፍ ማን ይባላል?
5. የያዕቆብ ሕልም ምን ነበር?
6. ያዕቆብ ሕልሙን ካየ በኋላ ምን አደረገ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ለሕፃናቱ የመላእክትን ምስል ያሳዩዋቸው።
- በመጽሐፉ ላይ ያለውን የመላእክት ምስል ሕፃናቱ ቀለም እንዲቀቡ ይንገሯቸው።
- ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል፣ ቅዱስ ዑራኤል የሚባሉ የመላእክት ስሞችን ለሕፃናቱ ያስጠኑዋቸው።

www.zeorthodox.org

# ይስሐቅ እና ርብቃ

## ሃያኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ሕፃናት፤ ከይስሐቅ እና ከርብቃ የሕይወት ታሪክ እግዚአብሔር በማንኛውም ውሳኔያችን እንደሚመራን አውቀው መምህሩ ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፤ ሥዕል ይሠራሉ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- "ስለ ስምህ መንገዴን አቅና፤ ምራኝም።" መዝ. ፳ (፳፪) ፥ ፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ ፳፬ ፥ ፩ - ፷፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ለሕፃናቱ ይከልሱላቸው።
- ሕፃናቱ ስለ ሰርግ ወይም ስለ ጋብቻ የሚያውቁት ነገር እንዳለ ይጠይቃቸው።
- ጋብቻ አንድ ወንድ እና ሴት ቤተሰብ ለመመሥረት ፈቃኛ ሲሆኑ የሚጣመሩበት ሥርዓት እንደሆነ ይግለጹላቸው።
- የአብርሃም ታማኝ አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት የምትሆነውን ሴት ለማግኘት የእግዚአብሔርን እርዳታ እና ምሪት በጸሎት እንደጠየቀ አጽንዖት ሰጥተው ለሕፃናቱ ያስተምሯቸው።

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

- ይስሐቅ ዕድሜው ለጋብቻ በደረሰ ጊዜ አባቱ አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት ሊፈልግለት ተነሣ። በጣም የሚወደውን ታማኝ አገልጋዩን ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት እንዲፈልግለት ትዕዛዝ ሰጠው። አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት ትሆነው ዘንድ የመረጣት ሴት እግዚአብሔርን የምትወድ፣ ለሕጉም የምትታዘዝና የምትገዛ መልካም ሴት መሆን ነበረባት። የአብርሃም ታማኝ አገልጋይ ጌታው አብርሃም የሰጠው አደራ እና ኃላፊነት ከባድ እንደሆነ እያሰበ ይጨነቅ ነበር። "አይዞህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል በምንም ነገር አትጨነቅ።" ሲል አብርሃም አገልጋዩን አጽናናው። ከዚህ በኋላ አገልጋዩ ለጉዞው የሚሆኑ ቁሳቁሶችን እና ግመሎችን አዘጋጀ።

- ለይስሐቅ ሚስት የሚሆኑ ውድ ጌጣጌጦችንና ስጦታዎችንም ይዞ ጉዞውን ጀመረ፡፡ ብዙ ከተጓዘ በኋላ በጣም ውኃ ተጠማ፡፡ በዚህ የተነሣ ከግመሉ ላይ ወርዶ የሚጠጣውን ውኃ ይፈልግ ጀመር፡፡ የአብርሃም አምላክ በመንገዱ እንዲመራውና ጉዞውን እንዲያቀናለት ጸሎቱን አድርጎ እንደጨረሰ በጣም ቆንጆ ወጣት ሴት ወደ አገልጋዩ መጣች፡፡ በጣም መልካምና ጥሩ ሴትም ስለነበረች የአብርሃም አገልጋይ ውሃ እንደጠማው መጠጣትም እንደሚፈልግ አውቃ "ውኃ ላምጣልህን?" ስትል ጠየቀችው፡፡ ግመሎቹንም ውኃ ልታጠጣለት ፈቃደኛ እንደሆነች ገለጸችለት፡፡
- የአብርሃም አገልጋይ የሴቲቱን መልካምነት እና የልቧን ቅንነት በተመለከተ ጊዜ እግዚአብሔር መንገዱን እንዳቀናለት ለይስሐቅም ሚስት እንድትሆን የመረጣት ሴት እርሷ እንደሆነች ተረዳ፡፡ እግዚአብሔርንም በጸሎት አመሰገነ፡፡ ከዚህ በኋላ ርብቃን የማን ልጅ እንደሆነች ጠየቃት፡፡ እርሷም ለአገልጋዩ አባቷ የአብርሃም ዘመድ እንደሆነ ነግራው ወደ አባቷ ወደ ላባ ወሰደችው፡፡ ለአባቷም የሆነውን ነገር ሁሉ ነገረችው፡፡ የርብቃ አባት ላባ ለአብርሃም ልጅ ለይስሐቅ መልካም ሚስት ሊፈልግ አገልጋዩ ከሩቅ እንደመጣ አወቀ፡፡ እግዚአብሔርም ርብቃን እንዳሳየው ሲሰማ ርብቃ የይስሐቅ ሚስት እንድትሆን ፈቀደለት፡፡ የአብርሃም አገልጋይም እግዚአብሔርን ካመሰገነ በኋላ ይዞ የመጣውን ውድ ጌጣጌጥ ለርብቃ ሰጠ፡፡ በማግስቱም ርብቃ ከአገልጋዩ ጋር ሆና ባሏ ይስሐቅን ለማግኘት ጉዞ ጀመረች፡፡ ይስሐቅም ርብቃን እንዳገኘ እግዚአብሔር መልካም ሚስት እንደመረጠለት እና እንደሰጠው አወቀ፡፡ ርብቃ እጅግ በጣም ጥሩ ሴት እግዚአብሔርንም የምታውቅ እና የምትፈራ ነበረች፡፡ ይስሐቅና ርብቃ በጣም ተዋደዱ፤ በሕይወታቸውም በጣም ደስተኞች ሆኑ፡፡

## ማጠቃለያ www.zeorthodox.org

- ሕፃናት እግዚአብሔር የሁላችንም አባት ስለሆነ በሥራችን፣ በመንገዳችን እና በጉዞአችን ሁሉ አይለየንም፡፡ ስለዚህ ከማንኛውም ነገር መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ፣ ምርጫና ምሕረት በጸሎት መጠየቅ አለብን፡፡ እግዚአብሔር በሕይወታችን ትክክለኛውን ነገር እንድንመርጥ እና እንድናደርግ መሪያችን ነው፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ለይስሐቅ ሚስት የፈለገለት ሰው ማን ነበር?

2. አገልጋዩ ሲጨነቅ ማን አጽናናው?
3. አገልጋዩ የማንን እርዳታ በጸሎት ጠየቀ?
4. የይስሐቅ ሚስት ማን ትባላለች? የማን ልጅ ነበረች?
5. የአብርሃም አገልጋይ ለጉዞው ምን አዘጋጀ?
6. የርብቃ አባት ማን ይባላል?

## ተግባር

- በትምህርቱ ማጠቃለያ ሕፃናት እንዲጸልዩ በተለያዩ ጊዜያት ጸሎት እንደሚደረግ መምህሩ ይንገሩዋቸው።
- ሕፃናት የይስሐቅን፣ የርብቃን፣ የአገልጋዩን እና የግመሎቹን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ይንገሩዋቸው።

www.zeorthodox.org

# ርብቃ መንታ ልጆችን ወለደች

## ሃያ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ሕፃናት የያዕቆብና የዔሳውን ታሪክ አውቀው ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- “እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ” ቆላ. ፫ ፥ ፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**

- ዘፍ ፳፭ ፥ ፳፭ - ፴፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት መንታ ልጆችን ዓይታችሁ ታውቃላችሁ?
- መምህር መንትዮች ምን እንደሆኑ? ምን እንደሚያመሳስላቸው? እና እንደሚለያያቸው? ለሕፃናቱ ይግለጹላቸው፡፡
- ልጆች በጣም ተርባችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ ምን አደረጋችሁ?
- ታሪኩ የበለጠ ለሕፃናቱ ግልጽ እንዲሆንና እንዲረዱት እንደ ዔሳው የፀጉራም ሰው እንደ ያዕቆብ ደግሞ ፀጉር የሌለው ሰው ምስል አሳዩዋቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zoorthodox.org

- ይስሐቅና ርብቃ ለብዙ ዘመናት ልጅ አልነበራቸውም፡፡ ከብዙ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ለርብቃ ልጆችን ሰጣት፡፡ ዔሳው እና ያዕቆብንም ወለደች፡፡ ዔሳውና ያዕቆብ መንትዮች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ዔሳው ቀድሞ ከርብቃ ማሕፀን ስለወጣ እና ስለተወለደ እንደ ታላቅ ልጅ ይቆጠር ነበር፡፡
- ምንም እንኳን ዔሳውና ያዕቆብ መንትዮች ቢሆኑም በብዙ ነገሮች የተለያዩ ነበሩ፡፡ ዔሳው አዳኝ ስለሆነ ብዙ ጊዜ እቤት አይውልም ነበር፤ ያዕቆብ ግን ብዙ ጊዜ እቤት ውስጥ ከእናቱ ጋር ያሳልፍ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዔሳው አደን ሊያድን ወጣ፡፡
- ነገር ግን ምንም አላገኘም ነበር፡፡ ስለዚህ በጣም ደክሞት እና ተርቦ ወደ ቤት ተመለሰ፡፡ እቤት ሲደርስ ያዕቆብ የምስር ወጥ እየሠራ ነበር፡፡

- ዔሳው የምግቡ ሽታ ረሃቡን አባባሰበት እና ለመብላት እጅግ ተመኘ፡፡ ስለዚህ ዔሳው ለወንድሙ ለያዕቆብ በጣም እንደራበው ገልጾ ምግብ እንዲሰጠው ለመነው፡፡
- ያዕቆብ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ዔሳው ብኵርናውን በምስር ወጥ እንዲለውጠው ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት፡፡ ዔሳው ረሃቡ ስለጸናበት፤ ‹‹እሺ አንተ ታላቅ የመጀመሪያ ልጅ ተባል፤ ለእኔ ግን እባክህን ሳልሞት ምግብ ስጠኝ›› አለው፡፡ ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ለዔሳው የሚበላውን ምግብ ሰጠው፣ ያዕቆብም የዔሳውን ብኵርና ወስዶ የመጀመሪያ ልጅ ተባለ፡፡
- ዔሳው እስኪጠግብ ድረስ ከበላ በኋላ በረታ፤ ነገር ግን ከዚህ በኋላ በኵር ወይም የመጀመሪያ ልጅ መሆን አልቻለም፡፡

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት እግዚአብሔር እንደ ዔሳው በረከትን ሲሰጠን በምስር ወጥ ልንለውጠው አይገባም፡፡ እግዚአብሔር የሚሰጠንን በረከት አክብረን ልንይዘውና ልንጠብቀው ይገባል፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ርብቃ ስንት ልጆች ወለደች? ስማቸው ማን ይባላል?
2. ከያዕቆብና ከዔሳው ታላቅ ማን ነበር? እንዴት?
3. ያዕቆብና ዔሳው ልዩነታቸው በምን ነበር?
4. የዔሳው ሥራ ምን ነበር? የያዕቆብስ?
5. ዔሳው ብኵርናውን እንዴት አጣ?

## ተግባር

- ሕፃናቱ የዔሳውንና የያዕቆብን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ይንገሩዋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም ተረጎመ

## ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ልጆች ከትምህርቱ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንደነበር አውቀው መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ግጥም፡-**

- "እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፡፡" ዘፍ. ፴፱ ፥ ፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**

- ዘፍ. ፵፩ ፥ ፩ - ፶፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናቱን ስለ ሕልም የሚያውቁት ነገር ካለ ይጠይቁዋቸው?
- ሕፃናት ከመካከላችሁ ሕልም አይቶ የሚያውቅ አለ?
- ለማስተማር የሚረዱ የሰባት ወፍራም ላሞች እና የሰባት ቀጭን ላሞች ሥዕል ይዘጋጅ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

- ከዕለታት አንድ ቀን የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ሕልም አየ፡፡ በሕልሙ መልካቸው ያማረ ሥጋቸውም የወፈረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ሲወጡ፣ በወንዙ ዳር በመስኩ ሲሰማሩ፤ ቀጥሎም መልካቸው የከፋ ሥጋቸውም የከሳ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዝ ውስጥ ወጥተው መልካቸው ያማረውን ሥጋቸው የወፈረውን ሰባቱን ላሞች ሲውጡአቸው አየ፡፡
- ፈርዖን ባየው ሕልም እጅግ በጣም ተገረመ፤ የሕልሙ ፍቺም ምን እንደሆነ አላወቀም ነበርና፡፡ በሚቀጥለው ቀንም ንጉሡ ሕልም አየ፡፡ በሕልሙ በአንድ አገዳ ላይ የነበሩ ያማሩና መልካም የሆኑ ሰባት እሸቶች ወጡ፤ ከእነርሱ ቀጥሎ ደግሞ የደረቁ እና በንፋስ የተመቱ ሰባት እሸቶች ወጡ፡፡
- የደረቁትና በነፋስ የተመቱት ሰባት እሸቶች ሰባቱን ያማሩና የዳበሩ እሸቶች

www.zeorthodox.org

ዋጡአቸው፡፡ ንጉሡ ባያቸው ሁለት ሕልሞች በጣም ተረበሸ፤ የሕልሙንም ፍቺ ገና አልተረዳም ነበር፡፡

- ንጉሡም የሕልሙን ፍቺ እንዲነግሩት የግብጽ ጠቢባንን እና ሕልም ተርጓሚዎችንም ሁሉ አስጠራ፤ ሕልሙንም ነገራቸው፡፡ ነገር ግን ከመካከላቸው ለፈርዖን ሕልሙን የሚፈታ እና የሚተረጉም አልተገኘም ነበር፡፡
- እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበር ሕልም የመፍታት ጥበብን ሰጥቶት ነበር፡፡ ዮሴፍ እንዲህ ሲል የፈርዖንን ሕልም ፈታ፡፡ ሰባት ዓመታት የጥጋብ ጊዜያት ይሆናሉ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ሰባት ዓመታት የራብ ዘመናት ይሆናሉ፡፡ ንጉሡ የሕልሙን ፍቺ ካወቀ በኋላ በጣም ተጨነቀ፤ ምን ማድረግ እንዳለበትም ዮሴፍን ምክር ጠየቀ፡፡ ዮሴፍም በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ምግብ እንዲቆጥቡ እና ለረኃቡ ዘመን እንዲያከማቹ ፈርዖንን እና የግብጽ ገዢዎችን መከራቸው፡፡ ንጉዉ ወይም ፈርዖኑ በዮሴፍ ምክር በጣም ተደሰተ፡፡ ከዚያም ዮሴፍን ከንጉሡ (ከእሱ) ቀጥሎ በግብጽ ሁለተኛ ሰው አድርጎ ሾመው፡፡ ዮሴፍ ግብጻውያን በጥጋብ ዓመታት ምግብ እንዲቆጥቡ እና ለሚመጣው የራብ ዘመን እንዲያከማቹ እረዳቸው፡፡ የዮሴፍ እቅድና ምክር እውነት ነበር፤ ከሰባቱ የጥጋብ ዓመታት በኋላ በሀገሪቱ ሁሉ ድርቅ ሆነ፡፡ ግብጻውያን ተራቡ፤ ወደ ንጉሡ መጥተው ጮሁ፤ ንጉሡም ዮሴፍን እንዲጠይቁ ነገራቸው፡፡ ዮሴፍም በሰባቱ የጥጋብ ዘመን የተከማቸውን ምግብ እየቆጠበ ይሰጣቸው ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ ንጉሡ እና ግብጻውያንም ምስጋናቸውን ያለማቋረጥ ለዮሴፍ ያቀርቡና ያከብሩትም ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንደነበር ዛሬም ከእናንተ ጋር ነው፡፡
- እግዚአብሔር በሰጠን ዕውቀትና ጥበብ ራሳችንን እና ሌሎችንም ልንረዳበት ይገባል፡፡

**ጥያቄዎች፡-** www.zeorthodox.org

1. ሕልም ያያው የግብጽ ንጉሥ ማን ይባላል?
2. የንጉሡ ሕልም ምን ነበር?
3. የፈርዖንን ሕልም የተረጎመለት ሰው ማን ይባላል?
4. ሕልሙን የፈታው ሰው ምን ሆነ?
5. ለዮሴፍ ሕልም የመፍታት ጥበብን የሰጠው ማን ነው?

## ተግባር

- መምህር ሕፃናቱ በሥዕል መጽሐፉ ላይ ያለውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ፍቀዱላቸው፡፡

# የጥበብ ሰዎች

## ሃያ ሦስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት ስለ ሰብዓ ሰገል (የጥበብ ሰዎች) ሕፃኑ ኢየሱስን ለማየት ስላደረጉት ጉዞ፣ ስለሰጡት ገጸ በረከት እና ስለ ደስታቸው ከትምህርቱ ተገንዝበው በመምህሩ የሚቀርቡ ላቸውን ጥያቄዎች ይመልሱ።

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን።" ዮሐ. ፲፪ ፥ ፳፩

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ማቴ. ፪ ፥ ፩ - ፲፪፣ ሉቃ. ፪ ፥ ፩ - ፲፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ትምህርት ይከልሱላቸው።

## የሳምንቱ ትምህርት

- በንጉሥ ሄሮድስ ዘመን በይሁዳ ቤተልሔም ኢየሱስ ተወለደ።
- የተወለደውን ሕፃን ኢየሱስን ለማየት ሰብዓ ሰገል (የጥበብ ሰዎች) በኮከብ እየተመሩ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። በዚያን ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ ነበር።

www.zeorthodox.org

- የጥበብ ሰዎች ንጉሡ ሄሮድስን "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ ዓይተን ልንሰግድለት መጥተናል" አሉት። ይህን ዜና ሲሰማ ንጉሥ ሄሮድስ በጣም ደነገጠ።
- የጥበብ ሰዎች የጠየቁት ጥያቄ ከባድ እና በእርሱ የሚመለስ ስላልነበረ፤ ንጉሡ ሄሮድስ የካህናት አለቆችን እና የሃይማኖት አባቶችን ወደ ቤተ መንግሥቱ ጠራቸው እና ሰበሰባቸው። ከዚያም የጥበብ ሰዎችን ይህን ጥያቄ እንዲመልሱ አዘዛቸው። እነርሱም ክርስቶስ በቤተልሔም እንደሚወለድ ተናገሩ።
- ከዚህ በኋላ የጥበብ ሰዎች በኮከቡ እየተመሩ ከኢየሩሳሌም ወደ ቤተልሔም ተጓዙ።

በምሥራቅ ያዩት ኮከብ የጥበብ ሰዎችን ሕፃኑ ኢየሱስ የተወለደበት ሥፍራ ድረስ መራቸው፡፡

- ወደ ተወለደበትም ቦታ ገብተው ሕፃኑ ኢየሱስን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፤ ወድቀውም ሰገዱለት፤ ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው ለሕፃኑ ኢየሱስ ይዘው የመጡትን ወርቅ፣ ዕጣን እና ከርቤ ስጦታ አድርገው ሰጡት፡፡ በሆነው ነገር ሁሉ እጅግ ደስ አላቸው፣ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ሀገራቸው ሄዱ፡፡

## ማጠቃለያ

- የጥበብ ሰዎች ከሩቅ ሀገር ውድ ስጦታ ይዘው በኮከብ እየተመሩ ሕፃኑ ኢየሱስን ለማየት ሄደዋል፡፡
- ኢየሱስን ከእናቱ ከማርያም ጋር ባገኙት ጊዜ በጣም ተደሰቱ፡፡
- ሕፃናት እናንተም በክርስቶስ ልደት ደስተኛ ሆናችሁ የገናን በዓል ከቤተሰባችሁ ጋር አክብሩ፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. የጥበብ ሰዎች ጥያቄ ምን ነበር?
2. ኢየሱስ በተወለደበት ዘመን በኢየሩሳሌም የነበረው ንጉሥ ማን ይባላል?
3. ኢየሱስ የተወለደበት ቦታ ምን ይባላል?
4. የጥበብ ሰዎች ሕፃኑ ኢየሱስን ከማን ጋር አገኙት?
5. የጥበብ ሰዎች ለሕፃኑ ኢየሱስ ያመጡት ስጦታ ምን ነበር?

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ የጥበብ ሰዎች በኮከብ እየተመሩ ሕፃኑ ኢየሱስን ለማየት ከምሥራቅ ሀገር ሲመጡ የሚያሳይ ሥዕል ለሕፃናቱ ያሳዩዋቸው፡፡
- በመጽሐፍ ላይ ያለውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡
- ሕፃናት የልደት መዝሙር እንዲዘምሩ ጋብዙዋቸው፡፡

# ወደ ግብጽ ሽሹ

## ሃያ አራተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ:-

- ሕፃናት፤ ዮሴፍ ሕፃኑን ኢየሱስንና እናቱ ማርያምን ይዞ ወደ ግብጽ የሸሹበትን ታሪክና ምክንያት ተገንዝበው፤ ከክፉ ሐሳብ እና ተግባር መሸሽ እንደሚገባ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

### በቃል የሚጠና ጥቅስ:-

- "ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ" ማቴ. ፪ ፥ ፲፫

### ተጨማሪ ምንባብ:-

- ማቴ. ፪ ፥ ፩ - ፳፫

### መግቢያ:-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው።
- መምህሩ ለሕፃናት ግብጽ የምትገኝበትን ከካርታ ላይ ያሳዩቸው።
- ለሕፃናቱ ስለ ስደት እና ሰዎች የሚሰደዱባቸውን የተለያዩ ምክንያቶች ይግለጹላቸው።

## የሳምንቱ ትምህርት:-

- ሕፃናት፤ ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ኢየሱስ በንጉሥ ሄሮድስ ዘመን በቤተልሔም ይሁዳ መወለዱን ከምሥራቅ በኮከብ እየተመሩ የመጡ ሦስት የጥበብ ሰዎች ስጦታ እንዳመጡለት እና በክርስቶስ ልደት እየተደሰቱ ወደ ሀገራቸው እንደተመለሱ ተምረን ነበር።
www.zeorthodox.org
- የጥበብ ሰዎች ሕፃኑ ኢየሱስን ከእናቱ ከማርያም ጋር አይተው ሲደሰቱ ንጉሡ ሄሮድስ ግን ደስተኛ አልነበረም። በዚህ ምክንያት ንጉሥ ሄሮድስ ሕፃኑ ኢየሱስን ሊገድለው ፈለገ። በቤተልሔም የተወለዱ ሁለት ዓመት የሆናቸውን እና ከዚያም በታች የሆኑትን ሕፃናት ሁሉ እንዲገደሉ አዘዘ።
- ብዙ ሕፃናትም ተገደሉ፤ እናቶች ልጆቻቸውን በግፍ ስለገደሉባቸው አለቀሱ፤ አዘኑ።
- ነገር ግን ሄሮድስ ይህን ሐሳብ ሲያስብ የእግዚአብሔር መልአክም ለዮሴፍ በሕልም ተገልጾለት፤ ሕፃኑን እና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ እንዲሸሽ ነገረው። ዮሴፍም

የእግዚአብሔር መልአክ እንደነገረው ሕፃኑ ኢየሱስንና እናቱ ማርያምን ይዞ ወደ ግብጽ ሀገር ሸሸ፡፡ የሕፃኑን ነፍስ የሚፈልገው ንጉሥ ሄሮድስ እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ፡፡

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት ንጉሥ ሄሮድስ ክፉ ሰው እንደነበረ፤ ሐሳቡ እና ተግባሩ ክፉ እንደሆነ በትምህርቱ አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ ከክፉ ሰዎች፣ ከክፉ ሐሳብ እና ተግባር መራቅ እና መሸሽ አለባችሁ፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ሕፃኑ ኢየሱስን ሊገድለው ይፈልግ የነበረ ሰው ማን ነው?
2. ንጉሥ ሄሮድስ ለምንድን ነው ሕፃናትን ያስገደለው?
3. ሄሮድስ የሕፃኑን ነፍስ ሊገድል እንደሚፈልግ ለዮሴፍ ማን ነገረው?
4. ግብጽ የት ትገኛለች?
5. ዮሴፍ ማንን ይዞ ወደ ግብጽ ሀገር ሸሸ?

www.zeorthodox.org

# ያዕቆብ እና ዔሳው ታረቁ

## ሃያ አምስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት የዓሳውንና የያዕቆብን ታሪክ ተገንዝበው፤ በወንድማማቾች መካከል መጣላት ቢኖርም መታረቅ እና በሰላም መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚቀር ቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "ይቅር ተባባሉ፡፡" ቆላ. ፫÷፲፫

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ቆላስይስ ፫ ÷ ፲፪-፲፯፣ ማር. ፲፩ ÷ ፳፭-፳፮፣ ዘፍ. ፴፪ - ፴፫ እና ዘፍ. ፳፯ ÷ ፴፮-፵፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናትን ጥል ምን እንደሆነ እና ከማን ጋር ተጣልተው እንደሚያውቁ ይጠይቁዋቸው፡፡
- ሕፃናት ከተጣሉት ወንድም፣ እኅት ወይም ጓደኛ ጋር እንዴት እንደሚታረቁ ይጠይቁዋው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

- ሕፃናት ታስታውሱ እንደሆነ ከዚህ ቀደም በነበረን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ጥናት ርብቃ ለይስሐቅ መንታ ልጆችን እንደወለደችለት፣ ዔሳው ከማሕፀን ቀድሞ ስለወጣ በኵር ወይም የመጀመሪያ ልጅ እንደተባለ ተምረናል፡፡ የዔሳውን ተረከዝ ይዞ የተወለደው ደግሞ ያዕቆብ እንደ ተባለ፣ ያዕቆብ የታላቁን የዔሳውን ብኵርና በምስር ወጥ እንደገዛ እና አባቱን በማታለል በረከትን እንዳገኘ ተምረን ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

- ያዕቆብ ወንድሙን ዔሳውን ሁለት ጊዜ ስላታለለው ዔሳው በያዕቆብ ቂም ይዞበት ሊገድለው ይፈልግ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ያዕቆብ ከዔሳው ለማምለጥ እንዲሁም ሚስት ለማግኘት ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ዘንድ ሄደ፡፡ አጎቱ ላባን ሃያ ዓመት አገልግሎ ልያንና ራሔልን አገባ፤ ብዙ ልጆችንም ወለደ፤ በብዙ ከብቶችና ሀብት ተባረከ፡፡ እግዚአብሔር ወደ ከነዓን እንዲመለስ ባዘዘው ጊዜ ያዕቆብን ሁለት ነገሮች አስጨነቁት፡፡

- ከአጎቱ ላባ መለየትና ወደ ተጣላው እና ሊገድለው ወደሚፈልገው ወንድሙ መመለስ ፈለገ፡፡ እግዚአብሔርም ከላባ እና ከዔሳው ቁጣ ያዕቆብን ጠበቀው፡፡ ከአጎቱ ላባ ጋር በሰላም ከተለያየ በኋላ ወደ ወንድሙ ለመሄድ ጉዞ ጀመረ፡፡ በጉዞውም እግዚአብሔር በዳን እና በቤተልሔም ተገለጠለት፡፡ ስሙንም "እስራኤል" ብሎ ጠራው፡፡ በብዙ በረከት እግዚአብሔር ያዕቆብን ባረከው፣ የአብርሃምንም ተስፋ ሰጠው፡፡ ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ለወንድሙ ዔሳው የሚሆን ስጦታ አዘጋጀና በአገልጋዮቹ አስቀድሞ ላከለት፡፡ እርሱም ቤተሰቡን ይዞ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ለአገልጋዮቹ ያዕቆብ እንዲህ አላቸው፡- "ወንድሜን ዔሳውን በመንገድ ያገኛችሁት እንደሆነ በፊቴ በሚሄደው እጅ መንሻ እታረቅሃለሁ በሉት፤ ከዚያም በኋላ ወንድሜ ዔሳው ይራራልኛል፤ ፊቱንም እንዳይ ይፈቅድልኛል፡፡" ብሎ በእምነት እና በተስፋ ወደ ዔሳው ላካቸው፡፡ ዔሳው ወንድሙ ያዕቆብን ሊያገኘው ሮጠ፡፡ አንገቱንም አቅፎ ሳመው፣ በጣም ተነፋፍቀው ስለነበር ተላቀሱ፡፡ ሁለቱ ወንድማማቾች ከነቤተሰባቸው ታረቁ፣ በመካከላቸውም ሰላም ሆነ፡፡

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት በዚህ ታሪክ ያዕቆብ ወንድሙን ዔሳውን ማታለሉ ምን ያህል እንደጎዳው እና ለመጣላታቸው ምክንያት እንደሆነ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከጓደኞቻችሁ እንዲሁም ከመምህሮቻችሁ ጋር እንዳትጣሉ ከፈለጋችሁ ማንንም አታታልሉ፣ አትዋሹ፣ ክፉ ቃል እና ስድብን አትናገሩ፡፡ ስታጠፉም ስሕተታችሁን አምናችሁ ይቅርታ ጠይቁ፣ ታረቁ፡፡ የዚህን ጊዜ በመካከላችሁ ሰላም ይሆናል፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ያዕቆብ ወንድሙን ዔሳውን ስንት ጊዜ አታለለው?
2. ያዕቆብ ወደ አጎቱ ላባ የሔደው ለምን ነበር?
3. ያዕቆብ ስንት ሚስት ነበረው? ስማቸው ማን ማን ይባላል?
4. ያዕቆብ በላባ ቤት ስንት ዓመት ኖረ?
5. ያዕቆብ ከወንድሙ ጋር እንዴት ታረቀ?

www.zoorthodox.org

### ተግባር

- መምህሩ ለሕፃናት የጥል መንሥኤዎችን እና መታረቅ የሚያስፈልገበትን ምክንያት በምሳሌ በተደገፈ ገለጻ ያስረዱአቸው፡፡
- ሕፃናት በመጽሐፉ ላይ ያለውን የያዕቆብን እና የዔሳውን እንዲሁም የቤተሰቦቻቸውን ምስል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡

# ታዛዡ ይስሐቅ

## ሃያ ስድስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት፤ ከይስሐቅ ሕይወት እግዚአብሔርን እና ወላጆችን እንዴት ማክበርና መታዘዝ እንዳለባቸው ያውቃሉ፤ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "አባትህንና እናትን አክብር" ዘጸ. ፳ ፥ ፲፪

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ዘፍ. ፲፰ ፥ ፩-፲፫፣ ዘፍ ፳፩ ፥ ፩-፯፣ ዕብ. ፲፩ ፥ ፱-፳፣ እና ሮሜ. ፬ ፥ ፲፯-፳፫

### መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት ለወላጆቻችሁ ትታዘዛላችሁ?
- ሕፃናት በቤት ውስጥ እንዲሁም በትምህርት ቤት ለማን እና እንዴት እንደሚታዘዙ መምህሩ ይጠይቁዋቸው፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

- አብርሃምና ሣራ ለብዙ ዘመናት በጋብቻ አብረው ቢኖሩም ልጅ አልነበራቸውም፡፡ ይህን ጉድለታቸውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጣቸው ቃል ስለገባላቸው አብርሃምና ሣራ በእምነትና በተስፋ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ልጅ ይጠብቁ ጀመር፡፡
- ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር አብርሃምንና ሣራን አሰበ፤ እግዚአብሔር እንደተናገረውም አደረገላቸው፡፡ በእርጅና ዘመናቸው እግዚአብሔር ይስሐቅን ስለሰጣቸው በጣም ደስ አላቸው፡፡ ይስሐቅ ማለት ይስቃል ማለት ነው፡፡
- ስሙን ያወጣችለት እናቱ ሣራ ናት፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ሳቅ አድርጎልናል፤ በእርጅና ዘመኔ ልጅ መውለዴን የሚሰማ ሁሉ በእኔ ምክንያት ይስቃል›› ስትል፤ እግዚአብሔር የሰጣትን ልጅ ይስሐቅ አለችው፡፡ አብርሃም ወንድ ልጁን ይስሐቅን በተወለደ በስምንተኛው ቀን እግዚአብሔር እንዳዘዘው ገረዘው፡፡
- ይስሐቅ አባቱን እና እናቱን እያከበረ፣ እየታዘዘ እና እያገለገለ አደገ፡፡

www.zeorthodox.org

- ገና ከሕፃንነቱ ጀምሮ እግዚአብሔርን መፍራት ከወላጆቹ ያውቅ ስለነበር ይስሐቅ እግዚአብሔርን ይወድና ይታዘዝ ነበር፡፡ በዚህም አባቱ አብርሃምና እናቱ ሣራ በይስሐቅ በጣም ደስተኞች ነበሩ፡፡
- ጎበዝ፣ አማኝ፣ ታዛዥ፣ ቅን እና መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ልጅ ስለሰጣቸው ሁል ጊዜ እግዚአብሔር ያመሰግኑ፤ ይስሐቅንም ይመርቁት ይባርኩት ነበር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ሕፃናት ይስሐቅ ታዛዥ በመሆኑ በወላጆቹ እና በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ልጅ እንደነበር ተምራችኋል፡፡ እናንተም እናትና አባታችሁን፣ ታላላቆቻችሁን በአጠቃላይ ሰውን ሁሉ ማክበርን ተማሩ፡፡
- ቅኖች፣ ታማኞች እና ታዛዦች ሁኑ፡፡ ይህን በማድረጋችሁ በስውር በእግዚአብሔር ፊት የተወደዳችሁ ትሆናላችሁ፣ የእግዚአብሔርም ጸጋ እና በረከት ይበዛላችኋል፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ይስሐቅ የማን ልጅ ነው?
2. ይስሐቅ የስሙ ትርጉም ምን ማለት ነው?
3. ለይስሐቅ ስም ያወጣለት ማን ነበር?
4. ይስሐቅ ምን ዓይነት ልጅ ነበር?
5. ከይስሐቅ ሕይወት ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ሕፃናት በመጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ይንገሩዋቸው፡፡
- ሕፃናት በቤት እና ከቤት ውጪ እንዴት እንደሚታዘዙ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ያድርጓቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ይስሐቅ ክፉውን በበጎ አሸነፈ

## ሃያ ሰባተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት ክፉ ነገሮችን እንዴት በበጎ ነገሮች ማሸነፍ እንደሚቻል ከይስሐቅ ሕይወት ይማራሉ፤በመምህሩ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- “ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ” ሮሜ ፲፪ ፥ ፳፩

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ዘፍጥ. ፳፮ ፥ ፩-፴፫፣ ሮሜ. ፲፪፥ ፱-፳፩፣ ማቴ. ፭ ፥ ፵፫-፵፰፣ እና ማቴ. ፲፰ ፥ ፳፩-፴፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው።
- መምህሩ ስለ ክፉ እና በጎ ነገሮች ሕፃናት ሊረዱት በሚችሉት ምሳሌ ይግለጹላቸው።
- ሕፃናት ጥሩ እና መጥፎን ከማን እንደሚማሩ እንዴት እንደሚለዩ መምህሩ ይጠይቋቸው።

## የሳምንቱ ትምህርት

- ይስሐቅ አርባ ዓመት ሲሆነው ርብቃን አግብቶ ያዕቆብን እና ዔሳውን ወለደ። በአባቱ በአብርሃም ዘመን እንደነበረው በምድሪቱ ላይ ራብ ሆነ። ስለዚህ ይስሐቅ ምግብ ሊፈልግ ከነቤተሰቡ ወደ ፍልስጥኤም ምድር ወረደ። እግዚአብሔር ከይስሐቅ ጋር ስለነበር የፍልስጥኤም ንጉሥ አቤሜሌክ ይስሐቅን ከነቤተሰቡ አክብሮ ተቀበላቸው።
- ሕዝቡም እነርሱን እንዳይነካ አዘዘ። ይስሐቅ በፍልስጥኤም ምድር በጌራራ ተቀምጦ እግዚአብሔር በብዙ ነገሮች ስለባረከው የፍልስጥኤም ሰዎች ቀኑበት። ሕፃናት በዚያ ዘመን ሰዎች የመጠጥ ውኃ የሚያገኙት ከጉድጓድ ውኃ ነበር። እንደዛሬው በየቤታቸው የባንቧ ውኃ አልነበረም። የፍልስጥኤም ሰዎች እግዚአብሔር ይስሐቅን በዘር በበግና በከብቶች መንጋ ስለባረከው ቀንተው በአባቱ በአብርሃም ዘመን የተቆፈሩትን የውኃ ጉድጓዶች ደፈኗቸው። ይስሐቅንም ከሀገራቸው እንዲወጣ ንጉሡ አቤሜሌክ አዘዘው።
- ይስሐቅ ምንም እንኳን በብዙ ነገር ከእነርሱ ይልቅ እጅግ የበረታ ሰው ቢሆንም ክፉውን

www.zeorthodox.org

በክፉ አልመለሰም፡፡ እነርሱ የውኃ ጉድጓዶቹን እንደደፈኑ በእነርሱ ላይ ክፉ አላደረገም፡፡

- ይልቁንም ቤተሰቡን ይዞ ከእነርሱ ተለይቶ ሄደ፤ በጌራራም ሸለቆ ተቀመጠ፡፡ በዚያም በአባቱ በአብርሃም ዘመን ተቆፍረው ነገር ግን አብርሃም ከሞተ በኋላ ፍልስጥኤማውያን ደፍነዋቸው የነበሩትን የውሃ ጉድጓዶች እንደገና አስቆፈራቸው፡፡ በአባቱ በአብርሃም ዘመን ይጠሩባቸው በነበረው ስም ጉድጓዶቹን ጠራቸው፡፡
- በመጀመሪያው ጉድጓድ የጌራራ አገር እረኞች ከይስሐቅ እረኞች ጋር "ውኃው የእኛ ነው" ሲሉ ስለተጣሉ የጉድጓዱን ስም ‹‹ኤሴቅ›› ብሎ ጠራው፡፡ በሁለተኛውም ጉድጓድ ደግመው ተጣሉ፤ የሁለተኛውን ጉድጓድ ስም ‹‹ስጥና›› አለው፡፡ ይስሐቅ ከዚያ እልፍ ብሎ ሌላ ጉድጓድ አስቆፈረ፡፡ በሦስተኛው ጉድጓድ ግን አልተጣሉም፤ ስለዚህ ይስሐቅ አሁን እግዚአብሔር አሰፋልን በምድርም እንበዛላለን ሲል ጥል የሌለበትን ጉድጓድ ስም ‹‹ርኆቦት›› (መርኅብ) ብሎ ጠራው፡፡ በዚህም ይስሐቅ ጠላቶቹን ፍልስጥኤማውያንን በመልካም አሸነፈ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ሕፃናት ከዚህ ታሪክ ይስሐቅ እንዴት ክፉ እና ቀናተኛ ሰዎችን በመልካም እንዳሸነፈ ተምራችኋል፡፡ እናንተም ክፉ ሥነ-ምግባር ያላቸውን ሰዎች ክፉ ነገር በመመለስ ወይም በማድረግ ሳይሆን እንደ ይስሐቅ በመልካም እና በበጎ ሥራ ማሸነፍ ትችላላችሁ፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ይስሐቅ ወደ ፍልስጥኤም ሀገር የሄደው በምን ምክንያት ነበር?
2. ይስሐቅን የተቀበለው የፍልስጥኤም ንጉሥ ማን ይባላል?
3. ፍልስጥኤማውያን በይስሐቅ የቀኑት ለምንድ ነው?
4. ፍልስጥኤማውያን በይስሐቅ ላይ ያደረጉት ክፉ ነገር ምን ነበር?
5. ይስሐቅ ክፉ የነበሩትን ፍልስጥኤማውያንን እንዴት ነበር ያሸነፋቸው?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ በመጽሐፍ ላይ የሚገኙትን ሥዕሎች ቀለም እንዲቀቡ እና የጉድጓዶቹን ስሞች እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ሕፃናት ክፉ ሰዎችን እንዴት ለማሸነፍ እንደሚፈልጉ ይጠይቋቸው፡፡
- ለሕፃናቱ ክፉውን በመልካም በማሸነፍ የሚገኘውን ጥቅም በሚገባቸው ቋንቋ እና ምሳሌ ያስረዱዋቸው፡፡

# ዮሴፍ ለቤተሰቡ ይቅርታ አደረገ

## ሃያ ስምንተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት፤ ከዮሴፍ ሕይወት ክፉ ላደረጉብን ሰዎች ይቅርታ ማድረግ እና ጠላቶቻችንን መውደድ እንደሚገባይማራሉ፤ በመምህሩ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ" ማቴ. ፭ ፥ ፵፬

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ማቴ. ፭ ፥ ፵፫-፵፰፣ ዘፍ. ፵፪ - ፵፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት በቤተሰብ ውስጥ ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ይጠይቁዋቸው፡፡
- ሕፃናት በቤተሰባቸውም ላይ ሆነ በጓደኞቻቸው ወይም ከሌሎችም ሰዎች ጋር መጣላትና ቂም መያዝ እንደሌለባቸው አጽንኦት ሰጥተው ያስተምሩአቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

- ዮሴፍ በግብጽ አገር በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር ሰባት ዓመት እህልን እየሰበሰበ አከማቹ፡፡ በራብ ዘመንም ብዙ ሰዎችን ከሞት አዳነ፡፡
- የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ግብጻዊቷን አስናትን ለዮሴፍ ሚስት ትሆነው ዘንድ አመጣለት፡፡ ዮሴፍም ከአስናት ምናሴንና ኤፍሬምን ወለደ፡፡ ዮሴፍ በግብጽ ምድር ከፈርዖን ቀጥሎ አለቃ በሆነበት ዘመን በምድረ እስራኤል ራብ ስለነበር የዮሴፍ ወንድሞች ምግብ ፍለጋ ወደ ግብጽ ሀገር መጡ፡፡ ዮሴፍ ምንም እንኳን ወንድሞቹ በክፋት ተነሣስተው ለባርነት ቢሸጡትም እና ክፉ ቢያደርጉበትም እርሱ ግን በመልካም ተቀበላቸው፡፡ ወንድሞቹ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ምግብ ከሰጣቸው በኋላ አባታቸው ያዕቆብን እና ታናሽ ወንድማቸውን ይዘው እንዲመጡ ነገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

- ዮሴፍ ወንድሞቹን ያውቃቸው ነበር፤ እነርሱ ግን ይህን ሁሉ ያደረገላቸው ዮሴፍ እንደሆነ አላወቁም ነበር። ዮሴፍ አባቱን ያዕቆብን ከብዙ ዓመታት በኋላ አየው ወንድሞቹንም እንዲሁ።
- ያዕቆብ ዮሴፍን ዳግም በሕይወት ስላገኘው እጅግ በጣም ደስ አለው፤ እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ዮሴፍንም ባረከው። ዮሴፍ ለቤተሰቡ ይቅርታ አደረገላቸው።
- ወንድሞቹ ክፉ እንደአደረጉበት እርሱ ክፉ አላደረገባቸውም። መቅጣት ሲችል ሊጎዳቸው አቅም ኖሮት እያለ እግዚአብሔር ሕልሙን ስለፈጸመለት ዮሴፍ ወንድሞቹን ይቅር ማለት ቻለ።
- በግብጽ ምድርም ይንከባከባቸው፣ መልካምና በጎ ነገርንም ያደርግላቸው ነበር።

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት ዮሴፍ ክፉ ነገር ያደረጉበትን ወንድሞቹን እንዴት ይቅርታ እንዳደረገላቸው ከዚህ ታሪክ ተምራችኋል። እናንተም ለወንድምና እኅቶቻችሁ፣ ለቤተሰባችሁ እንዲሁም ለጓደኞቻችሁ ይቅርታ ማድረግን እና በጎ ሥራ መሥራትን ልመዱ።

### ጥያቄዎች:-

1. የዮሴፍ ሚስት ማን ትባላለች?
2. ዮሴፍ ስንት ልጆችን ወለደ? ስማቸው ማን ማን ይባላል?
3. ዮሴፍ ለቤተሰቡ ምን አደረገ?
4. ያዕቆብ ዮሴፍን ዳግመኛ ሲያገኘው ምን ተሰማው?
5. ከዮሴፍ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህሩ ሕፃናት የሚጠሉት ወይም ቂም የያዙበት ሰው ካለ በግልጽነት እንዲነግሩት እና ይቅርታ እንዲያደርጉለት ይምከሩአቸው።
- ይቅርታ ማድረግና መታረቅ የሚሰጠውን ጥቅምና በእግዚአብሔር የተወደደ ተግባር እንደሆነ ሕፃናቱ በሚገባቸው መንገድ በምሳሌ ይንገሩዋቸው።
- ዮሴፍና ቤተሰቡ ከብዙ ዘመናት በኋላ ሲገናኙ እና ይቅር ሲባባሉ የሚያሳየውን ምስል ሕፃናት ቀለም እንዲቀቡ ይንገሩዋቸው።

# ሳሙኤል ዳዊትን ቀባው

## ሃያ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ሕፃናት ስለ ንጉሥ ዳዊት የልጅነት ዘመን አውቀው፤ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

- "በላያቸውም *አንድ እረኛ አቆማለሁ፤ እርሱም ያሰማራቸዋል፥ እርሱም ባሪያዬ ዳዊት ነው፣ ያሰማራቸዋል እረኛም ይሆናቸዋል።"* ትን.ሕዝ. ፴፬÷ ፳፫

**ምንባብ፡-**

- ፩ኛ ሳሙ. ፲፮÷፴፬-፴፮

## መግቢያ

- ዳዊት የአይሁድና የመላው እስራኤል ንጉሥ ነበር፡፡ እምነትና ትሕትና ስለነበረውም እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሆን መረጠው፡፡
- በዛሬው ትምህርታችን የዳዊትን የልጅነት ዘመንና ለንግሥና መመረጡን እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

- ሕፃኑ ዳዊት የአባቶቹን በጎች የሚጠብቅ መልከ መልካም ልጅ ነበር፡፡ በጎቹን ይወዳቸዋል፡፡ በዋሽንት ያዜምላቸዋል፤ በጎቹም በዙሪያው ይሰበሰባሉ፡፡
- ዳዊት በጎቹን የሚጠብቅበት ዘንግ ነበረው፡፡ ለበጎቹም ይጠነቀቃል፡፡ እነርሱን ለመጠበቅ እና አውሬ እንዳይበላቸው ለመከላከል ከአንበሳና ድብ ጋር ይታገል ነበር፡፡
- ዳዊት ሁሌም የእግዚአብሔርን ስም ይጠራል፡፡ የአባቱን በጎች ለመጠበቅ ከመውጣቱም በፊት ሁልገዜ ይጸልያል፣ ይዘምራል፡፡
- ከአንበሳና ድብ በጎቹን የሚያድንበትን ኃይልና ችሎታ እንደ ሰጠው ያውቅና ያምን ስለነበር ሁሌም እግዚአብሔርን ያመሰግናል፡፡

### *ለንጉሥነት መመረጡ፡-*

- ሳሙኤል የተባለ ነቢይ ነበር፡፡ *ልጆች ነቢይ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?* ነቢይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መልእክት እንዲነግር የሚልከው ነው ፡፡

www.zeorthodox.org

- እግዚአብሔር አንድ ቀን ነብዩ ሳሙኤልን ቀንዱን በዘይት ሞልቶ እሴይ ወደ ተባለ ሰው ቤት እንዲሄድ ነገረው። ከእሴይ ልጆችም ለንግሥና የመረጠውን እንዲቀባው አዘዘው።
- እግዚአብሔር እንደነገረውም ነብዩ ሳሙኤል ወደ እሴይ ሄደ። እሴይና ጎረቤቶቹ ሳሙኤል የእግዚአብሔር ነቢይ ስለሆነ የእግዚአብሔር መልእክት እንዳለው አውቀው ለምን እንደመጣ ጠየቁት። ሳሙኤልም መሥዋዕት ለማቅረብ እንደመጣ፤ ራሳቸውን እንዲያነጹና ለመሥዋዕት ሥርዓቱ እንዲዘጋጁ ነገራቸው።
- ወደ እሴይ ቤት ከገባ በኋላም፤ የመጀመሪያው የእሴይ ልጅ ሲመጣ ሳሙኤል ‹‹እግዚአብሔር ለንግሥና የመረጠው ይሄ ይሆናል›› አለ። እግዚአብሔር ግን እርሱን እንዳልመረጠና ሰው ፊትን ቢያይም እርሱ ግን ልብን እንደሚያይ ነገረው።
- እሴይ ልጆቹን ሁሉ በሳሙኤል ፊት ተራ በተራ እያመጣ አቆመ። እግዚአብሔር ግን ሁሉንም አልመረጠም። በመጨረሻም ‹‹የቀረ ልጅ የለምን?›› ብሎ ነብዩ ሳሙኤል እሴይን ጠየቀው። እሴይም የመጨረሻው ልጅ እንዳለና በጎች እየጠበቀ መሆኑንም ነገረው።
- ሳሙኤልም ፈጥኖ እንዲያመጣው ነገረው፤የመጨረሻው ልጅ ዳዊት ሲመጣ ብሩህ፣ መልከ መልካምና ግርማ ሞገስ ያለው ልጅ ነበር። እግዚአብሔርም ለሳሙኤል ***"ይህ ነውና ተነሥተህ ቀባው"*** አለ።
- ዳዊት በወንድሞቹ መካከል ተቀባ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ።

**ጥያቄዎች፡-**

1.ዳዊት አባቱን ያገለግል የነበረው እንዴት ነው?

_______________________________________________

www.zeorthodox.org

2. ዳዊት ዘንግ ይይዝ የነበረውስ ለምንድነው?

_______________________________________________

3. ከድብና ከአንበሳ ጋር የሚታገልበትን ኃይል ማን ሰጠው?

_______________________________________________

4. ዳዊት ከድብ እና ከአንበሳ ጋር የሚታገለው ለምን ነበር?

_______________________________________________

5. ነቢይ ምንድነው?

______________________________

6. ወደ እሴይ ቤት የተላከው ነቢይ ማን ነው?

______________________________

7. ነቢዩ በእሴይ ቤት ለንግሥና የሚሆነውን ሲመርጥ  ዳዊት ምን ያደርግ ነበር?

______________________________

***መዝሙር፡-***

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው (2)

የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው (2) አምላኬ መመኪያዬ ነው (2)

www.zeorthodox.org

# ዳዊት ጎልያድን አሸነፈ

## ሠላሳኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት፤ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደሆነ አውቀው፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

### የሚጠና ጥቅስ፡-

- "በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል:: "መዝ. ፳፫ ÷ ፬

### ምንባብ፡-

- ፩ኛ ሳሙ. ፩፮ እና ፩፯

## መግቢያ

- የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን የተመረጠው ሳኦል ነበር።
- ሳኦል ግን በተደጋጋሚ ለእግዚአብሔር አልታዘዘም ነበር። ስለዚህ የእግዚአብሔር መንፈስ ተለይቶት በርኩስ መንፈስ ይሰቃይ ነበር።
- በዛሬው ትምህርታችንም ዳዊት በሳኦል ላይ የነበረውን ሰይጣን እንዴት እንዳራቀለት፤ ንጉሡንና እስራኤልን ረድቶ ጎልያድን ያሸነፈበትን ታሪክ እንማራለን።

## ትምህርቱ፡-

- ሳኦል ለእግዚአብሔር ሳላልታዘዘ የእግዚአብሔር መንፈስ ራቀው። ርኩስ መንፈስም በላዩ አድሮበት ያሰቃየው ነበር። በገና ደርዳሪ እንዲጠሩለት አገልጋዮቹን አዘዘ። አገልጋዮቹም የእሴይ ልጅ ዳዊት ጥሩ በገና ደርዳሪ እንደሆነ ለሳኦል ነገሩት።
- ሳኦል እሴይ ልጁን ዳዊትን እንዲልክለት መልእክት ላከበት። እሴይም ዳዊትን አህያ ሰጥቶ፣ ምግብና ወይን አስይዞ ወደ ሳኦል ዘንድ ላከው። ሳኦል ዳዊትን ሲያየው በጣም ወደደው፣ ሾመውም። ስለዚህ ሳኦል ከዳዊት ጋር መኖር ጀመረ፤ በገና ይደረድርለትም ነበር።
- ዳዊት በገና ሲደረድር ሳኦልን የሚያሰቃየው ርኩስ መንፈስ ይርቅለት ነበር።
- ዳዊት በገና የመደርደር፣ በመዝሙር እግዚአብሔርን የማመስገን ጸጋ ነበረው። ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው 'መዝሙረ ዳዊት' ዳዊት ለእግዚአብሔር ያቀረባቸው ምሥጋናዎች ናቸው።

www.zeorthodox.org

- ዳዊት አባቱንና ሳኦልን እያገለገለ ኖረ፡፡
- አንድ ቀን ፍልስጥኤም ከእስራኤል ጋር ሊዋጉ ወጡ፡፡ ከፍልስጤማውያን ወገን ጎልያድ የተባለ ግዙፍ ሰው ወጥቶ፤ ‹‹ከእስራኤላውያን ወገን ከእኔ ጋር መዋጋት የሚችል አንድ ሰው ይምጣ›› አለ፡፡ እስራኤልንም አዋረደ፣ በእግዚአብሔር ያላቸውንም እምነት ናቀባቸው፡፡
- እስራኤልም ጎልያድ ግዙፍና ጠንካር ስለነበረ ፈሩ፡፡ ዳዊት ግን ወጣት ብላቴና ቢሆንም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ ስለሚያውቅ እና ጽኑ እምነት ስልነበረው ጎልያድን አልፈራም፡፡
- ዳዊት ወደ ንግሡ ሳኦል ቀርቦ በጎቹን ከአንበሳና ድብ አፍ እንዴት ያድን እንደነበረ፤ ግዙፉን ጎልያድንም እንደሚያሸንፈው በእግዚአብሔር ታምኖ ተናገረ፡፡ ሳኦልም ከጎልያድ ጋር እንዲዋጋ ፈቀደለት፡፡
- ጎልያድ ትንሹን ብላቴና ዳዊትን ሲያየው በንቀት ***"ወደ እኔ ና÷ ሥጋህንም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ"*** አለው፡፡
- ዳዊትም ***"አንተ ሰይፍና ጦር ይዘህ ትመጣብኛለህ እኔ ግን …….በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ"*** አለ፡፡
- ዳዊት ከእረኛ ኮሮጆው አንድ ድንጋይ አውጥቶ በወንጭፍ አድርጎ ወነጨፈው፣ በጎልያድ ግምባር ድንጋዩ ተቀረቀረ፤ ግዙፉ ጎልያድም ወደቀ፡፡ ዳዊት እግዚአብሔር ድል እንደሚሰጠው አምኖ ግዙፉን ሰው በወንጭፍና በድንጋይ ድል አደረገ፡፡
- እስራኤልም በደስታ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡ ***"ሳኦል ሺህ ዳዊትም እልፍ (አሥር ሺህ) ገደለ"*** አሉ፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ሳኦልን በእስራኤል እንዲነግሥ የሾመው ማነው?
2. የእግዚአብሔር መንፈስ ለምን ከሳኦል ተለየ?
3. ዳዊት ከሳኦል ርኩስ መንፈስ ያርቅለት የነበረው እንዴት ነው?
4. የዳዊት አባት ማነው?
5. እስራኤልን የተገዳደረው/የተሳደበው/ ግዙፍ ሰው ማን ይባላል?እስራኤልስ ለምን ፈሩት?
6. ዳዊት ጎልያድን ፈርቶት ነበርን? ምንስ አለው?

***መዝሙር፡-***

ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ
ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ *መዝ ፵፮÷፲፩*

www.zeorthodox.org

# ዳዊትና ዮናታን

## ሠላሳ አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ሕፃናት ከዳዊትና ከዮናታን ታሪክ ስለ እውነተኛ ወዳጅነት ተገንዝበው፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

- **"ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወድዳል፤ ወንድምም ለመከራ ይወለዳል። "** ምሳሌ ፲፯፥፲፯

**ምንባብ ፡-**

- ፩ኛ ሳሙ. ፲፰-፳ እና ፪ኛ ሳሙ. ፩ እና ፱

***መግቢያ***

- ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ዳዊት ከፍልስጤማውያ ወገን የሆነውን ግዙፉን ጎልያድን በእግዚአብሔር ኃይል ካሸነፈ በኋላ እስራኤላውያን፤ ***"ሳኦል ሺህ፣ ዳዊት ዐሥር ሺህ ገደለ።"*** እያሉ ማመስገናቸውን ታስታውሳላችሁ?
- በዛሬው ትምህርታችን፤ ሳኦል በቅንዓት ዳዊት ላይ እንደተነሣበት እንማራለን። በተጨማሪም በሳኦል ልጅ በዮናታንና በዳዊት መካከል የነበረውን ፍጹም ወንድማማችነት እናያለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

***ዮናታን ለዳዊት፡-***

- የመጀመሪው የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል ዮናታን የተባለ ልጅ ነበረው።
- ዳዊት ግዙፉን ጎልያድን ከገደለው በኋላ የንጉሡ ሳኦል ልጅ ዮናታን ዳዊትን እጅግ ወዶት፤የራሱን ልብስና ሰይፍም ሸልሞታል።
- ዳዊት ከንጉሡ ከሳኦል በላይ በእስራኤላውያን ዘንድ ታዋቂ ሆነ። ንጉሡ ሳኦልም በዚህ ቀንቶ ዳዊትን ለመግደል ፈለገ።
- አንድ ቀን ሳኦል ታምሞ ዳዊት በገና እየደረደረለት ሳለ ጦር ወረወረበት፤ዳዊትም ዘወር ብሎ አመለጠ።
- ከዚያም በተደጋጋሚ ሊገድለው እንደሚፈልግ አውቆ ዳዊት ከሳኦል ፊት ሸሸ። በሌላ ሥፍራም ሄዶ ተቀመጠ፤እስራኤላውያን ግን ዳዊትን ይወዱት ነበር።
- አንድ ቀንም የሳኦል ልጅ፣የዳዊት ወዳጅ ዮናታን አባቱን ***"እርሱ አልበደለህምና***

www.zeorthodox.org

*ሥራውም ለአንተ እጅግ መልካም ሆኖአልና ንጉሡ ባሪያውን ዳዊትን አይበድለው"* ብሎ ተናገረው፡፡

- ንጉሡም በልጁ ንግግር ተደስቶ ለጊዜው ዳዊትን እንደማይገድለው ቃል ገባለት፡፡ ነገር ግን ቅናቱ ተነሥቶበት ሳኦል ዳዊትን በድጋሚ ሊገድለው ፈለገ፤ዮናታንም ሳኦልን አስመለጠው፡፡
- ስለዚህም በሳኦል ልጁን ዮናታንን *"ዳዊት በሕይወት ካለ አንተ ንጉሥ አትሆንም"* አለው፡፡
- ዮናታን ግን ንጉሥ ለመሆን ከመጓጓት ይልቅ ለወዳጁ ለዳዊት ተጠነቀቀለት፡፡ ምልክት ሰጥቶም አስመለጠው፡፡ (መምህር በዳዊትና በዮናታን መካከል የነበረውን ምልክት ያስረዱአቸው፡፡) ፩ኛ ሳሙ. ፳÷ ፲፰-፴፪
- ዮናታንና ዳዊት በምስጢር ተገናኝተው፣ተቃቅፈውና ተላቅሰው ተለያዩ፡፡ ለምን ያለቅሱ ይመስላችኋል? የሚዋደዱ ጓደኛሞች ስለነበሩ ነው፡፡
- ዮናታን ዳዊትን *"በደኅና ሂድ፤ እነሆ÷ በእኔና በአንተ መካከል ለዘላለም እግዚአብሔር ይሁን"* አለ፡፡ ዳዊት ተሰደደ፣ ዮናታንም ወደ ከተማ ገባ፡፡

### *ዳዊት ለዮናታን፦*

- "ዮናታን *ቸርነትን እንዳደረግሁልህ ለኔም ቸርነትን አድርግልኝ"* ባለው መሠረትና እግዚአብሔርን በመካከላቸው እንዳደረጉ፤ ዳዊትም የዮናታንን መልካምነት አሰበ፡፡
- ዳዊት ከሳኦል ቤተ መንግሥት ከሸሸ በኋላ ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ተዋጉ፡፡ ሳኦልና ሦስት ልጆቹ የዳዊት ወዳጅ ዮናታንንም ጨምሮ ሞቱ፡፡
- ዳዊትም በስደት ሆኖ ይሄን ሲሰማ በጣም አዘነ አለቀሰም፡፡
- ከዚህ በኋላ ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ሆነ፡፡ በርሱና በዮናታን መካከል የነበረውን እግዚአብሔርንና የዮናታንን ቃንነት አስቦ፤ለዮናታን ቤተሰቦች መልካም ለማድረግ ወሰነ፡፡ እያጠያየቀ ሲያስፈልግ የዮናታን ልጅ መኖሩን አረጋግጦ አስጠራው፡፡ ልጁም ለንጉሡ የሚገባውን ክብር ሰጥቶ ወደ ዳዊት መጣ፡፡
- ንጉሡ ዳዊትም *"ስለ ዮናታን መልካም አደርግልሃለሁ÷የሳኦልን መሬት በሙሉ ውሰድ"* አለው፡፡ በጦርነቱ ወቅት አሳዳጊው ይዛው ስትሸሽ ውድቆ የተጎዳው ልጅም ንጉሡን አመስግኖ በደስታ ሄደ፡፡

ዳዊት ለዮናታን የነበረውን ፍቅርና ውለታውን ለልጁ መልካም በማድረግ አሳየ፡፡

www.zeorthodox.org

**ጥያቄዎች ፡-**

1.ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ለምን ፈለገ ?

2. የዳዊት ወዳጅ የነበረው የሳኦል ልጅ  ማን ነበር ?

3. ቅናት ምንድን ነው?

4.በዳዊትና በዮናታን መካከል የነበረው ቃል ኪዳን ምን ነበር?

5. ዳዊት ቃሉን ጠብቋልን? እንዴት?

6. ሳኦልና ዮናታን ሲሞቱ ዳዊት ምን ተሰማው?

7. ዮናታን እውነተኛ ወዳጅ ነበር? ለምን?

www.zeorthodox.org

**መዝሙር፡-**

እግዚአብሔር ይወዳናል ይጠብቀናል(2)
እርሱ ለኛ ደሙን ክሶልናል(2)

# ተአምረኛው ዓሣ አጠማመድ

## ሠላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**ዓላማ :-**

- ሕፃናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸማቸውን ተአምራት አውቀው፤ ከመምህሩ ለሚቀርበርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**ምንባብ፡-**

ሉቃ ፭÷፩-፲፩

## መግቢያ

- ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ የፈጸመው የመጀመሪያ ተአምር ምን ነበር? ውኃን ወደ ወይንነት ቀይሮአል፡፡
- በዚህ እና በሚቀጥሉት ተከታታይ ትምህርቶታቻችን ጌታችን የፈጸማቸውን ተአምራት እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ፡-

- አንድ ቀን ጌታችን በባሕር ዳርቻ በዓሣ አጥማጆች ጀልባ ላይ ያስተምር ነበር፡፡
- ልጆች ዓሣ አጥማጆች ምን እንደሚሠሩ ታውቃላችሁ? ታንኳ ወይም ጀልባ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ለመምህር ንገሩ ፡፡
- ጌታችን በባሕር ዳርቻ ቆሞ ሁለት ታንኳዎችን አየ፤ ከዚያም ወደ ስምዖን ታንኳ ወጥቶ ያስተምር ጀምር፡፡ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ስምዖንን ታንኳይቱን ወደ መሐል ፈቀቅ አድርጎ ዓሣ እንዲያጠምድ አዘዘው፡፡ ዓሣ ለማጥመድ ብዙ ደክመው አጥተው ስለነበረ፤ ***"ምንም አልያዝንም ስለ ቃልህ እንጥላን"*** ብሎ መረቡን ጣለ፡፡
- ይህንንም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፡፡ መረቦቹ ዓሣዎቹ ብዛት የተነሳ ተቀደዱ፡ እነ ስምዖን በመረቡ የተያዙትን እጅግ ብዙ ዓሣዎች ለማውጣት ፤ ስላልቻሉ በሌላ ታንኳ ያሉ ጓደኞቻቸውን እርዳታ ጠየቁ፡፡ ሁለቱ ታንኳዎች እንኪሰጥሙም ዓሣ አከማቹ፡፡
- ስምዖንም የጌታችንን ተአምር ካየ በኋላ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ አለው፡፡
- በሌላይቱ ታንኳ የነበሩና የረዱት ያዕቆብና ዮሐንስ በዚያ የነበሩትም ሁሉ እጅግ

www.zeorthodox.org

ተደነቁ፤ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ። ልጆች እኛም እግዚአብሔር ሲረዳን ማመስገን አለብን።

- ጌታችን ኢየሱስም ስምዖንን "ከእንግዲህ ሰውን ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታጠምድ ትሆናለህ" አለው።
- በሁለቱ ታንኳዎች የነበሩት ዓሣ አጥማጆች ታንኳዎቻቸው ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት።

**ልምምድ፡-**

1. ጌታችን በመጀመሪያ ያደረው ተአምር ምን ነበር? ----------------------------------------------
2. ዓሣ አጥማጆች ሥራቸው ምንድን ነው? ----------------------------------------------------
3. ስምዖንና ጓደኞቹ ጌታችን ወደ እነሱ መጥቶ ካስተማራቸው እና ወደ መሐል ፈቀቅ አድርገው በቀኝ በኩል መረባቸውን እንዲጥሉና ዓሣ እንዲያጠምዱ ካዘዛቸው በፊት ዓሳ ማጥመድ እና መያዝ ችለው ነበር?--------------------------------------------------------
4. ጌታችን ካዘዛቸው በኋላስ ምን ተፈጠረ ? ----------------------------------------------
5. ዓሣ አጥማጆቹ ከተአምራቱ በኋላ ምን አደረጉ? -------------------------------------------
6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተሉትን ዓሣ አጥማጆች ስም ግለጹ?

   ----------------------------------------------------------------------------------------

**መዝሙር፡-**

ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ

ተአምሩን ለዓለም ንገሩ(2) ድንቅ ሥራውን መስክሩ።

***ይቆየን።***

www.zeorthodox.org

# ጌታችን ዓይነ ሥውሩን አዳነ

## ሠላሳ ሦስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ሕፃናት ከትምህርቱ ጌታችን የፈጸማቸውን ተአምራት አውቀው፤ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**ምንባብ፡-**

- ዮሐ ፱÷፩-፲፩

## መግቢያ

- ከዚህ በፊት ስለፈጸመው ተዓምራት ተምረናል። ልጆች ካለፈው ትምህርት የምታስታውሱትን ለመምህራችሁ ግለጹ።
- ዛሬም የጌታቻንን ተአምራት እንማራለን።

## ትምህርቱ፡-

- ሲወለድ ጀምሮ ዕውር የሆነ አንድ ሰው ነበር። ጌታችን እያስተማረ ሲያልፍ ዐይነ ስውሩ ባለበት ቦታ ደረሰ።
- ***"መምህር ሆይ ÷ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ?"*** ብለው ደቀ መዛሙርቱ ጠየቁት።
- ጌታችንም ***"የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢኣት አልሠሩም"*** አላቸው።
- ይህንንም ብሎ ወደ መሬት እንትፍ ብሎ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና፤ ‹‹ሂድ በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ›› አለው። ጌታ እንዳዘዘው ሄዶ ታጠበ፤ እያየም መጣ። ድሮ የሚያውቁት ግን ***"እርሱ ነው! አይደለም!"*** በሚል ተከራከሩ። እርሱ ግን እኔ ነኝ አላቸው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደአዳነውም መሰከረላቸው።

www.zeorthodox.org

**ጥያቄዎች፡-**

1. ጌታችን ያዳነው ሰው ለምን ዕውር ሆኖ ተወለደ?
2. ጌታ ዕውሩን ሰው እንዴት አዳነው?
3. ዕውሩ ሰው ከዳነ በኋላ በፊት የሚያውቁት ምን አሉት?
4. እርሱስ ምን አላቸው?

# ነቢዩ ኤልያስ በቁራዎች ተመገበ

## ሠላሳ አራተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ሕፃናት የነቢዩ ኤልያስን፣ የንጉሡ አስዓብን እና የሕዝቡን ታሪክ ተገንዝበው፤ እግዚአብሔር ትእዛዙን ለሚፈጽሙ የሚያደርገውን እንክብካቤ ያውቃሉ፤ መምህሩ ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- **“ እንደ እግዚአብሔር ቃልም አደረገ፡፡......ቍራዎቹም በየጠዋት እና በየማታው እንጀራ እና *ሥጋ* ያመጡለት ነበር፣ ከወንዙም ይጠጣ ነበር፡፡ ”** *፩ኛ ነገ ፲፯÷ ፮- ፯*

**ምንባብ፡-**

- *፩ኛ ነገ ፲፯÷ ፩-፯*

## መግቢያ

- ዛሬ ኤልያስ ስለሚባል ነቢይና የእግዚአብሔር ሰው እንማራለን፡፡
- ነቢይ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ የሚያደርስ እና ሕዝቡም ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ የሚያስተምር ነው፡፡

## ትምህርቱ

- አክዓብ የተባለ የእስራኤል ንጉሥ ነበር፡፡ ጣዖት አምላኪም ነበር፡፡ ልጆች ጣዖት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ጣዖት ሰዎች መሥዋዕተ የሚሠውለትና የሚያመልኩት ራሳቸው በእጃቸው የሚሠሩት ቅርጽ ወይም ሐውልት ነው፡፡
- ይህም ***"የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም፣..."*** የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ መቃረን እና መጣስ ነው፡፡ የእስራኤል ንጉሥ አስዓብና ሕዝቡ የእግእዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሰው ጣዖት በማምለካቸው ምክንያት፤ ኤልያስ ዝናብ እንደማይኖር ለአክዓብ ነገረው ውጤቱም ረኃብ ሆነ፡፡
- ኤልያስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለጠበቀ፣ ወደ አንዲት ትንሽ ወንዝ እንዲሄድና ቍራዎች እንዲመግቡት እግዚእብሔር አዘዘለት፡፡
- ቍራ የአዕዋፍ ዝርያ ሆኖ ንስር የሚመስል ትልቅ ወፍ ነው፡፡ ኤልያስም እግዚአብሔር

www.zoorthodox.org

ወዳዘዘው ሥፍራ ሄደ። ቊራዎቹም በየዕለቱ ዳቦና ሥጋ ያመጡለታል፣ ያንን እየተመገበ ከትንሿ ወንዝ ምንጭም ይጠጣ ነበር።

## ማጠቃለያ፡-

- ልጆች ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ አለብን። ይህንን ስናደርግም እግዚአብሔር በአስቸጋሪ ጊዜያት ሁሉ ይጠብቀናል።
- በአክዓብ እና በሕዝቡ ኃጢአት ዝናብ እና ምግብ አልነበረም።
- እግዚአብሔር ግን ኤልያስን ሥጋ እና ዳቦ በየቀኑ እንዲመግቡት ቊራዎችን ልኮለታል። እግዚአብሔር እኛንም ይጠብቀናል።

### መልመጃ፡-

1 ጣዖታት ምንድን ናቸው ?

______________________________

2. እግዚአብሔር ኤልያስን የት እንዲሄድ አዘዘው ?

______________________________

3. ነቢዩ ኤልያስን እግዚአብሔር እንዴት ጠበቀው?

______________________________

### መዝሙር

ኢትግድፈነ(2) ወኢትመንነነ (2)
አምላከ ሰላም ተረድኣነ(4)

አትተወን(2) አትናቀንም
የሰላም አምላክ ሆይ እርዳን።

**ይቆየን።**

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ኤልያስና መበለቲቱ (አንድ)

## ሠላሳ አምስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ሕፃናት ከነቢዩ ኤልያስና ከመበለቲቱ ታሪክ እግዚአብሔር ትእዛዙን ለሚፈጽሙ የሚያደርገውን እንክብካቤ ያውቃሉ፤ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**ምንባብ፡-**

- ፩ኛ ነገ ፲፯÷ ፩-፯

## መግቢያ

- ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤልያስ እንዴት እንደተጠነቀቀለት ተምረናል፡፡
- ዛሬም እግዚአብሔር ለኤልያስ የሚያደርገው ጥበቃና እንክብካቤ እንደቀጠለ እና ነቢዩ ኤልያስ የመበለቲቱን ቤት እንደባረከ እንማራለን፡፡

# ትምህርቱ

- ባለፈው ትምህርታችን እግዚአብሔር የላካቸው ቁራዎች ለኤልያስ ዳቦና *ሥጋ* እያመጡለት፣ ከወንዝ ውኃ እየጠጣ መኖሩን ተምረናል፡፡
- ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ ግን ዝናብ ስላልነበረ ወንዙ ደረቀ፡፡ ***ዝናብ ለምን እንደቆመ ታስታውሳላችሁ?*** አክዓብና ሕዝቡ ጣዖት ስላመለኩ ነበር፡፡
- ወንዙ ስለደረቀ እግዚአብሔር ኤልያስን ወደ አንዲት መበለት ቤት ላከው፡፡ ባልዋ የሞተባት ሴት መበለት ትባላለች፡፡
- ነቢዩ ኤልያስ እግዚአብሔር ወደላከው ቦታ ሲሄድ ሴትዮዋ እንጨት ስትሰበስብ አገኛት፡፡ ጠርቶም ውኃ እና ዳቦ እንድትሰጠው ጠየቃት፡፡
- ሴትዮዋ በችግሩ ምክንያት ዳቦ እንደሌላት፤ በማሰሮዋ ጥቂት ዱቄትና ዘይትም ብቻ እንደቀራት ነገረችው፡፡ እንጨት የምትሰበሰበውም ለእርስዋና ለልጅዋ የሚሆን ምግብ ለማብሰል መሆኑን ገለጸችለት፡፡
- ነገር ግን ነቢዩ ኤልያስ በመጀመሪያ ሄዳ በማሰሮዋ የቀራትን ጥቂት ዘይት እና ዱቄት ለእርሱ እንድታመጣ ነገራት፡፡ ለእርስዋና ለልጅዋም እንደሚተርፍላት፤ ይሄም የእግዚአብሔር በረከት መሆኑንና ዝናብ እስኪዘንብ ድረስ ዱቄቱና ዘይቱ እንደማይጎድል አበሠራት፡፡

www.zeorthodox.org

- ስለዚህም ወደ ቤትዋ ሄዳ ለኤልያስ፣ለእርስዋና ለልጅዋም ዳቦ ጋገረች፣ያለቀው ዱቄትና ዘይትም እንደ ነበዩ ቃል ሙሉ ሆኖ ኖረ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- እግዚአብሔር በረከቱን በቅዱሳን ይልካል፡፡ሴትየዋ ነቢዩን ኤልያስን ስላገለገለች እግዚአብሔር ቤትዋን እና ያላትን ባረከላት፡፡ እርሷና ልጅዋም ከረሀብና ከሞት ተረፉ፡፡

### መልመጃ፡-

1. ኤልያስ ይጠጣበት የነበረ ወንዝ ሲደርቅ የት ሄደ?
2. እግዚአብሔር የመበለቲቱን ቤት እንዴት ባረከ?

### መዝሙር፡-

አትተወን (2) አምላክ ሆይ አትጣለን
የሰላምአምላክአንተእርዳን

*ይቆየን፡፡*

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ኤልያስ እና መበለቲቱ (ሁለት)

## ሠላሳ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፦**

- ሕፃናት ከታሪኩ ኤልያስ የመበለቲቱን ልጅ ከሞት ማዳኑን እና እግዚአብሔር ቤቷን በነቢዩ ኤልያስ አማካኝነት እንዴት እንደባረከላት አውቀው፤ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

**ምንባብ፦**

- ፩ኛ ነገ ፲፯

**መግቢያ፦**

- ባለፉት ሁለት ሳምንታት እግዚአብሔር ኤልያስን እንዴት እንደመገበው እንዲሁም እግዚአብሔር የመበሊቲቱን ቤት በነቢዩ ኤልያስ እንደባረከላት ተምረናል።
- ዛሬም በኤልያስ አማካኝነት በመበሊቲቱ ቤት የተፈጸመውን ሌላ ተአምር እናያለን።

**ትምህርቱ፦**

- በነቢዩ ኤልያስ ዘመን በንጉሡ አክዓብ ኃጢአት ምክንያት በሀገሩ ሁሉ ረኃብና ድርቅ መጣ። ለነቢዩ ኤልያስ የሚመግበው ቊራ ከእግዚአብሔር ተልኮለት እየተመገበ፤ ከወንዝ ምንጭ ውኃ እየጠጣ ቆይቶአል። ከዚያም በኋላ በመበሊቲቱ ቤት ተጠግቶ አሳልፎአል።
- ከብዙ ቀናት በኋላም የመበለቲቱ ልጅ ታሞ ሞተ።
- መበለቲቱም በጣም አዝና እያለቀሰች ነቢዩን፤ ***"የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ ልጄንስ ትገድል ወደ እኔ መጥተተሃልን?"*** አለችው።
- ኤልያስም ይኖርበት በነበረው ሰገነት ልጅዋን ወስዶ በአልጋው ላይ አስተኛውና ***"የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ።"*** ሲል ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።
- ልጆች ሞቶ የነበረው የመበለቲቱ ልጅ ምን የሆነ ይመስላችኋል? ጌታችን እግዚአብሔር የኤልያስን ቃል ሰማ የሕፃኑም ነፍስ ተመለሰች።
- ነቢዩም ከሰገነት ሕፃኑን አወረደና ለእናቱ ***"እነሆ ልጅሽ በሕይወት ይኖራል"***ብሎ ሰጣት።

www.zeorthodox.org

**መደምደሚያ፡-**

- ኤልያስ የሕፃኑን ነፍስ ሁለቴ አድኖአል። በመጀመሪያ በራብ እንዳይሞቱ ዱቄቱን እና ዘይቱን በበረከት አብዝቶላቸዋል።ሁለተኛው እግዚአብሔር የኤልያስን ጸሎት ሰምቶ ከሞት አድኖታል።

## ከነዚህ ተከታታይ የነብዩ ኤልያስ ታሪኮች ሦስት ተአምራትን አይተናል።

- ቁራዎች ኤልያስን መገቡት።
- ለአንድ ጊዜ ብቻ የነበረውን ምግብ አብዝቶ ባረከላቸው።
- እግዚአብሔር የኤልያስን ጸሎት ሰምቶ የሕፃኑን ነፍስ መለሰለት።

**ልምምድ፡-**

1. ኤልያስ የድርቅና የራቡን ወቅትን እንዴት አለፈ?
2. የመበሊቲቱ ልጅ ምን ሆነ?
3. ነቢዩ ኤልያስ መበለቲቱንና የልጅዋን ሕይወት እንዴት አዳነ?

**መዝሙር**

እግዚአብሔር ይወደናል ይጠብቀናል (2)
እርሱ ለኛ ደሙን ክሶልናል (2)

www.zeorthodox.org

# የሦስቱ ሕፃናት ጽናት

## ሠላሳ ሰባተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ሕፃናት ስለ ቅዱስ ገብርኤል የማዳን ስራ እና የሦስቱን ሕፃናት የእምነት ጽናት ተገንዝበው፤ በመምህሩ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

- “ ***የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤*** ” ዳን. ፫÷፲፯
- **“ መልአኩም መልሶ፦ “እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥”** ሉቃ. ፩÷፲፱

**ምንባብ፡-**

- ሉቃ. ፩÷፳ - ፍጻሜ ምዕራፍ፤ ትንቢተ ዳንኤል ፫÷፩ - ፍጻሜ ምዕራፍ፣

## መግቢያ

- በዛሬው ትምህርታችን ቅዱስ ገብርኤል ሠለስቱ ደቂቅን ማዳኑን እንማራለን።

## ትምህርቱ ፡-

- ድኅነታችን ሲታወጅ የተላከው መልአክ **ቅዱስ ገብርኤል ነው**። በእምነታቸው የጸኑትን ሠለስቱ ደቂቅንም አድኖአል።
- ሦስቱ ወጣቶች የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው ጣዖት ***አንሰግድም*** በማለታቸው ወደ ሚነደው እቶን ሲጣሉ፤እሳቱን ሊያበርድላቸው የተላከው ***ቅዱስ ገብርኤል*** ነበር።
www.zeorthodox.org
- ታሪኩም እንዲህ ነበር፤ ናቡከደነፆር ዱራ ሜዳ በተባለ ቦታ ትልቅ ጣዖት አቆመ። ከዚያም ላቆመው ምስል ሁሉም እንዲሰግዱ ዐዋጅ አስነገረ።የሀገሩ ሕዝብ ሁሉ ንጉሡ ላቆመው ጣዖት ለምስሉ ሲሰግዱ ሦስቱ ወጣቶች ግን አንሰግድም አሉ። ሦስቱ ወጣቶች ናቡከደነፆር ላቆመው ጣዖት አንሰግድም በማለታቸው ከለዳውያን ከስሰው በንጉሡ ፊት አቆሙዋቸው።፡ንጉሡም በታላቅ ቁጣ ላቆመው ጣዖት ካልሰገዱ በሚነድ እቶን ውስጥ እንደሚጣሉ አስጠነቀቃቸው ።
- እነርሱም “***ንጉሥ ሆይ እኛ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም።***

*የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ከእጅህም ያድነናል፤ንጉሥ ሆይ ነገር ግን እርሱ ባያድነን፤አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ" አሉት።*

- ናቡከደነፆር ተቆጥቶ ሲድራቅ ሚሳቅ እና አብደናጎ የተባሉ ሦስቱ ወጣቶች ታስረው በሚነድ የእሳት እቶን ውስጥ እንዲጣሉ አደረገ። እሳቱ በተቀጣጠለበት ጉድጓድ የጣሉዋቸውንም ሰዎች የነበልባሉ ወላፈን ገደላቸው። በዚያን ጊዜም ንጉሡ ባየው ተደንቆ፤ "*ሦስቱ ሰዎች አስረን በእሳቱ ውስጥ ጥለን አልነበረምን?........እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ፤ ምንም አላቆሰላቸውም፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን መልክ ይመስላል"* አለ።
- ወጣቶችንም ‹‹ኑ ውጡ›› ብሎ ጠራቸው። የሦስቱ ወጣቶች የራሳቸው ጠጉር ሳይቃጠል ሰናፊላቸውም (ልብሳቸውም) የጢስ ሽታ ሳይኖረው ከእሳቱ ውስጥ ወጡ። ናቡከደነፆርም "*መልአኩን የላከ... በእርሱ የታመኑትን ባርያዎቹን ያዳነ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎንም አምላክ ይባረክ"* አለ። ያም መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነበረ።

# ማጠቃለያ

- ሲድራቅ፣ ሚሳቅ እና አብደናጎን የተባሉት ሦስቱ ወጣቶች ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው ጣዖት አንሰግድም አሉ። እግዚአብሔርን በማመን የጸኑት ወጣቶች በእሳት ውስጥ ሲጣሉ እግዚአብሔር መልአኩን ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ አዳናቸው።
- ንጉሡ ናበከደነፆርም ወጣቶቹ በእግዚአሔር ጥበቃ በእሳቱ ከመቃጠል መዳናቸውን አይቶ በእግዚአብሔር ሥራ ተደነቀ።

### መልመጃ

1. ጣዖት አቁሞ ሦስቱን ወጣቶች እንዲሰግዱለት ያዘዘው ንጉሥ ማን ይባላል? ___________
2. እግዚአብሔር አምላካችን ያድነናል፤ ለጣዖት አንሰግድም በማለታቸው በእሳት ውስጥ የተጣሉት ወጣቶች ስማቸው ማን ይባላል? ___________
3. ሦስቱን ወጣቶች ከተጣሉበት እሳት ውስጥ በእግዚአብሔር ተልኮ ያዳናቸው መልአክ ማነው? ___________

www.zeorthodox.org

### መዝሙር፦

እንደ አናንያ እንደ አዛርያ እንደ ሚሳኤል አጽናን እኛን

አጽናን እኛን(3) በእምነታችን

# ዳንኤል በአናብስት ጕድጓድ ተጣለ

## ሠላሳ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ሕፃናት የነቢዩ ዳንኤልን ታሪክ ተገንዝበው፤ እግዚአብሔር አምላካችንን ጸንተን ካመንበት ከማንኛውም አደጋ እንደሚያድነን ያውቃሉ፤ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-**

- **"የዚያን ጊዜም ንጉሡ አዘዘ፥ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጕድጓድ ጣሉት፤ ንጉሡም ተናገረ ዳንኤልንም፡- ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ እርሱ ያድንህ አለው።" ዳን.፮ ፥፲፮**

**ምንባብ፡-**

- ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ፮

## መግቢያ

- ልጆች ከዚህ ቀደም የተማራችሁትን የነቢዩ የኤልያስን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? በመከራ ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት እንደጠበቀው? እግዚአብሔር የመበለቲቱን ቤት በኤልያስ አማካኝነት እንደባረከ ታስታውሳላችሁ ? ለመምህር ግለጹ።
- ዛሬም እግዚአብሔር ዳንኤል የተባለውን ነቢይ ከአንበሶች እንዴት እንዳዳነው እንማራለን።

## ትምህርቱ፡-

- በአንድ ወቅት፤ ዳርዮስ የተባለ ንጉሥ በአገሩ ያሉ ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንዳይጸልዩ ዐወጀ። ሲጸልይ የተገኘም ወደ አናብስት ጕድጓድ እንደሚጣል ተነገረ። በዚያም ዳንኤል የተባለ የእግዚአብሔር ሰው ነበረ። ዳንኤል በቀን ሦስት ጊዜ ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አገር አቅጣጫ አዙሮ፤ መስኮቱን በመክፈት ይጸልይ ነበር። ዳንኤል የንጉሡን ዓዋጅ ቢሰማም እግዚአብሔርን በማምለክ መጸለዩን ግን አላቋረጠም።
- ዳንኤል በቤተ መንግሥቱ ከፍተኛ ሥልጣን ስለተሰጠው የሚቀኑበት ሰዎች በከተማይቱ ነበሩ። ዳንኤል መስኮቱን ከፍቶ እንደተለመደው ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ሲያዩ ፤ የንጉሡን ዓዋጅ ዳንኤል ሽሯል ብለው ከሰሱት። ንጉሡም ዳንኤል በአናብስት ጕድጓድ እንዲጣል አዘዘ።

www.zeorthodox.org

- ከዚያም በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ንጉሡ በአንበሶች ጉድጓድ በተጣለው በዳንኤል ላይ የሆነውን ለማየት ሄደ። ወደ ጉድጓዱም ተጠግቶ እንዲህ አለ "የሕያው እግዚአብሔር አገልጋይ ዳንኤል ሆይ፤ አምላክህ ከአናብስቱ አዳነህን?" ዳንኤልም "አምላኬ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ የአናብስቱን አፍ ዘጋ እነርሱም አልጎዱኝም" አለው።
- ንጉሡም ዳንኤል በመዳኑ በጣም ተደስቶ፤ በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራም ተገርሞ አገልጋዮቹ ዳንኤልን ከአንበሶቹ ጉድጓድ ውስጥ እንዲያወጡት አዘዘ። ዳንኤል በእግዚአብሔር ስላመነ አንዳችም ሳይደርስበት ወጣ ።
- ንጉሥ ዳርዮስ በግዛቱ ያሉ ሁሉ የዳንኤልን አምላክ እንዲያመልኩ ዓወጀ። እንዲህም አለ ‹‹ሕያው አምላክ ለዘላለም የሚኖር ነውና... ያድናል፤ይታደጋልም፤በሰማይ እና በምድርም ተአምራትን እና ድንቅን ይሠራል...።››

## ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን ?

- በእግዚአብሔር ስናምን ዳንኤልን እንዳዳነው እኛንም ከማንኛቸውም መከራ ያድነናል። እንደ ዳንኤልም መልአኩን ይልክልናል።
- እነዚህን የዳርዮስ ንግግሮች ድገሙ።
- የዳንኤል አምላክ ሕያው አምላክ ነው፣ያድናል፤ይታደጋልም።
- በሰማይና በምድርም ተአምራትና ድንቅ ይሠራል።

### ጥያቄዎች:-

1. ንጉሡ ዳርዮስ ስለአምልኮት ያወጣው ዐዋጅ ምን ነበር ?

___

2. ዳንኤል በቀን ስንቴ ይጸልይ ነበር ?

www.zeorthodox.org

___

3. ዳንኤል ወደ አናብስት ጉድጓድ የተጣለው ለምንድን ነው? አንበሶቹስ በሉት ?

___

### መዝሙር:-

እግዚአብሔር ይወደናል ይጠብቀናል (2)
እርሱ ለእኛ ደሙን ክሶልናል (2)

# በማኅፀን የተቀደሰ ነቢይ

## ሠላሳ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ:-**

- ሕፃናት ስለ ነቢዩ ኤርምያስ ታሪክ አውቀው፤ በመምህሩ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-**

- ***" በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፤በማሕፀንም ቀድሼሃለሁ "*** ኤር. ፩፥፭

**ምንባብ:-**

- ኤርም. ፩፥፩-፲፤ ፴፯፥፩-፳፰

## መግቢያ

- ነቢዩ ኤርምያስ ወላጁ ኬልቅያስ የተባለ ካህን ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መልእክት ከአርባ ዓመታት በላይ ለሕዝቡ ሲያደርስ ነበር፡፡ ዛሬ ስለዚህ ነቢይ እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

- ኤርምያስ ማለት "እግዚአብሔር ከፍ ያደርጋል" ማለት ነው፡፡ አባቱ በብንያም አገር ከነበሩት ካህናት አንዱ የሆነው ኬልቅያስ ነው፡፡
- ኤርምያስ ገና ብላቴና ሳለ የእግዚአብሔር ቃል መጣለት፡፡ እንዲህም አለው፡-***" በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፤በማሕፀንም ቀድሼሃለሁ "*** ኤር. ፩፥፭
- ***ኤርምያስም "ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም"*** አለ፡፡ እግዚአብሔርም ***"ወደምሰድህ ሁሉ ዘንድ ትሔዳለህና የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና ብላቴና ነኝ አትበል፡፡ እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ፡፡"*** አለው፡፡
- ከዚያም አፉን ዳሰሰውና ***"እነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ፤"*** አለው፡፡ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተላለፍ ጀመረ፡፡
- እንዲህ አድርጎ እያገለገለ ከዕለታት አንድ ቀን ለሕዝቡ እግዚአብሔር የፈቀደውን እና ያዘዘውን ተቀብለው በሕይወት እንዲኖሩ ይህን ባይፈጽሙ ግን እንደሚሞቱ ነገራቸው፡፡ የሚቀኑበት ሰዎች ተነሥተው በጉድጓድ ውስጥ ጣሉት፡፡
- አቤሜሌክ የተባለ ኢትዮጵያዊም በቤተመንግሥት ነበር እና ወደ ንጉሡ ገብቶ በከተማ

www.zeorthodox.org

ምግብ የለም በጕድጓድ ውስጥ የሚመግበው የለምና ነቢዩ በራብ እንዳይሞት ከጕድጓድ ላውጣው ብሎ አስፈቀደ። ንጉሡም ፈቀደለት ኤርምያስንም በጨርቅ ጕትቶ ከተጣለበት ጉድጓድ ውስጥ አወጣው። ነቢዩም ወጣ እና በግዞት አደባባይ ተቀመጠ።

## ተግባር

- ከቤተሰቦቻችን እና ከቤተ ክርስቲያን የሚነገረንን መልካም እና የእግዚአብሔርን ቃል መስማት አለብን።

### ጥያቄ

1. ኤርምያስ ማለት ትርጉሙ ምን ማለት ነው? ——————————-
2. በማሕፀን ሳለ የተቀደሰው ነቢይ ማን ይባላል? ——————————-
3. ኤርምያስ ከተጣለበት ጉድጓድ ያወጣው ማን ይባላል ? ——————————-

### መዝሙር፡-

ቃልህን ሰምቼ ሕይወትን እንዳገኝ
ማስተዋል እና ጥበብን ስጠኝ

www.zeorthodox.org

# ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ

## አርባኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ሕፃናት የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እና መልካም ማድረግን ከኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ተምረው በመምህሩ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- ***"እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ሰዎች መልካም እናድርግ፡፡"*** ገላ. ፮ ፥ ፲

**ምንባብ፡-**

- ኤር ፴፰፥፯-፲፫፤ ፴፱፥፲፭-፲፰

## መግቢያ

- ስለ ነቢዩ ኤርምያስ የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ? አቤሜሌክ ማን ነው? የት ይኖር ነበር?
- አዎን አቤሜሌክ በኢየሩሳሌም ቤተመንግሥት የሚኖር ሰው ነበር፡፡ ልጆች ዛሬ ደግሞ ስለ አቤሜሌክ በሰፊው እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

- ከብዙ ዓመታት በፊት ሴዴቅያስ የተባለ ንጉሥ በኢየሩሳሌም ነበረ፡፡ አቤሜሌክ የተባለ ሰውም በኢየሩሳሌም የሚኖር የንጉሥ አገልጋይ ነበር፡፡
- ይህ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ ቃሉንም የሚያዳምጥ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን በቤተ መንግሥት ሆኖ ነቢዩ ኤርምያስ በእስር መጣሉን ሰማ፡፡ ወዲያውም ንጉሡን አስፈቅዶ ከንጉሡ ቤትም ጨርቅ ወስዶ ነቢዩ ኤርምያስ ወደ ተጣለበት ጉድጓድ ሄደ፡፡
- ጨርቁን ለነቢዩ ወደ ጉድጓድ ጣለለት እና ይህንን አሮጌውን ልብስ ከገመዱ በታች በብብትህ አድርግ አለው ፡፡ በገመዱም ጎተተው አወጡት፡፡ ኤርምያስም ከሞት ተረፈ እና በግዞት አደባባይ ተቀመጠ፡፡
- ነቢዩ ኤርምያስ በግዞት አደባባይ ከቆየ ከቀናት በኋላ እግዚአብሔር ኤርምያስን ***"ሂድ ለኢትዮጵያዊው ለአቤሜሌክ እንዲህ በለው፤ አድንሃለሁ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ***

www.zeorthodox.org

*አልሰጥህም፡፡ ፈጽሜ አድንሃለሁ ነፍስህም እንደምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይፍ አትወድቅም በእኔ ታምነሃልና ...፡፡"* ኤር. ፴፱ ፥ ፲፮-፲፰

- በዚህ ቃል መሠረት ናቡከደነፆር የተባለው የባቢሎን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ወረረ፡፡ ሕዝቡ ሁሉ ተማረኩ፡፡ በዚያም ነቢዩ ኤርምያስ አቤሜሌክን በለስ አምጣልኝ ብሎ ላከው፡፡ አቤሜሌክ በተላከው መሠረት ሲሄድ በመንገድ ላይ እንቅልፍ ይዞት ተኛ፤ በዚህ ምክንያትም የምርኮውን ሰዓት አለፈ፡፡
- አያችሁ ልጆች እግዚአብሔር መልካም የሆነውን የልባችንን ፍላጎት ያውቃል፣ ሳንነግረውም ይፈጽምልናል፡፡

## ተግባር

- ለሰው ሁሉ በጎነት እና ሐዘኔታ ሊኖረን ይገባል፡፡

## *ጥያቄ*

1. አቤሜሌክ የየት አገር ሰው ነበር? ___________________
2. እግዚአብሔር ነቢዩ ኤርምያስን ወደ አቤሜሌክ ልኮ ምን አለው? ___________________
3. ነቢዩ ኤርምያስ አቤሜሌክን ምን እንዲያመጣለት ነበር የላከው? ___________________
4. አቤሜሌክ የተላከውን ለማምጣት ሲሄድ ምን ሆነ? ___________________
5. እግዚአብሔር አቤሜሌክን እንቅልፍ ይዞት እንዲተኛ ያደረገው ለምንድነው? __________

## *መዝሙር፡-*

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው

የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው አምላኬ መመኪያዬ ነው

www.zeorthodox.org

# የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት

## አርባ አንደኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ ፡-

- ልጆች የንጉሥ ሰሎሞን ታሪክና ጸሎት ተገንዝበው፤ መጸለይ ስለሚገባቸው ጸሎት ለይተው ያውቃሉ፤ በመምህሩ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

### መግቢያ

- ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ለጸሎት ስትቆሙ ምን ብላችሁ ትጸልያላችሁ?
- በዛሬው ትምህርታችን እግዚአብሔር ስለወደደለት የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት እንማራለን፡፡

### የሚጠና ጥቅስ፡-

- ***"ጥበብንና እውቀትን ስጠኝ"*** ፪ኛ ዜና. ፩፥፲

## የትምህርቱ ዋና ይዘት

- ንጉሥ ዳዊት ከሞተ በኋላ በእስራኤል ላይ ለንጉሥነት የተሾመው ልጁ ሰሎሞን ነው፡፡
- የዳዊት ልጅ ሰሎሞን እንደነገሠ አንድ ሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ፣ እግዚአብሔርንም አመሰገነ፡፡
- በዚያው ሌሊት እግዚአብሔር ተገልጦ ‹‹ምን እንድሰጥህ ለምነኝ›› ሲል ለሰሎሞን ተገለጠለት፡፡
- ልጆች፤ ንጉሥ ሰሎሞን  ምን ብሎ የሚለምን ይመስላችኋል?፤ እናንተስ ምን ልስጥህ ተብላችሁ ብትጠየቁ ምን ትለምናላችሁ ?
- ሰሎሞን ግን በመጀመሪያ ስላደረገለት ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ከዚያም በታላቅ ሕዝብ ላይ ስለተሾመ ፍርድ እና ማስተዋል ስለሚጠበቅበት እግዚአብሔርን፤ ***"ጥበብንና ዕውቀትን ስጠኝ"*** አለው ፡፡
- ሰሎሞን የጠየቀው ሌሎች ነገሥታት የሚጠይቁትን ክብር፣ባለጠግነት፣እድሜ…… ሳይሆን የተሰጠውን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለውን ***ጥበብንና ዕውቀትን*** ስለጠየቀ እግዚአብሔር ተደሰተበት፡፡ " ***ጥበብንና ዕውቀትን ሰጥቼሃለሁ*** " አለው፡፡ አያችሁ ልጆች ! እግዚአብሔር የለመነውን መልካም ነገር ሁሉ ይሰጠናል ፡፡
- ከጠየቅነውም በላይ ያደርግልናል ፣ ለዚህም ነው ለሰሎሞን ‹‹***አንድ ስንኳ የሚመስልህ እንዳይኖር ባለጠግነትንና ሀብትን ክብርንም እሰጥሃለሁ***›› ያለው፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- በእግዚአብሔር ፊት ስንቆም ስለምንጸልየው ጸሎት ማወቅ አለብን፡፡ ልጆች እናንተ አሁን ሥራችሁ መማር እና የታዘዛችሁትን መፈጸም ነው፡፡
- በዚህ መሠረትም ትምህርታችሁን እንዲገልጥላችሁ እግዚአብሔርን ለምኑት እርሱም ዕውቀትንና ማስተዋልን ይሰጣችሁዋል፡፡

## ጥያቄ

1. የእስራኤል ንጉሥ የነበረው የንጉሥ ሰሎሞን አባት ማን ነው? ——————————-
2. ንጉሥ ሰሎሞን እግዚአብሔርን የለመነው ምን ብሎ ነው? ——————————-
3. እግዚአብሔር ንጉሥ ሰሎሞንን ምን አለው? ——————————-

www.zeorthodox.org

# የጌታችን ልደት

## አርባ ሁለተኛ ሳምንት

**ዓላማ:-**

- ልጆች ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ አውቀው፤ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ :-**

- ***" አማኑኤል - እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው።"*** **ማቴ. ፩፥፳፫**

**ምንባብ :-**

- ማቴ.፩ እና ፪ ፤ ሉቃስ ወንጌል ፩ እና ፪

## መግቢያ:-

- ያለፈውን ትምህርት መከለስ ።
- መምህር የጌታችንን የልደት ሥዕል ለልጆቹ ያሳዩአቸውና ስለሥዕሉን ልጆቹ እንዲያስረዱ ያድርጉ።

## የትምህርት ይዘት:-

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከአበሠራት በኂላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፀነሰች።
- ከዚያም ወደ አክስቷ ኤልሳቤጥ ሄደች፤ የእግዚአብሔርንም ሥራ ተነጋግረው አመሠገኑት።
- የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስም በሀገሩ መንግሥት ሕዝቡ እንዲቆጠር ዓዋጅ ወጥቶ ነበር። በሕዝብ ቆጠራው ምክንያትም ቅዱስ ዮሴፍ እመቤታችንን ይዞ ለመቆጠር ወደ ቤተልሔም ሄደ።
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የመውለጃዋ ቀን ስለደረሰ ጻድቁ ዮሴፍ ለሕዝብ ቆጠራው በሄዱበት ቤተልሔም ማደሪያ ቢፈልግ አላገኘም። በመጨረሻም በከብቶች በረት አረፉ። በዚያም እመቤታችን ቅድስት ድንገል ማርያም ጌታችንን ወለደችው፤ በግርግምም አስተኛችው።
- ልጆች ጌታችን የተወለደው በቤተልሔም በሚገኝ የከብቶች በረት ነው። በግ፣ በሬ፣ ላም……ብርዱን ለመከላከል ትንፋሻቸውን በመስጠት አሙቀውታል።

www.zeorthodox.org

- በጎች በአአ …ላሞች እንቧ….እያሉ ሲጮሁ፤ጌታችን ተወልዶ ካለ ፍርሃት ተኝቶ ነበር፡፡እናቱም በጨርቅ ጠቅልላ አስተኛችው፡፡

## ማጠቃለያ

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ሊመስለን ስለመጣና መልካም መሆንን በትኅትና ስለ አሳየን እንወደዋለን እንከተለዋለንም፡፡

## ተግባር:-

### ወላጆች

- ከመጽሐፍ ቅዱስ ሉቃ.፪፥፩-፯ እና ማቴ. ፩፥ ፲፰-፳፫ ያንብቡላቸው፡፡
- ለቅዳሴ /ለበዓል/ ቤተ ክርስቲያን ሲወስዱዋቸው የልደትን ሥዕል እንዲያዩት እና እንዲሳለሙ ያድርጉ፡፡

### መምህር

- ልጆች የጌታችንን ፣ የእመቤታችንን እና የቅዱስ ዮሴፍን ሥዕል እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡
- የሚጠናውን ጥቅስ በእየተራ እየተነሱ በቃላቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- በክፍል በድራማ መልክ ይሳተፉ፡፡

## ጥያቄዎች:-

1. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትወልድ ያበሠራት መልአክ ማን ይባላል? ____________________-
2. እመቤታችን ጌታችንን ከፀነሰች በኋላ የሄደችባት አክስቷ ማን ትባላለችች? __________
3. እመቤታችን ጌታችንን የወለደችው የት ነው? በምን ውስጥ? ____________________-

www.zeorthodox.org

# መላእክት እና እረኞች

## አርባ ሦስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-**

- ልጆች ቅዱሳን መላእክት ጌታችን ሲወለድ ያደረጉትን አውቀው፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**ምንባብ፡-**

- ሉቃ.፪፤፲-፲፩

## መግቢያ

- መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው፡፡ ስለኛ ይጸልያሉ ፣ በብዙ መንገድ ይረዱናል፡፡ ዛሬ ለኛ /ለሰው ልጆች በሙሉ / መልካም ዜና ያበሠሩባቸውን እንማራለን፡፡
- **መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል** የሰው ልጆች ድኅነት ሲታወጅ የተላከ መላአክ ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትፀንስና እንደምትወልደው አብሥሯታል፡፡
- በመጀመሪያ ገና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ መላእክት ለእረኞች የክርስቶስን መወለድ አብሥረዋቸዋል፡፡ መልአኩ እንዲህ ነበር ያላቸው፡- ***"ዛሬ ለዓለም ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምስራች እነግራችኋለሁ፡፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት የሚሆን ጌታ ክርስቶስ ተወልዶላችኋልና አትፍሩ፡፡"***
- መልካም ዜና ሲያበሥሩንም ከእኛ ጋር ይደሰታሉ፡፡ በገና (ጌታ ሲወለድ) ***"በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድር በጎ ፈቃድ ለሰው ልጆች …"*** ሲሉ ዘምረዋል፡፡

www.zeorthodox.org

**ጥያቄዎች፡-**

1. በገና ምሽት መላእክት የዘመሩት መዝሙር ምን ነበር?
2. የጌታችንን መወለድ ያበሠረው ማነው?
3. መላእክት ምንድን ናቸው? ምን ያደርጉልናል?

***መዝሙር***

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት
ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብዕ ሃሌሉያ

# ዮሴፍ በአባቱ ቤት

## አርባ አራተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት የዮሴፍን ታሪክ አውቀው፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "እስራኤልም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር" ዘፍ. ፴፯÷፫

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ዘፍ. ፴÷፳፪- ፳፬፣ ዘፍ. ፴፯÷፩-፴፮

## መግቢያ

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት በቤተሰብ ውስጥ ተወዳጅ ልጅ ናችሁን? በምን?
- ስታድጉ እና ትልቅ ስትሆኑ ምን መሆን ትፈልጋላችሁ?
- ከወንድሞቻችሁ እና ከእኅቶቻችሁ ጋር ትዋደዳላችሁ? ትጣላላችሁ እና ቀንታችሁስ ታውቃላችሁ? የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለመምህሩ እና ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ያዕቆብ ሁለት ሚስቶች ነበሩት፡፡ የመጀመሪያዋ ልያ የምትባል ስትሆን ከእርሷ ብዙ ልጆችን ወለደ፡፡ ሁለተኛ ሚስቱ ራሔል ግን መካን ስለነበረች ለብዙ ዘመናት ልጅ ሳትወልድ ኖረች፡፡ ራሔል ‹‹ልጅ የሌላት! ልጅ መውለድ የማትችል!›› እየተባለች ትሰደብ ነበር፡፡ ይህን ስድቧን እንዲያርቅና ልጅ እንዲሰጣት እግዚአብሔርን አብዝታ በለመነች ጊዜ እግዚአብሔር የራሔልን ልመና ሰማ፡፡ እግዚአብሔር ራሔን አሰባት፣ ተለመናት፣ ማሕፀኗንም ከፈተላት፡፡ ራሔል ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች፡፡ እግዚአብሔር ሁለተኛ ወንድ ልጅን ይጨምርልኝ ስትል የልጇን ስም ‹‹ዮሴፍ›› ብላ ጠራችው፡፡ ራሔል ሞተች፣ ወደ ኤፍራታ በምትወስደው መንገድ በቤተልሔም ተቀበረች፡፡
- ያዕቆብ ዮሴፍን በሽምግልናው ዘመን የወለደው ልጁ ስለነበር እና እናቱ ስለሞተችበት እንዲሁም መልካም ጠባይ እና ሥነ-ምግባር ስለነበረው ዮሴፍን ከሌሎቹ ልጆች አብልጦ ይወደው ነበር፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች አባታቸው ያዕቆብ ዮሴፍን ከእነርሱ

www.zeorthodox.org

አብልጦ እንደሚወደው እና ሕልመኛ ስለሆነ ቀንተውበት ነበር፡፡ ስለዚህ ዮሴፍን ጠልተውት ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች በሃያ ብር ሸጡት፡፡ ነጋዴዎቹም ዮሴፍን ወደ ግብጽ ሀገር ወሰዱት፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች በውሸት ለአባታቸው ለያዕቆብ ዮሴፍን አውሬ በላው ብለውነገሩት፡፡ ሽማግሌው አባታቸውም የምወደው ልጄ ዮሴፍ ሞተ ብሎ በሐዘን አለቀሰ፡፡ ያዕቆብም ዮሴፍን በጣም ይወደው ስለነበር ከባድ ሐዘን ሆነበት፡፡

## ማጠቃለያ

- ዮሴፍን አባቱ ያዕቆብ በጣም ይወደው ነበር፡፡ ዮሴፍን ከወንድሞቹ በላይ በአባቱ ተወዳጅ ልጅ ያደረገው መልካም ጠባዩ፣ ታማኝነቱ እና መታዘዙ ነበር፡፡ ዮሴፍ የአባቱን ምክር የሚሰማ እና የሚታዘዝ ስለነበር ምንም እንኳን ወንድሞቹን ቢወዳቸውም በክፉ ሥራቸው ግን አይተባበራቸውም ነበር፡፡ ለአባቱ ታማኝ ስለነበር የወንድሞቹን ክፉ ሥራ እየተናገረ በአባታቸው ምክር እንዲስተካከሉ ጥሩ ሰው እንዲሆኑ ያደርግ ነበር፡፡ ሕፃናት እናንተም የወላጆቻችሁን ምክር በመስማትና ለእነርሱ በመታዘዝ ለቤተሰቦቻችሁ ተወዳጅ ልጆች መሆን ትችላላችሁ፡፡ የቤተሰባቸውን ምክር ከማይሰሙና ከማይታዘዙ ልጆች ጋር በክፉ ሥራዎቻቸው መተባበር የለባችሁም፡፡ እንደ ዮሴፍ ክፉ ነገር የሚያደርጉትን ጥፋታቸውን ሳትደብቁላቸው ከስሕተታቸው እንዲማሩ ለወላጆች መናገርን ልመዱ፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. የዮሴፍ እናት ማን ትባላለች?
2. ዮሴፍን ተመራጭና ተወዳጅ ልጅ ያደረገው ምን ነበር?
3. ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ የቀኑበት ለምንድን ነው?
4. ዮሴፍን ወንድሞቹ በስንት ብር ሸጡት?
5. ዮሴፍን የገዙት ነጋዴዎች ዮሴፍን ወደ የት ሀገር ወሰዱት?

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህር ሕፃናት ወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልጉ በዝርዝር እንዲናገሩ ይጋብዙዋቸው፡፡
- ሕፃናት ከቤተሰባቸው ምንም የሚደብቁት ነገር መኖር እንደሌለበት እና በውሸት ቤተሰባቸውን እንዳያሳዝኑ መመህሩ በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡
- ሕፃናት በመጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉዋቸው፡፡

# ሳሙኤል በእግዚአብሔር ተጠራ

## አርባ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ሕፃናት ከሳሙኤል ታሪክ እግዚአብሔር ለተለያየ ዓላማ እንዲሁም አገልግሎት ሰዎችን እንደሚመርጥ ያውቃሉ፡፡ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- "ባሪያህ ይሰማልና ተናገር" ፩ ሳሙ. ፫÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

- ፩ሳሙ. ፩÷፫፣ ፩ጴጥ. ፪÷፱-፲

**መግቢያ**

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ልጆች የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንደሚፈልጋችሁ ተረድታችኋል?
- እግዚአብሔርን በምን እና እንዴት ለማገልገል ትፈልጋላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

- ሳሙኤል የኤፍሬማዊው የሕልቃና እና መካን የነበረችው የሐና ልጅ ነው፡፡ ሐና ለብዙ ዘመናት ልጅ አልነበራትም፡፡ መካን በመሆኗም ብዙ ስድብና ነቀፋ ይደርስባት ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ሐና እግዚአብሔርን ልጅ እንዲሰጣት በቤተ መቅደሱ ፊት ቆማ ለመነችው፤ ስለትንም ተሳለች፡፡ እግዚአብሔር ወንድ ልጅ የሚሰጣት ከሆነ ልጁ የእግዚአብሔር አገልጋይ ይሆናል ስትል ስለት ተሳለች፡፡ እግዚአብሔር ሐናን አሰባት፣ ጸሎቷንም ሰማ፣ ወንድ ልጅም ሰጣት፡፡ እርሷም ‹‹እግዚአብሔር ልመናዬን እና ጸሎቴን ሰምቷል›› ስትል የልጇን ስም ሳሙኤል ብላ ጠራችው፡፡ ሕፃኑ ሳሙኤል እስኪጠነክር

እና ጡት እስኪተው ድረስ ከእናቱ ጋር ኖረ፡፡ የእናቱን ጡት መጥባት በተወ ጊዜ እናቱ ሐና በሴሎ ወደሚገኘው ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ወሰደችው፤ በዚያም ምስጋናዋን እና ስለቷን አቅርባለች፡፡ ልጇ ሳሙኤል በእግዚአብሔር ቤት እንዲያድግና አምላኩን እንዲያገለግል ለካህኑ ዔሊ አስረከበችው፡፡

- ካህኑ ዔሊ ብላቴናውን ሳሙኤልን በቤተ መቅደስ ያሳድገው ነበር፡፡ የዔሊ ልጆች እግዚአብሔርን የማይፈሩ ክፉዎች ነበሩ፡፡ ሳሙኤል ግን እግዚአብሔርን በመፍራት በቅንነት እና በንጽሕና እያገለገለ በቤተ መቅደስ ይኖር ነበር፡፡ አንድ ቀን ሳሙኤል የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት በመቅደሱ ተኝቶ ሳለ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው፡፡ ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ድምፅ ለይቶ ስለማያውቅ ካህኑ ዔሊ የጠራው መስሎት ወደ ዔሊ ሔደ፡፡ ካህኑ ዔሊ "ልጄ ሳሙኤል ሒድ ተኛ እኔ አልጠራሁህም" አለው፡፡ እግዚአብሔርም ሳሙኤልን ሦስት ጊዜ እየደጋገመ ጠራው፡፡ አሁንም ሳሙኤል ወደ ዔሊ ሔደ፡፡በዚህ ጊዜ ዔሊ እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንደጠራው አስተዋለ፡፡ ሳሙኤልንም "ሄደህ ተኛ ቢጠራህም አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው" አለው፡፡ ሳሙኤል እንደገና ተኛ፤ እግዚአብሔርም እንደ መጀመሪያው ‹‹ሳሙኤል ሳሙኤል›› ብሎ ጠራው፡፡ ሳሙኤል ዔሊ እንደነገረው አደረገ፡፡ እግዚአብሔርም ለሳሙኤል በእስራኤል እና በዔሊ ልጆች ላይ የሚያደርገውን ነገረው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ድምፅ ለይቶ አወቀ፣ እግዚአብሔርንም በታማኝነት ያገለግል ነበር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ልጆች ብላቴናው ሳሙኤል የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት መቅደስ የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደሰማ ለአገልግሎትም እንደተጠራ ተምራችኋል፡፡ እናንተንም እንደ ሳሙኤል ለተለያየ አገልግሎት እግዚአብሔር ሊመርጣችሁ ስለሚፈልጋችሁ በቤተ ክርስቲያን ድምፁን እየሰማችሁ እደጉ፡፡

www.zeorthodox.org

### ጥያቄዎች፡-

1. ሳሙኤል የማን ልጅ ነው? ሳሙኤል ማለት የስሙ ትርጓሜ ምን ማለት ነው?
2. የሐና ስለት ምን ነበር? ሳሙኤል በቤተ መቅደስ ያሳደገው ካህን ማን ይባላል?
3. ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ድምፅ የት ሆኖ ሰማ?

## ተግባር፡-

- መምህር ሕፃናት ስለ ስለት፣ በእግዚአብሔር ስለመመረጥ እና በቤተ ክርስቲያን ስለማደግ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በምሳሌ ትምህርቱን ያብራሩላቸው፡፡
- ሕፃናትን እንደ ዔሊ በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል እየነገረ የሚያሳድጋቸው አባት እንደሚያስፈልጋቸው፣ አባቶች ካህናትን እንዲወዱ፤ ሃይማኖታቸውን እንዲያውቁ፤ የእግዚአብሔርን ቃልና ትዕዛዝ እንዲገነዘቡ፤ ሳያፍሩ እና ሳይፈሩ ጥያቄ እንዲጠይቁ ይንገሩዋቸው፡፡ ያበረታቱአቸው፡፡
- በመጽሐፉ ላይ ሕፃኑ ሳሙኤል በእግዚአብሔር ሲጠራ የሚያሳየውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉዋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዮሴፍ ወደ ግብፅ ወረደ

## አርባ ስድስተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ልጆች ዮሴፍ በእግዚአብሔር ታምኖ በፈተና እንደጸና ይገነዘባሉ፤ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፋውን አልፈራም፡፡" መዝ. ፳፱(፳፫)÷፬

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ዘፍ.፴፯÷፳፫ -፴፮፣ ዘፍ. ፴፰-፴፱

### መግቢያ፡-

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናትን ምን እንደሚያስፈራቸው ይጠይቋቸው፡፡
- ሕፃናት ከእነርሱ አቅም በላይ የሆነ ነገር ሲገጥማቸው ምን እንደሚያደርጉ ያወያዩአቸው

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ልጆች ያለፈውን ሳምንት ትምህርታችንን ታስታውሳላችሁ፡፡ ዮሴፍ መልካም ጠባይ እና ሥነ-ምግባር ያለው ልጅ ነበር፡፡ አባቱ ያዕቆብ ከሌሎቹ ልጆች በላይ አብልጦ ይወደው ነበር፡፡ በዚህም ወንድሞቹ ቀንተው በሃያ ብር ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች እንደሸጡት ተምረናል፡፡ እስማኤላውያን ዮሴፍን ወደ ግብጽ ሀገር ወሰዱት፡፡
- በግብጽ ለፈርዖን የዘበኞች አለቃ ጲጥፋራ ለሚባለው ባርያ ሆኖ እንዲያገለግል ሸጡት፡፡ ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ውስጥ በቅንነት እና በታማኝነት ያገለግል ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ስለነበር ሥራው ሁሉ መልካም የተሳካ እንዲሆንለት አደረገው፡፡ ጲጥፋራ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንደሆነ ስለተገነዘበ ዮሴፍን በቤቱ ላይ ሐላፊ አድርጎ ሾመው፡፡
- ከዚህ በኋላ የዮሴፍ አምላክ እግዚአብሔር የጲጥፋራን ቤት ባረከ፡፡ የእግዚአብሔርም

www.zeorthodox.org

በረከት በውስጥም በውጪም ሆነ፡፡ ነገር ግን የጲጥፋራ ሚስት በሐሰት ዮሴፍን ስለ ከሰሰችው ዮሴፍ ታሰረ፡፡

- እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበር በእስር ቤት ውስጥ ሞገስን ሰጠው፤ ሕልም የመፍታት ጥበብንም ጨመረለት፡፡ ዮሴፍ የእስር ቤቱ አለቃ ሆነ፤ ለእስረኞቹም ሕልማቸውን ይፈታና ይተረጉምላቸው ነበር፡፡ በመጨረሻም የግብጽ ንጉሥ የፈርዖንን ሕልም መፍታትና መተርጎም ስለቻለ ፈርዖን ከእስር ቤት አውጥቶ በግብጽ ምድር ሁሉ ላይ አለቃና ገዢ አደረገው፡፡

## ማጠቃለያ

- ዮሴፍ በቅናት የተነሣሱበት ወንድሞቹ ከሸጡት ጀምሮ ብዙ ችግሮች ተራ በተራ ደርሰውበታል፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር በእምነትና በትዕግሥት እንዴት እንዳለፈ ተምራችኋል፡፡
- ዮሴፍ በእምነቱ ጸንቶ የደረሰበትን ችግርና ፈተና ሁሉ በታማኝነት እና በትዕግሥት በማለፉ እግዚአብሔር በብዙ ባርኮታል፡፡
- ስለዚህ ሕፃናት ዕለት ዕለት የሚገጥሟችሁን ችግሮች ማለፍ እንድትችሉ በእግዚአብሔር ታመኑ፣ በፈተና ጽኑ፣ ታገሱ፡፡ እግዚአብሔር እንደ ዮሴፍ ያሳድጋችኋል፤ በብዙ በረከትም ይባርካችኋል፡፡

**ጥያቄ፡-**

1. ዮሴፍን ወንድሞቹ በሃያ ብር የሰጡት ለማን ነው?
2. ነጋዴዎቹ ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወስደው ለማን ሸጡት?
3. የዘበኞች አለቃ ዮሴፍን በቤቱ ላይ የሾመበት ምክንያት ምን ነበር?
4. ዮሴፍ በእስር ቤት የታሰረበት ምክንያት ምንድነው?
5. ዮሴፍ እንዴት ከእስር ቤት ሊወጣ ቻለ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህር ልጆች ማንንም በሐሰት መክሰስ እንደሌለባቸው ይምከሯቸው፡፡ የሐሰት ምስክርነትን እግዚአብሔር እንደማይወድ አጽንኦት ሰጥተው በምሳሌ ያስረዱአቸው፡፡
- በመጽሐፍ ላይ ያለውን የዮሴፍን እና የነጋዴዎቹን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉቸው፡፡

# በገና ደርዳሪው ዳዊት

## አርባ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ሕፃናቱ ከዳዊት ታሪክ እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- "የእግዚአብሔርም መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ፡፡" ፩ሳሙ. ፲፮÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**

- ፩ሳሙ. ፲፮ ÷ ፩÷፲፫

## መግቢያ

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- መምህሩ የሚቻል ከሆነ በገና ካልተቻለ የበገና ቪዲዮ ፊልም አምጥተው ለሕፃናት ያሳዩአቸው፡፡ ሕፃናቱ ምን ዓይነት ችሎታ እና ጸጋ እንዳላቸው? ወደፊት እንዴት ሊጠቀሙበት እንዳሰቡ ይጠይታቋቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

- በይሁዳ ቤተልሔም የሚኖር የነበረ እሴይ የሚባል ሰው ነበር፡፡ እሴይ ብዙ ልጆች ነበሩት፡፡ ከእሴይ ልጆች መካከል የሁሉም ታናሽ የሆነው ዳዊት ነው፡፡ ዳዊት የአባቱን በጎች በመጠበቅ በእረኝነት ቤተሰቡን እያገለገለ የልጅነት ዘመኑን አሳለፈ፡፡ ዳዊት መልኩ ያማረ ልጅ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ከዳዊት ጋር ነበር፡፡ በሥራው ታታሪ፣ ጽኑ እና ኃያል እንዲሁም ብልኅ ልጅ ነበር፡፡ በአባቱ በእሴይ እና በቤተሰቡ ሁሉ ተወዳጅ ልጅ ነበር፡፡ ዳዊት በገና መምታት ይችላል፡፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡፡ ‹‹በቤተልሔም ወደ እሴይ ሒድ በልጆቹ መካከል ንጉሥ አዘጋጅቻለሁ›› አለው፡፡ ሳሙኤል ይህን ሲሰማ በጣም ደነገጠ ፈራ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር "የምታደርገውን አስታውቅሃለው የምነግርህንም ቅባልኝ" ሲል ደግሞ ተናገረው፡፡
- ሳሙኤል እግዚአብሔር እንደተናገረው አደረገ፡፡ ወደ ቤተልሔም መጣ እሴይንና ልጆቹን አገኛቸው፡፡ እግዚአብሔርም ዳዊትን እንዲቀባ ለሳሙኤል ነገረው፤ ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ዳዊትን ቀባው፡፡ በዚያን ዘመን የእስራኤል

www.zeorthodox.org

ንጉሥ የነበረው ሳኦል የእግዚአብሔር መንፈስ ርቆት ስለነበር በክፉ መንፈስ ይሰቃይና ይጨነቅ ነበር፡፡ የንጉሥ ሳኦል ወታደሮች መልካም አድርጎ በገና የሚመታ ሰው መፈለግ ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ መልካም አድርጎ በገና መምታት የሚችለው የእሴይ ልጅ ዳዊት ነበር፡፡ ዳዊት በገናውን ሲመታ ንጉሥ ሳኦል ከሚያሰቃየው ክፉ መንፈስ ደኅና እንደሚሆን ወታደሮቹ ለንጉሡ ነገሩት፡፡ ንጉሥ ሳኦል ወደ አባቱ ወደ እሴይ ወታደሮቹን ልኮ ዳዊትን አስጠራው፡፡ ዳዊት ወደ ሳኦል መጥቶ በንጉሡ ፊት ቆመ፡፡ ንጉሡ ሳኦል  እጅግ ወደደው፤ ታማኝ አገልጋዩ ሆነ፡፡ ንጉሥ ሳኦል በክፉ መንፈስ ሲጨነቅ ዳዊት በገናውን እየመታ፣ ሳኦልንም ደስ ያሰኘውና ያሳርፈው ነበር፡፡ ክፉው መንፈስም ከንጉሡ እርቆ ይሄድ ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

- ዳዊት በቅንነት እና በታማኝነት የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር፡፡ ቤተሰቡንም በትሕትና እና በቅንነት ያገለግል ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በማገልገሉ እንዴት ለትልቅ ኃላፊነት እንደመረጠው፣ ጸጋውንም እንዳበዛለት ተገንዝባችኋል፡፡ ዳዊት እግዚአብሔር የሰጠውንም ጸጋ ሌሎችን ደስ ለማሰኘት እና ለማሳረፍ እንደተጠቀመበት ተምራችኋል፡፡ ልጆች ቤተሰቦቻችሁን በቅንነትና በታማኝነት ስታገለግሉ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወደ እናንተ ይመጣል፤ ለትልቅ አገልግሎትም ይመርጣችኋል፡፡ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችንም ይሰጣችኋል፡፡ ስለዚህ ልጆች እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ጸጋ እና ችሎታ ሌሎችን ለማስደሰት፣ ለመርዳት እና ለማገልገል ተጠቀሙበት፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ዳዊት የማን ልጅ ነው? ዳዊት የልጅነት ጊዜውን እንዴት ነበር ያሳለፈው?
2. ዳዊት ምን ዓይነት ተሰጥኦ ነበረው? ዳዊትን የቀባው ሰው ማን ይባላል?
3. በክፉ መንፈስ ይጨነቅና ይሰቃይ የነበረው ንጉሥ ማን ነው? ከዳዊት ምን ተማራችሁ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህር በቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን የዜማ ዕቃዎች ከነ አገልግሎታቸው ለሕፃናት በሥዕል የተደገፈ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ሕፃናት ለጓደኞቻቸው እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋ እና ተሰጥኦ እንዲያካፍሉ አድርጉዋቸው፡፡
- በመጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡና የሚያውቁትን የዜማ ዕቃ እንዲሥሉ አድርጉዋቸው፡፡

# አቡነ አረጋዊ

## አርባ ስምንተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት የአቡነ አረጋዊን ታሪክ አውቀው የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "ጻድቅ በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል" መዝ. ፷፫(፷፬)÷፲፤

### ተጨማሪ ምንባብ፡-

- ገድለ አቡነ አረጋዊ፡፡

## መግቢያ

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ለሕፃናት የአቡነ አረጋዊን ምስል ያሳዩአቸው፡፡
- ሕፃናት ሊረዱት በሚችሉት አገላለጽ ስለ ቅዱሳን ሕይወት ይንገሩአቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

- አቡነ አረጋዊ ከአባታቸው ይስሐቅ እና ከእናታቸው አድና በሮም ሀገር ተወለዱ፡፡ የመጀመሪያ ስማቸው ዘሚካኤል ይባላል፡፡ በዘመኑ የነበረውን መንፈሳዊ ትምህርት እየተማሩ አደጉ፡፡ ዕድሜያቸው አሥራ አራት ዓመት ሲሞላ ቤተሰቦቻቸው ከነገሥታት ቤተሰብ ሚስት አጩላቸው፡፡
- ነገር ግን አቡነ አረጋዊ ይህን ሲሰሙ ወደ ድርጌ (ግሪክ) ሀገር ኮበለሉ፡፡፡ ዻውናስ የሚባል ገዳም ገብተው መነኮሱ፡፡ አቡነ አረጋዊ እጅግ በጣም መንፈሳዊ ሰው ነበሩ፡፡ በሕይወታቸው እና ለመንፈሳዊ ሕይወት በነበራቸው ብዙዎችን ቅንዓት ወደ እግዚአብሔር መልሰዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ስማቸው አቡነ አረጋዊ ተባለ፡፡
- ከዚህ በኋላ እናታቸው ንግሥት አድና ዜናቸውን ሰምታ አቡነ አረጋዊን ልትይጠይቃቸው ወደ አሉበት መጣች፡፡ ‹‹እናቴ ስለምን መጣሽ?›› ሲሉ ጠየቋት፡፡ እናታቸውም እርሳቸው የናቁትን ዓለም ንቃ እንደመጣች ነገረቻቸው፡፡

www.zeorthodox.org

- አቡነ አረጋዊ በእናታቸው ውሳኔ በጣም ተደስተው፤ እናታቸው የምንኵስና ማዕረግ እንዲቀበሉ እና በሴቶች ገዳም እንዲኖሩ አደረጉአቸው፡፡
- ከሰባት ዓመት በኋላ ወደ ሮም ተመልሰው ሲያስተምሩ የሀገራችንን የኢትዮጵያን ዜና ሰምተው ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡
- በብዙ ቦታዎች እያስተማሩና ሕሙማንን እየፈወሱ ደብረ ዳሞ የሚባል ስፍራ ደረሱ፡፡ ነገር ግን መውጫ የሌለው ረዥም ተራራ ስለነበር "አሁን ይህን ተራራ በምን ልወጣው እችላለሁ?" እያሉ ሲጨነቁ እግዚአብሔር ዘንዶ ተሸክሞ እንዲያወጣቸው አደረገ፡፡
- ከዚህ በኋላ እግዚአብሔርን እያገለገሉ በጸሎትና በጾም ኖሩ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጦላቸው፤ ሰማያዊ መንግሥትን እንደሚያወርሳቸው፣ በእርሳቸው አማላጅነት ለሚታመኑም የእርሳቸውን ጸጋ እና በረከት እንደሚያገኙ ቃል ገባላቸው፡፡
- አቡነ አረጋዊ ደቀ መዝሙሮቻቸውን ሰብስበው ‹‹ከእንግዲህ በሥጋ አታዩኝም›› ብለው ነግረዋቸው ተሰወሩ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ሕፃናት አቡነ አረጋዊ በእግዚአብሔር ደስተኛ ሆነው ዘመናቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንደሰጡ እና እንዳገለገሉት እናንተም እግዚአብሔርን በፍቅር እና በቅንነት ማገልገልን ልመዱ፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. አቡነ አረጋዊ የማን ልጅ ናቸው?
2. የት ሀገር ተወለዱ?
3. ወደ ገዳም የሔዱበት ምክንያት ምን ነበር?
4. ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ሊመጡ ቻሉ?
5. ደብረ ዳሞ ተራራ ላይ እንዴት ወጡ?
6. ከአቡነ አረጋዊ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህር ደብረ ዳሞ ገዳም የት እንደሚገኝ በቪዲዮ እና በካርታ የተደገፈ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ሕፃናት የአቡነ አረጋዊን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ይንገሩአቸው፡፡

# እምነትሽ አድኖሻል

## አርባ ዘጠነኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ከሕመሟ የተፈወሰችውን ሴት ታሪክ በመገንዘብ በእምነት መዳን እንደሚቻል ያውቃው፤ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- "ልጄ ሆይ እምነትሽ አድኖሻል በሰላም ሂጂ ከስቃይሽም ተፈወሽ" ማር. ፭÷፳፭-፴፬

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ማር. ፭÷፳፭-፴፬ ማቴ. ፱÷፳-፳፫፣ ሉቃስ ፰÷ ፵፫-፵፰

## መግቢያ

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት ታማችሁ ታውቃላችሁ ስትታመሙ የሚሰማችሁ ስሜት ምንድን ነው?
- ሕፃናት ስትታመሙ የምትፈልጉት ነገር ምንድን ነው? ቤተሰቦቻችሁ ምን ያደርጉላችኋል?

## የሳምንቱ ትምህርት

- ከዐሥራ ሁለት ዓመቷ ጀምሮ ደም ያለማቋረጥ የሚፈሳት ሴት ነበረች፡፡ በጣም ትታመም ስለነበር ከሕመሟ ለመዳን ከብዙ ባለመድኃኒቶች ዘንድ እየሄደች መድኃኒት ለማግኘት ደከመች፡፡ ብዙ ተሰቃየች፡፡ ነገር ግን ሕመሟ ባሰባት እንጂ ምንም አልተጠቀመችም፡፡
- ገንዘቧን ሁሉ ለብዙ ባለመድኃኒተኞች ከፍላ መዳን አልቻለችም፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው፤ ‹‹የናዝሬቱ ኢየሱስ ሕሙማንን ያድናል በነፃ ይፈውሳል›› ሲል ነገራት፡፡ የኢየሱስን ወሬ ከሰማች በኋላ አንድ ቀን በእርሷ መንደር ሲያልፍ በሰዎች መካከል ‹‹ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደሆነ እድናለሁ›› ብላ አመነች፡፡
- ሴቲቱ የኢየሱስን ልብስ በዳሰሰች ጊዜ ወዲያውኑ የሚፈስሰው ደምዋ ደረቀ፣ ከሥቃይዋም ዳነች፡፡ ወዲያውም ኢየሱስ "ማን ነው የነካኝ?" ሲል ደቀ መዛሙርቱን ጠየቀ፡፡ ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ማን እንደነካው አላወቁም፡፡ በዚህ ጊዜ ሴቲቱ የተደረገላትን ስላወቀች ወደ ኢየሱስ መጣችና በፊቱ ተደፍታ ሰገደችለት፡፡ እውነቱንም ሁሉ ነገረችው፡፡ሴቲቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ከባረካት በኋላ እግዚአብሔርን እያመሰገነች ወደ ቤቷ ድና ሔደች፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

- ሕፃናት በሕይወታችን ውስጥ በእግዚአብሔር የሚኖረን እምነት ትልቅ ጉልበት ነው፡፡ ሴቲቱ በታመመች ጊዜ ቀድሞ በእግዚአብሔር እምነት አልነበራትም፡፡
- ብዙ ባለመድኃኒተኞች ጋር ሄደች፡፡ ያድኑኛል ብላ በማሰብ ገንዘቧን በተነች፡፡ ብዙ ደክማ፣ በስቃይ ቆይታ ገንዘቧንም አባክና መዳን አልቻለችም፡፡
- በመጨረሻው ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከሕመሟ ዳነች፣ የደሟም ምንጭ ደረቀ፡፡
- ስለዚህ ሕፃናት የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆናችሁ ስትታመሙ እግዚአብሔር እንዲምራችሁ በእምነት ሆናችሁ ጸልዩ ለሌሎችም መጸለይን ልመዱ፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ሴቲቱ ለስንት ዓመት ነበር ደም የፈሰሳት?
2. ሴቲቱን ማን አዳናት?
3. ሴቲቱ ከሕመሟ የዳነቸችው ምን ስላደረገች ነው?

## ተግባር፡-

- መምህር ሕፃናት ጤንነታቸውን እንዲንከባከቡና የሕመም ስሜት ሲሰማቸው ለቤተሰብ መናገር እንደሚገባቸው ይንገራቸው፡፡
- የጸሎትን ኃይል እና ከችግሮቻቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ባለን እምነት መዳን እንደምንችል አጽንኦት ሰጥተው ያስረዱዋቸው፡፡
- ሕፃናት ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመት ደም የፈሰሳትን ሴት ሲፈውሳት የሚያሳየውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ አድርጓቸው፡፡

www.zoorthodox.org

# የመበለቲቱ ትልቅ ስጦታ

## ሃምሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ልጆች ከመበለቲቱ ታሪክ እግዚአብሔር የሚቀበለውን በእምነትና በፍቅር የሆነ ንጹሕ ስጦታ መስጠትን አውቀው፤ በመምህሩ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- “ይህች ድሃ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች” ሉቃ. ፳፩፥፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

- ማር. ፲፪፥ ፵፩-፵፬፣ ሉቃ. ፳፩፥፩-፬

## መግቢያ

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትመጡ ስጦታ ይዛችሁ መጥታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ዓይነት ስጦታ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ከዕለታት አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መባቸውን በመዝገብ የሚጥሉ ባለጠጎችን ተመለከተ፡፡ ሕፃናት ‹‹መባ›› ማለት፤ ሰው ለአምላኩ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው ስጦታ ማለት ነው፡፡ መባቸውን በምጽዋት ሙዳዩ ውስጥ ከሚጥሉት ሰዎች መካከል አንዲቱ ድሃ መበለት ሁለት ሳንቲም በዚያ ስትጥል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አያት፡፡
- ሕፃናት ‹‹መበለት›› ማለት ባልዋ የሞተባት ወይም በማናቸውም ምክንያት ያለ ባል የምትኖር ሴት ማለት ነው፡፡
- ኢየሱስ የደሃዋን ሴት ስጦታ ከተመለከተ በኋላ ስጦታዋ በእግዚአብሔር ሚዛን እና በጌታ ዓይን ትልቅ ስለነበር “ይህች ድሃ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች” ብሎ መሰከረላት፡፡ ሌሎቹ የሰጡት በብዙ ሃብታቸው ከትርፋቸው ነበር፡፡ እርሷ ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ሁሉ ሰጠች፡፡ ይህም ስጦታዋ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ሆነላት፡፡
- ጌታ ኢየሱስም እውነኛ ስጦታ በእምነት እና ከልብ በመነጨ ፍቅር መቅረብ እንዳለበት አስተማረ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- ሕፃናት በፍቅርና በእምነት የሚቀርብ ማንኛውንም ንጹሕ ስጦታ እግዚአብሔር እንደሚቀበል ከመበለቲቱ ታሪክ ስለተማራችሁ እናንተም እንዲሁ አድርጉ፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ‹‹መባ›› ማለት ምን ማለት ነው?
2. ‹‹መበለት›› ማለት ምን ማለት ነው?
3. የመበለቲቱ ስጦታ ምን ነበር?
4. ስጦታዋን ያየው ማን ነው?
5. ስጦታውን ትልቅ ያደረገው ምን ነበር?

## ተግባር

- መምህር ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ይዘን የምንመጣቸውን መባ ዓይነቶች ለሕፃናት ይንገሩአቸው፡፡ ለምሳሌ ጧፍ፣ ሻማ፣ እጣን፣ ዘቢብ . . . ወዘተ፡፡
- መምህሩ በቤተ ክርስቲያን መግቢያ በር ላይ የሚቀመጡትን የምጽዋት ሳጥኖች አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ ለሕፃናት ይግለጹላቸው፡፡
- መምህሩ ሕፃናት በመጽሐፉ ላይ ያለውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሆሣዕና

# ሃምሳ አንደኛ ሳምንት

## የትምህርቱ ዓለማ፡-

- ሕፃናት የሆሣዕና በዓል በቤተክርስቲያን የሚከበርበትን ምክንያትና ሥርዓቱን ያውቃሉ፡፡ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

## በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- “በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው” ማር ፲፩÷፲

## ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ማር. ፲፩÷፩--፲፤ ማቴ. ፳፩÷፩-፲፩፣ መዝ. ፻፲፯(፻፲፰) ÷ ፳፭-፳፯

## መግቢያ፡-

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት የሆሣዕና በዓል ለምን እንደሚከበር ታውቃላችሁ?
- ሕፃናት የአህያ ልጅ ምን ትባላለች?
- የአህያ አገልግሎት ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እየተጓዘ ነበር፡፡ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተፋጌ ሲደርሱ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ሁለት ሰዎችን መረጠ፡፡
- ከዚያም በፊታቸው ወዳለችው መንደር ሄደው የታሰረችውን አህያ ውርንጫዋንም ፈትተው እንዲያመጡለት አዘዛቸው፡፡ በመንገድም የሚይጠይቃቸው ሰው ቢኖር ለጌታ ያስፈልጉታል እንዲሉ ነገራቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱም እንዳዘዛቸው አደረጉ፡፡ ልብሳቸውንም አውልቀው በአህያዋ ላይ አኖሩ ኢየሱስም ተቀመጠባት፡፡
- ይህን የተመለከቱ ሌሎች ሰዎች እና ብዙ ሕዝብ ልብሳቸውን፣ የዛፍ ቅርንጫፍ (የቅጠል ዝንጣፊ) እና ዘንባባ እየቆረጡ በመሬት ላይ አነጠፉ፡፡ ከፊትና ከኋላ ሆነውም “ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም” እያሉ ይዘምሩ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

- ሕፃናትም “ሆሣዕና በአርያም” እያሉ ከሕዝቡ መካከል ሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን ያመሰግኑ ነበር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ሕፃናት ቤተ ክርስቲያን የሆሣዕና በዓልን በታላቅ ድምቀት የምታከብርበትን ምክንያት ተምራችኋል፡፡
- ‹‹ሆሣዕና›› ማለት አሁን አድን ማለት ነው፡፡ እናንተም በዚህ ቀን እግዚአብሔርን በዝማሬ የምታመሰግኑበት ቀን ስለሆነ በዓሉን በደስታ እና በፍቅር አክብሩ፡፡ ለጌታ እንደምታስፈልጉ ክርስቶስም እንደሚፈልጋችሁና እንደሚወዳችሁም እወቁ፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ‹‹ሆሣዕና›› ማለት ምን ማለት ነው?
2. ቤተ ክርስቲያን በዓሉን የምታከብርበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አህያዋንና ውርንጭላዋን እንዲያመጡለት ስንት ሰው ላከ?
4. ሕዝቡ ምን እያሉ ይዘምሩ ነበር?
5. ሕፃናት ምን እያሉ ነበር ያመሰገኑት?

## ተግባር፡-

- መምህር በቪዲዮ እና በሥዕል በተደገፈ መረጃ የሆሣዕናን በዓል አከባበር ለሕፃናት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- የሆሣዕናን መዝሙር አስጠኑዋቸው እና ሕፃናቱ ይዘምሩ፡፡
- በመጽሐፉ ላይ ያለውን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ አድርጓቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የጌታ ትንሣኤ

## ሃምሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ሕፃናት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ አውቀው፤ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- "አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኲራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል"

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

- ማቴ. ፳፰፥፩-፲፫፣ ዮሐ. ፳፥፩-፲፰፣ ሉቃ. ፳፬፥፩-፲፪

## መግቢያ

- መምህር ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ሕፃናት እስካሁን ስንት ጊዜ የጌታን ትንሣኤ አክብራችኋል? በዓሉን እንዴት ነው የምታከብሩት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የትንሣኤ በዓል ከዓቢይ ጾም በኋላ በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡
- ‹‹ትንሣኤ›› ማለት ከሞት በኋላ በሥጋና በነፍስ ሕይወት ማግኘት ማለት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ሰው ሆኖ፤ በዚህ ምድር እያስተማረ፣ ሕሙማንን እየፈወሰ፣ ኖሮ ጊዜው ሲደርስ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ፡፡ እንደተናገረውም ሞትን ድል አድርጎ በሦስተኛው ቀን ተነሣ፡፡
- ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስ ክርስቶስን መቃብር ሥፍራ ሔደው ተመለከቱ፡፡ ነገር ግን የኢየሱስ መቃብር ባዶ ነበር፡፡ ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያየ ጊዜና ሥፍራ እየተገለጠ ለደቀ መዛሙርቱ ታያቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሣ አመኑ፡፡ ይህን እውነትም ይመሰክሩ

www.zeorthodox.org

ነበር፡፡ ይህን የክርስቶስን ትንሣኤ ለማስታወስ ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾም በኋላ የትንሣኤን በዓል ታከብራለች፡፡ ለምእመናንም ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ ዳግመኛ ልክ እንደ ክርስቶስ እንደምንነሣ ታስተምራለች፡፡

# ማጠቃለያ

- በክርስቶስ ትንሣኤ ደቀ መዛሙርቱ እጅግ በጣም ደስተኛ ሆነዋል፡፡ እግዚአብሔርንም አመስግነዋል፡፡
- ሕፃናት እናንተም በደስታ የትንሣኤውን በዓል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከቤተሰቦቻችሁ ጋር እያመሰገናችሁ አክብሩ፡፡

## ጥያቄዎች፡-

1. ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤ በዓልን የምታከብረው ለምንድን ነው?
2. ‹‹ትንሣኤ›› ማለት ምን ማለት ነው?
3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስንተኛው ቀን ተነሣ?
4. የክርስቶስን መነሣት ደቀ መዛሙርቱ እንዴት አወቁ?
5. በክርስቶስ ትንሣኤ ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት ምን ተሰማቸው?

# ተግባር

- መምህር ስለ ትንሣኤ በዓል ለሕፃናት ሰፊ ገለጻ ያደርጉላቸው፡፡
- የትንሣኤ መዝሙራትን ለሕፃናት ያስጠኑዋቸው፡፡
- ሕፃናት በመጽሐፉ ላይ ያለውን የክርስቶስን ትንሣኤ የሚያሳየውን ሥዕል እንዲቀቡ አድርጉአቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በቃል የሚጠኑ ትምህርቶች

## ሃምሳ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ልጆች ስለ ቤተ ክርስቲያን የቃል ትምህርት ምንነት ተገንዝበው መሠረታዊ የሆኑትን የጸሎት ዓይነቶችና ይዘታቸውን አውቀው ይጸልያሉ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-**

- ‹‹እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ።›› ማቴ ፮ ÷ ፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-**

- ማቴ ፮ ÷ ፭ - ፲፭

## መግቢያ

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቃል ትምህርት ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ የማስተማሪያ ዘዴ ነው። እንደ ዛሬው መጻሕፍት እንደልብ በማይገኙበት ዘመን ለቤተ ክርስትያን ትልቅ ውለታን ውሏል። አባቶቻችን የጸሎት መጻሕፍትን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜን፣ የዜማ መጻሕፍትን፣ መዝሙረ ዳዊትን… ወዘተ በቃላቸው በማጥናት የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎትን ይፈጽሙባቸው ነበር።
- የቃል ትምህርት ከሚሰጠው መንፈሳዊ ጥቅም ባሻገር የማስታወስ ችሎታችንን ይጨምራል። ስለዚህ ይህን የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ሕፃናት እንዲጠቀሙበት ማድረግ የሁላችንም ሐላፊነት ነው። በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የቃል ትምህርቶች በመምህሩ እና በወላጆቻቸው እየታገዙ ሕፃናት እንዲማሩ እንጋብዛለን።

www.zeorthodox.org

### መልእክተ ዮሐንስ

- መልእክተ ዮሐንስ ሐዋሪያ ወልደ ዘብዴዎስ ቀዳማዊ፤ ንዜንወክሙ በእንተ ውእቱ ዘሀሎ እምቅድም ውእቱ ዘሰማዕናሁ በእዘኒነ ወዘርኢናሁ በአዕይንቲነ ወዘጠየቅናሁ ወዘገሠሣሁ እደዊነ በእንተ ነገረ ሕይወት፤ እስመ ሕይወት ተዐውቀት ለነ ወርኢናሃ ወስምዐ ኮነ ወንዜንወክሙ ለክሙኒ ንሕነ ሕይወተ እንተ ለዓለም እንተ ሀለወት ኀበ

አብ ወተዐውቀት ለነ፡፡ ወርኢናሃ ወሰማዕናሃ ወንዜንወክሙ ለክሙኒ ከመ አንትሙኒ ትኩኑ ሱታፌ ምስሌነ ወሱታፌነሳ ምስለ አብ ወምስለ ወልዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወዘንተ ንጽሕፍ ለክሙ ከመ ትፍሥሕትክሙ ፍጽምተ ትኩን፡፡

## ትርጉም

- መጀመሪያይቱ የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፡፡ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል፣ እንመሰክርማለን፡፡ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኂለን፡፡ እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኂለን፡፡ ኅብረታችንም ከአባቱ ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው፡፡ ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን እንጽፍላችኂለን፡፡

## ጸሎት ዘዘወትር

- አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ በቅድስት ሥላሴ እንዘ አአምን ወእትመሐፀን እክሕደከ ሰይጣን በቅድመ ዛቲ እምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ይእቲ ስምዕየ ማርያም ጽዮን ለዓለመ ዓለም፡፡

## ትርጉም

- በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ትእምርተ መስቀል ፊቴንና መላ ሰውነቴን ሦስት ጊዜ አማትባለሁ፡፡ አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በቅድስት ሥላሴ እያመንኩና እየተማፀንኩ ጠላቴ ሰይጣንን በዚች በእናቴ በቤተ ክርስቲያን ፊት ቆሜ እክድሃለሁ፡፡ ለዚህም ምስክሬ ማርያም ናት፤ በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም እሷን አምባ መጠጊያ አድርጌ እክድሃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

## ነአኵተከ

- ነአኵተከ እግዚኦ ወንሴብሐከ ንባርከከ እግዚኦ ወንትአመነከ፡፡ ንገኒለከ እግዚኦ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ፡፡ ንሰግድ ለከ ኦ ዘለከ ይሰግድ ኵሉ ብርክ ወለከ ይትቀነይ ኵሉ ልሳን አንተ ውእቱ አምላከ አማልክት ወእግዚኦ አጋዕዝት ወንጉሠ ነገሥት

አምላክ አንተ ለኲሉ ዘሥጋ ወለኲላ ዘነፍስ፣ ወንጼውዐከ በከመ መሐረነ ቅዱስ ወልድከ እንዘ ይብል አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ።

## ትርጉም

- አቤቱ እናመሰግንሃለን፣ አቤቱ እናከብርሃለን፣ አቤቱ እንገዛልሃለን፣ አቤቱ ቅዱስ ስምህን እናመሰግናለን፤ ጉልበት ሁሉ የሚሰግድልህ አቤቱ እንሰግድልሃለን፤ አንደበትም ሁሉ ለአንተ ይገዛል፤ የአምላኮች አምላክ የጌቶች ጌታ የንጉሦችም ንጉሥ አንተ ነህ። የሥጋም የነፍስም ፈጣሪ አንተ ነህ። እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ እንዲህ ብላችሁ ጸልዮ ብሎ ቅዱስ ልጅህ እንዳስተማረን እንጠራሃለን።

## አቡነ ዘበሰማያት

- አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ። ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም። ኀድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመሕነኒ ንኀድግ ለዘአበሰ ለነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት፤ አላ አድነነ ወባልሐነ እምኲሉ እኩይ፣ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም።

## ትርጉም

- አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር፤ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማያት እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ፤ በደላችንንም ይቅር በለን፣ እኛም የበድሉንን ይቅር እንደምንል፤ አቤቱ ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ መንግሥት ያንተ ናት እና ኃይል ክብር ምስጋና ለዘለዓለሙ አሜን።

www.zeorthodox.org

## በሰላመ ገብርኤል

- በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በኀሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ። ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ፣ ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፣ ሰአሊ ወጸልይ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይስረይ ለነ ኃጣውኢነ።

## ትርጉም

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን፤ በሐሳብሽ ድንግል ነሽ፣ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፤ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ለንቺ ይገባሻል፤ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤ የማሕፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው፤ ጸጋን የተመላሽ ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ልዑል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና፤ ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታና ምሕረትን ለምኚልን፣ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ አሜን።

## ተግባር

- መምህር ልጆች የተማሯቸውን ጸሎቶች እንዲለማመዱና እንዲጸልዩ ያድርጓቸው።

www.zeorthodox.org

# ፍልሰታ

## ሃምሳ አራተኛ ሳምንት

### የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ሕፃናት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጾም እና ትንሣኤ እንዲሁም ዕርገት አውቀው፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-

- “እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል” ሉቃ ፩÷ ፵፰

### ተጨማሪ ምንባባት፡-

- ሉቃ. ፩÷፳፮ -፶፮፣ ማቴ. ፮÷፲፮-፲፰

### መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡ ሕፃናቱን ስለጾም የሚያውቁትን ነገር ይጠይቁዋቸው፡፡ ስለ እመቤታችን ሕይወት ሕፃናት ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ እና ምሳሌ ይንገሩአቸው፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት፡-

- የፍልሰታ ጾም የእመቤታችን ቅድስት ማርያም ጾም በመባል ይታወቃል፡፡ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት፣ ትንሣኤና ዕርገት ምስጢር ለሐዋርያት የተገለጠበት ታሪክ መታሰቢያ ጾም ነው፡፡
- እመቤታችን ካረፈች በኋላ ክቡር ሥጋዋ በገነት ተቀምጦ ነበር፡፡ ለጊዜው ከሐዋርያት መካከል ለማየት የበቃው ቅዱስ ዮሐንስ ብቻ ነበር፡፡ ዮሐንስም ለሌሎች ሐዋርያት ይህን ዜና ነገራቸው፡፡ ሐዋሪያትም ‹‹የዚህ ታላቅ ምስጢር ተካፋዮች ሳንሆን ለምን ቀረን?›› ብለው ከነሐሴ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 14 ቀን በጾምና በጸሎት ተወስነው እግዚአብሔር የእመቤታችንን ክቡር ሥጋ እንዲያሳያቸው ጠየቁ፡፡
- ነሐሴ 14 ቀን እግዚአብሔር የእመቤታችንን ሥጋ ስለሰጣቸው ክቡር ሥጋዋን ተቀብለው በጌቴሴማኒ ቀብረዋታል፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነሐሴ 16 ቀን በሦስተኛው ቀን ተነሥታ ወደ ሰማይ አርጋለች፡፡
- ይህን ትንሣኤዋንና ዕርገቷን የተመለከተው ሐዋርያው ቶማስ ብቻ ነበር፡፡ ስለዚህ ሐዋርያት እንደገና በዓመቱ ከነሐሴ 1 ቀን ጀምረው እስከ ነሐሴ 15 ቀን ከጾሙ በኋላ

www.zeorthodox.org

በነሐሴ 16 ቀን የእመቤታችን ትንሣኤና ዕርገት ለሁሉም ደቀ መዛሙርት ተገልጾላቸዋል፡፡

- ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሐዋርያትን ፈለግ በመከተል እና ከእመቤታችን በረከት ለማግኘት በየዓመቱ የማርያምን ጾም ብዙ ክርስቲያኖች ይጾማሉ፡፡
- በተለይ በሀገራችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሁሉ የእመቤታችንን ጾም እጅግ በተለየ መንፈሳዊ ድምቀት እና ሥርዓት ይጾማሉ፡፡ ሕፃናትና ወጣቶች በትጋት የሚጾሙት እና ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት ጊዜም ነው፡፡
- ብዙ ምእመናን የጾም ጊዜን በጸሎት ተወስነው የሚያሳልፉበት ከእግዚአብሔር ምሕረትና ይቅርታ የሚለምኑበትም ጊዜ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

- ሐዋርያት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የተለየ ፍቅር ስለነበራቸው በጸሎትና በጾም የእመቤታችንን ትንሣኤና ዕርገት ለማየት ችለዋል፡፡ ሕፃናት እናንተም እንደ ሐዋርያት ለእመቤታችን ጥልቅ ፍቅር ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ የእግዚአብሔርን ምስጢር ለማየት እንድትችሉ በጸሎት፣ በምስጋና እንዲሁም በጾም እደጉ፡፡

### ጥያቄዎች

1. የእመቤታቸን ቅድስት ድንግል ማርያምን ጾም የጀመረው ማን ነው? በምን ምክንያት?
2. የእመቤታችን ማርያም ጾም መቼ ነው የሚጾመው?
3. የእመቤታችን ሥጋ በገነት መሆኑን ቀድሞ ያየው ሐዋርያ ማን ነው?
4. ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ በየት ቀበሩት?
5. ለመጀመሪያ ጊዜ የእመቤታችንን ትሣኤና ዕርገት ያየው ሐዋርያ ማን ይባላል?
6. ነሐሴ 16 ቀን የሚከበረው የእመቤታችን በዓል ምን ይባላል?

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህሩ ሕፃናት እመቤታችንን ጾም በፍቅር እንዲጾሙ እና እንዴት መጾም እንደሚገባቸው ሥርዓተ ቤተ ክርቲያንን ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ እና ምሳሌ ይግለጹላቸው፡፡
- ሕፃናት በሥዕል መጽሐፉ ላይ ያለውን የሐዋርያትን እና የእመቤታችንን ሥዕል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።


www.zoorthodox.org

- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.

www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሠራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ

ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ ዐሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸዉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸዉ። በዚህም መሠረተ ጥርት ያለዉን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸዉ እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸዉ መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸዉም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

www.zoorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ

ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣ ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለዉን ርእስ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸዉን ተረድተዉና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | ዐውደ ዓመት | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | ሥነ ፍጥረት/አንድ/ | 4 | | ሁለተኛ | |
| 3. | ሥነ ፍጥረት/ሁለት/ | 7 | | ሦስተኛ | |
| 4. | ሥነ ፍጥረት/ሦስት/ | 10 | | አራተኛ | |
| 5. | አዳም ለእንስሳት ስም አወጣላቸው | 12 | | አምስተኛ | |
| 6. | አዳም እና ሔዋን በገነት | 14 | | ስድስተኛ | |
| 7. | የተወደደው የአቤል መሥዋዕት | 16 | | ሰባተኛ | |
| 8. | ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ታዘዘ | 18 | | ስምንተኛ | |
| 9. | ኖኅ ያቀረበው መሥዋዕት | 20 | | ዘጠነኛ | |
| 10. | ማክበር ያስባርካል | 21 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | የሰናዖር ግንብ | 23 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | የአብርሃም መጠራት | 25 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | አብርሃም እና ሎጥ | 27 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | አብራም በካህኑ ተባረከ | 29 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | ኢየሱስ እናቱን ይታዘዛት ነበር | 31 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ኢየሱስ ተጠመቀ | 33 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | አሮጊቷ ሣራ ወንድ ልጅ ወለደች | 35 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | ሕፃኑ ሙሴ | 37 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | ያዕቆብ በቤቴል ያየው ሕልም | 39 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | ይስሐቅ እና ርብቃ | 41 | | ሃያኛ | |
| 21. | ርብቃ መንታ ልጆችን ወለደች | 44 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም ተረጎመ | 46 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | የጥበብ ሰዎች | 48 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | ወደ ግብጽ ሸሹ | 50 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | ያዕቆብ እና ዔሳው ታረቁ | 52 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | ታዛዡ ይስሐቅ | 54 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ይስሐቅ ክፉውን በበጎ አሸነፈ | 56 | | ሃያ ሰባተኛ | |
| 28. | ዮሴፍ ለቤተሰሱ ይቅርታ አደረገ | 58 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ሳሙኤል ዳዊትን ቀባው | 60 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | ዳዊት ጎልያድን አሸነፈ | 63 | | ሠላሳኛ | |


www.zeorthodox.org


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 31. | ዳዊት እና ዮናታን | 65 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | ተአምረኛው ዓሣ አጠማመድ | 68 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | ጌታችን ዓይነ ሥውሩን አዳነ | 70 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | ነቢዩ ኤልያስ በቁራዎች ተመገበ | 71 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | ነቢዩ ኤልያስ እና መበለቲቱ /አንድ/ | 73 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | ነቢዩ ኤልያስ እና መበለቲቱ /ሁለት/ | 75 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | የሦስቱ ሕፃናት ጽናት | 77 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ ተጣለ | 79 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | በማኅፀን የተቀደሰ ነቢይ | 81 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ | 83 | | ዐርባኛ | |
| 41. | የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት | 85 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | የጌታችን ልደት | 87 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | መላእክት እና እረኞች | 89 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | ዮሴፍ በአባቱ ቤት | 90 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ሳሙኤል በእግዚአብሔር ተጠራ | 92 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | ዮሴፍ ወደ ግብጽ ወረደ | 95 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | በገና ደርዳሪው ዳዊት | 97 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | አቡነ አረጋዊ | 99 | | ዐርባ ስምንተኛ | |
| 49. | እምነትሽ አድኖሻል | 101 | | ዐርባ ዘጠነኛ | |
| 50. | የመበለቲቱ ትልቅ ስጦታ | 103 | | ሃምሳኛ | |
| 51. | ሆሣዕና | 105 | | ሃምሳ አንደኛ | |
| 52. | የጌታ ትንሣኤ | 107 | | ሃምሳ ሁለተኛ | |
| 53. | በቃል የማጠኑ ትምህርቶች | 109 | | ሃምሳ ሦስተኛ | |
| 54. | ፍልሰታ | 113 | | ሃምሳ አራተኛ | |


www.zeorthodox.org

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ። በመጨረሻም የሚያስ ፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም።

## መታሰቢያነቱ




በትምህርተ ቤተ ክርስቲያንና በክህነት ወልደው ላሳደጉኝ ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ይሁንልኝ።

www.zeorthodox.org

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል።

# መሠረተ ሕይወት

## ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

**ስሙዓስ ሕፃናት**

ተማሪዎች የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ

www.zeorthodox.org

አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ነሐሴ

፳፻፫ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፩ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት**

አድራሻ፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

www.zeorthodox.org

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website፡- www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው